# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች - አንደኛ

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-9)

I. ጳውሎስ አስቀድሞ በሰማቸው ችግሮች ላይ የተደረገ ውይይት (1፥10—6፥20)

(ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሠተ መለያየት (1፥10—4፥21)

1. አራቱ ቡድኖች (1፥10-17)
2. የመለያየት ምክንያቶች (1፥18—4፥5)

(ሀ) ጥበብን በተመለከተ የነበረው የተሳሳተ አስተሳሰብ (1፥18—3፥4)

(ለ) የክርስትናን አገልግሎት በተመለከተ የነበረው የተሳሳተ አስተሳሰብ (3፥5—4፥5)

3. ለዕርቅ የቀረበ ጥያቄ (4፥6-21)

*መርሕ:* ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አንድ አካል ስለሆነች (ከ12፥12...ጋር ያነጻጽሩ) በተለያዩ ብልቶች መከፋፈል የለባትም (1፥10:13)።

(ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ግብረገባዊ ችግሮች (5፥1—6፥20)

1. በሥጋ ዘመዳሞች መካከል የተፈጸመ የዝሙት ችግርና የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዐት እርምጃ (5፥1-13)
2. የክርስቲያኖች በአሕዛብ ዳኞች ፊት የመካሰስ ችግር (6፥1-11)
3. የዝሙት ኀጢአት (6፥12-20)

*መርሕ:* ከጌታ ጋር የተባበራችሁ እናንተ ለእርሱ ክብርን የሚያመጣ አድርጋችሁ ራሳችሁን አቅርቡ (6፥17:20)

II. የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለጻፉአቸው ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች (7፥1—16፥9)

(ሀ) ጋብቻን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች (7፥1-40)

1. ማግባትና አለማግባት (7፥1-9)
2. በጋብቻ ውስጥ ያለ ክርስቲያናዊ ግዴታ (7፥10-16)
3. በተጠሩበት ሁኔታ የመርካት መርሕ (7፥17-24)
4. ላላገቡ ሰዎች የተሰጠ ምክር (7፥25-38)
5. ዳግም ስለ ማግባት የተሰጠ ትእዛዝ (7፥39-40)

*መርሕ:* እግዚአብሔር ስለ መንግሥቱ ሲል ለአንዳንዶች ባል ወይም ሚስት የመሆን ስጦታ ሲሰጥ፣ ለሌሎች ደግሞ ያለማግባትን ስጦታ ይሰጣል (7፥7:32)።

(ለ) የክርስቲያናዊ ነጻነትን አጠቃቀም በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች (8፥1—11፥1)

1. ለጣዖት የተሠዋን ምግብ ስለ መብላት (8፥1-13)
2. ጳውሎስ ነጻነቱን ሥርዐት ባለው መንገድ መጠቀሙ (9፥1-27)
3. ድፍረት የተሞላ በራስ የመተማመን መንፈስን በሚመለከት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (10፥1-13)
4. የጣዖት ግብዣ ከጌታ ማእድ ጋር ኅብረት እንደሌለው (10፥14-23)
5. አንዳንድ አጠቃላይ መርሖችና ተግባራዊ ምክሮች (10፥24—11፥1)

*መርሕ:* ለእግዚአብሔር ክብር የሚያመጣውን ማንኛውንም ነገር አድርጉ፤ ሌሎችን ሊያሰናክል የሚችለውን (10፥31-32) ወይም እናንተን ከሩጫ ውጪ የሚያደርጋችሁን ነገር አታድርጉ (9፥24-27)።

(ሐ) የጉባኤ አምልኮን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች (11፥2—14፥40)

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሴቶች ጠጉርን የመሸፈን ጉዳይ (11፥2-16)

2. የጌታ እራት ሥርዐት በሚፈጸምበት ጊዜ ሊኖር የሚገባ ባሕርይ (11፥17-34)
3. መንፈሳዊ ስጦታዎች (12፥1—14፥40)

*መርሕ:* ሁሉም ነገር በአግባብና በሥርዐት ይሁን (14፥40)

(መ) ትንሣኤን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች (15፥1-58)

1. ጥያቄ: አንዳንዶች እንዴት የሙታን ትንሣኤ የለም ለማለት ቻሉ? (15፥12)
   *መልስ:* የሙታን ትንሣኤ ርግጠኝነት (15፥1-34)
2. ጥያቄ: ሙታን እንዴት ይነሣሉ? የሚወጡትስ በምን ዐይነት አካል ነው? (15፥35)
   *መልስ:* የትንሣኤ አካል ተፈጥሮ (15፥35-57)
3. የጥያቄዎች ማጠቃለያ (15፥58)

*መርሕ:* የክርስቶስ ከሞት መነሣት እርሱ ዳግም በሚመለስበት ጊዜ የክርስቶስ የሆኑት ከሞት እንደሚነሡ ዋስትና ነው (15፥22-23)

(ሠ) ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚደረግ የገንዘብ መዋጮን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች (16፥1-9)

የመጨረሻ ትእዛዞች (16፥10-24)

**ጸሓፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የቤተ ክርስቲያን ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው*

**የተጻፈበት ዘመን፤** *55/56 ዓ.ም.*

**ታሪካዊ ዳራ**

ቆሮንቶስ ጥንታዊት የግሪክ ከተማ ስትሆን፣ በጳውሎስ ዘመን በብዙ መንገድ ታዋቂ የነበረች የግሪክ መዲና ናት። በአሁን ዘመን እንዳሉት ሀብታም ከተሞች ቆሮንቶስ በዕውቀት የታበየች፣ በሀብት የበለጠገችና በኢግብረገባዊ ሕይወት የረከሰች ነበረች። ማንኛውም ዐይነት ኀጢአት በዚህች በወጣላት ዓለማዊ ከተማ ተስፋፍቶ።

ከጵርስቅላና ከአቂላ (16፥19) እንዲሁም ከራሱ ሐዋርያዊ ቡድን (ሐሥ 18፥5) ጋር በመጣመር፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል ጉዞው (ሐሥ 18፥1-17) ዐሥራ ስምንት ወር በቆሮንቶስ ከተማ ለአገልግሎት በቈየበት ጊዜ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ። ከቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ጥቂቶቹ አይሁድ ሲሆኑ፣ በአብዛኛው ጣዖት አምላኪዎች የነበሩ አሕዛብ ናቸው። ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ከሄደ በኋላ የእርሱን ሐዋርያዊ ሥልጣንና ትምህርት የሚሹ፣ ደብዳቤ በመጻፍና ጉብኝት በማድረግ መልስ እንዲሰጥባቸው የሚያስገድዱ አጠያያቂ ጕዳዮች በታዳጊዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተከሠቱ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን የመጀመሪያውን የቆሮንቶስን መልእክት የጻፈው ሦስት ዓመት በኤፌሶን ባገለገለበት (ሐሥ 20፥31) በሦስተኛው የወንጌል ጉዞው ወቅት ነበር (ሐሥ 18፥23—21፥16)። ጳውሎስ በኤፌሶን ሳለ በነበረበት ጊዜ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ወሬ ደረሰው (1ቆሮ 1፥11)፤ ከዚያም በኋላ የቆሮንቶስ ጉባኤ ተወካዮች በተለያዩ ጕዳዮች ላይ የእርሱን ምክር የሚጠይቅ (7፥1 ይመ፤ ከ8፥1፣ 12፥1፣ 16፥1 ጋር ያነጻጽሩ) ደብዳቤ ይዘውለት መጡ (16፥17)። ለሰማው ወሬና ከቆሮንቶስም ለደረሰው ደብዳቤ ምላሽ ይሆን ዘንድ ጳውሎስ ይህን መልእክት ጻፈ።

**ዐላማ**

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልእክት ሲጽፍ የሚከተሉት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩት፤ (1) ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሰማው ከባድ ችግር ላይ ተገቢውን እርምት ለመስጠት ነው። የቆሮንቶስ ምእመናን በቀላሉ የተመለከቷቸውን እነዚህን ሕገወጥ ድርጊቶች ጳውሎስ ግን እንደ ከባድ ኀጢአት ቈጥሮአቸዋል። (2) የቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፉት ደብዳቤ ውስጥ ለተጠቀሱት አያሌ ጥያቄዎች ምክርና መመሪያ ለመስጠት ነው። በእነዚህም ውስጥ የአስተምህሮ እንዲሁም በግልና በጋራ ሊኖር ስለሚገባ የባሕርይና የቅድስና ጕዳዮች ተካትተዋል።

### ቅኝት

ይህ መልእክት የሚናገረው ምእመናን “ሥጋውያን” (3፥1-3) ወይም ዓለማውያን በሚሆኑበት ጊዜና ራሳቸውን በአካባቢያቸው ካለው ጣዖት አምላኪ ኅብረተሰብ መለየት በሚያቅታቸው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሊያጋጥሟት ስለሚችሉ ችግሮች ነው (2ቆሮ 6፥17)፤ እነዚህም ችግሮች መለያየትን (1፥10-13፤ 11፥17-22)፣ በቤተ ዘመድ መካከል የሚደረግ ጋብቻን በቸልተኝነት መመልከትን (5፥1-13)፣ በአጠቃላይ ወሲባዊ ኢግብረገባዊነትን (6፥12-20)፣ በክርስቲያኖች መካከል በተፈጠረ ጠብ በአሕዛብ ዳኞች ፊት መካሰስን (6፥1-11)፣ ሐዋርያዊ እውነትን በተመለከተ የነበረውን ሰብዓዊ አስተሳሰብን (ምዕ 15) እንዲሁም “ክርስቲያናዊ ነጻነትን” (ምዕ 8፡10) በተመለከተ የተፈጠሩ ግጭቶችን የመሳሰሉ ነበሩ። ሐዋርያው ጳውሎስ በተጨማሪ በድንግልና መኖርንና ማግባት (ምዕ 7) የጉባኤ አምልኮን እንዲሁም የጌታን እራትና (ምዕ 11—14) ለኢየሩሳሌም ቅዱሳን የተደረገውን የገንዘብ መዋጮ (16፥1-4) በተመለከተ ለቆሮንቶስ ምእመናን ትምህርት ሰጥቶአል።

በአንደኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ሐሳቦች አንዱ በጋራ አምልኮ ዐውድ ውስጥ ስለሚኖሩት መገለጦችና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርት ነው (ምዕ 12—14)። በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት ሌሎች ክፍሎች ይልቅ እነዚህ ምዕራፎች በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የአምልኮ ባሕርይና ይዘት ያመለክታሉ (ከ14፥26-33 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ዐላማ፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች (12፥28-30) በተጠሩ ታማኝ አማኞች (12፥4-10) እና ግለሰቦች አማካይነት የሚፈጸመውን ብዛት ያላቸው የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ መገለጦችን እንደሚያካትት ጳውሎስ አመልክቶአል፤ ይህም አንድነት በልዩነት በሰው አካል አሠራሮች ውስጥ ከሚታየው አንድነት ጋር ተመሳሳይ ነው (12፥12-27)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በጋራ ለሚሠሩት ሥራ መመሪያን ለመስጠት፣ በጉባኤ የሚገለጡ ጸጋዎች ወይም ስጦታዎች ሁሉ ከፍቅር የሚመነጩና (ምዕ 13) የተሰበሰበው ምእመን የሚታነጽበት መሆን እንዳለባቸው (12፥7፤ 14፥4-6፡26) በማሳሰብ ጳውሎስ በግል በመታነጽና በጋራ በመታነጽ መካከል ያለውን አስፈላጊ ልዩነት አመልክቶአል (14፥2-6፡12፡16-19፡26)።

### ልዩ ገጽታ

አንደኛ ቆሮንቶስን ልዩ የሚያደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት መልእክቶች ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ በችግር ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ነው። በቆሮንቶስ ስለነበሩት አያሌ ችግሮችና ጉዳዮች በሚናገርበት ጊዜ ጳውሎስ በየትኛውም ቦታ ላሉ አብያተ ክርስቲያናት ሊጠቅሙ የሚችሉ ግልጽና ዘለቄታ ያላቸውን መንፈሳዊ መርሖዎች ሰጥቶአል (ለምሳሌ 1፥10፤ 6፥17፡20፤ 7፥7፤ 9፥24-27፤ 10፥31-32፤ 14፥1-10፤ 15፥22-23)። (2) ስለ መለያየት፣ ስለ ጌታ እራትና ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ገለጻ በተደረገባቸው ሁኔታዎች የክርስቶስ አካል በሆነችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለው አጠቃላይ አንድነት ላይ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ በአጽንዖት ይገልጻል። (3) ይህ መልእክት በድንግልና መኖርን፣ ማግባትንና ዳግም ማግባትን (ምዕ 7)፣ የጌታ እራትን (10፥16-21፤ 11፥17-34)፣ በጋራ ስብሰባዎች የሚገለጡትን ስጦታዎች ማለትም በልሳን መናገርን፣ ትንቢትን መናገርንና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን (ምዕ 12—13) እንዲሁም አጋፔ ፍቅርንና (ምዕ 13) የአካል ትንሣኤን (ምዕ 15) የመሳሰሉትን እጅግ አስፈላጊ የሆኑና ሰፋፊ የአዲስ ኪዳን ትምህርቶችን የሚያካትት ነው። (4) ከቤተ ክርስቲያን ሥርዐት አንጻር ለመጋቢነት አገልግሎት እጅግ ጠቃሚ የሆነ ጥበብን ይሰጣል (ምዕ 5)። (5) ርኩሰትን በማድረግ ጸንተው የሚመላለሱና ክርስቶስን አጥብቀው የማይዙ ከእምነት መንገድ ስተው ሊወድቁ እንደሚችሉ በአጽንዖት ያሳያል (6፥9-10፤ 9፥24-27፤ 10፥5-12፡20-21፤ 15፥1-2)።

### የአንደኛ ቆሮንቶስ መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ አንደኛ ቆሮንቶስን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ19 ቀናት መነበብ ይኖርበታል።

❏ 1 ❏ 2 ❏ 3 ❏ 4 ❏ 5 ❏ 6 ❏ 7 ❏ 8 ❏ 9 ❏ 10፥1-13 ❏ 10፥14—11፥1
❏ 11፥2-34 ❏ 12 ❏ 13 ❏ 14፥1-25 ❏ 14፥26-40 ❏ 15፥1-34 ❏ 15፥35-58 ❏ 16

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ እንዲሆን ከተጠራው ከጳው
ሎስ፣ ከወንድማችንም ከሶስቴንስ፤
[2]በቆሮንቶስ ላለችው የእግዚአብሔር ቤተ ክር
ስቲያን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ተቀድሰው፣
የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን
የኢ የሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ሆነው
ከሚ ጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን
ለተጠሩት፤
[3]ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## ምስጋና

[4]በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ተሰጣችሁ
ጸጋ ዘወትር ስለ እናንተ እግዚአብሔርን
አመሰግናለሁ። [5]ምክንያቱም በማናቸውም
ነገር ይኸውም በንግግር ሁሉ፣ በዕውቀትም
ሁሉ በእርሱ በልጽጋችኋል፤ [6]ስለ ክርስቶስ
የመሰከርንላችሁም በእናንተ ዘንድ
ጸንቶአል። [7]ስለዚህ የጌታችንን የኢየሱስ
ክርስቶስን መገለጥ በጉጉት በመጠባበቅ
ላይ ሳላችሁ፣ ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ
አይጐድልባችሁም። [8]በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትገኙ
እርሱ እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንቶ
ይጠብቃችኋል። [9]ወደ ልጁ፣ ወደ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራ ችሁ
እግዚአብሔር የታመነ ነው።

1ቆሮ 12፥1-31

1፥1 ሐሥ18፥17፤ ሮሜ1፥1፤ 2ቆሮ1፥1፤ ኤፌ1፥1፤ 2ጢሞ1፥1
1፥2 ሐሥ2፥21፤ 18፥1፤ ሮሜ1፥7፤ 1ቆሮ10፥32
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ሮሜ1፥8
1፥5 2ቆሮ8፥7፤ 9፥11
1፥6 2ተሰ1፥10፤ 1ጢሞ2፥6፤ ራእ1፥2
1፥7 ማቴ16፥27፤ ሉቃ17፥30፤ ሮሜ1፥11፤ 1ቆሮ12፥1-31፤ 1ተሰ1፥10፤ 2፥19፤ ቲቶ2፥13፤ ያዕ5፥7:8፤ 1ጴጥ1፥13፤ 2ጴጥ3፥12፤ ራእ1፥7
1፥8 አሞ5፥18፤ 1ቆሮ5፥5፤ ፊል1፥6:10፤ 2፥16፤ 1ተሰ3፥13፤ 5፥2
1፥9 ዘዳ7፥9፤ ኢሳ49፥7፤ ሮሜ8፥28፤ 1ቆሮ10፥13፤ 1ተሰ5፥24፤ 2ተሰ3፥3፤ 2ጢሞ2፥13፤

## በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሠተ መለያየት

[10]ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ መለያ
የት እንዳይኖር፣ አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብ
እንዲኖራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም እንድት
ስማሙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም እለምናችኋለሁ። [11]ወንድሞች ሆይ፤
በመካከ ላችሁ ክርክር እንዳለ ከቀሎዔ ቤተ
ሰብ ሰምቻለሁ፤ [12]ነገሩም እንዲህ ነው፤
ከእናንተ አንዱ፣ "እኔ የጳውሎስ ነኝ" ሲል፣
ሌላው፣ "እኔ የአጵሎስ ነኝ" ይላል፤ ደግሞም
አንዱ፣ "እኔ የኬፋ[a] ነኝ" ሲል፣ ሌላው
ደግሞ፣ "እኔስ የክርስቶስ ነኝ" ይላል።
[13]ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሎአልን?
ጳውሎስስ ለእናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ
በጳውሎስ[b] ስም ተጠምቃችኋልን? [14]ከቀር
ስጳስና ከጋይዮስ በስተቀር ከእናንተ ማን ንም
ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤
[15]ስለዚህ በስሜ መጠመቁን የሚናገር ማንም
የለም። [16]በርግጥ የእስጢፋኖስንም ቤተ ሰው
አጥምቄአለሁ፤ ከእነዚህ ሌላ ግን ማጥመቄ
ትዝ አይለኝም። [17]ክርስቶስ የላከኝ ወንጌልን

1፥9 ዕብ10፥23፤ 11፥11፤ 1ዮሐ1፥3 1፥10 ሮሜ7፥1፤ 15፥5፤ 1ቆሮ11፥18 1፥11 ሐሥ11፥14 1፥12 ዮሐ1፥42፤ ሐሥ18፥24፤ 1ቆሮ3፥4:22፤ 9፥5 1፥13 ማቴ28፥19 1፥14 ሐሥ18፥8፤ 19፥29 1፥16 ሐሥ16፥14፤ 1ቆሮ16፥15 1፥17 ዮሐ4፥2፤ ሐሥ2፥38፤ 1ቆሮ2፥1:4:13

*[a]1፥12 ጴጥሮስ ማለት ነው*
*[b]1፥13 ወይም ወደ ጳውሎስ፤ እንዲሁም ቍ 15 ይመ*

**1፥2 ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤** በሐሥ 9፥13 ላይ "የቅዱሳንን" ትርጓሜ በተመለከተ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**1፥7 ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ አይጐድልባችሁም፤** እግዚአብሔር በጸጋው (ቍ 4) ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ስለሰጣቸው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን ያደንቃቸዋል። እንደዚህ ዐይነት ስጦታዎች እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ሲሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው፤ ያለ እነዚህ ስጦታዎች አማኞች እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እርስ በርስ መበረታታትና መረዳዳት አይችሉም። በዚህ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ እነዚህን ስጦታዎች ቸል ያለበትን ስፍራ አናገኝም። ነገር ግን እግዚአብሔር እንዳሰበው በተሰጣቸው ስጦታ ያገለግሉ ዘንድ የቆሮንቶስ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን እንዲቀበሉ ጳውሎስ አስተሳሰባቸውን ለመለወጥ ይፈልጋል።

**1፥7 የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ በጉጉት በመጠባበቅ፤** የጥንት ክርስቲያኖች ክርስቶስ በቅርብ እንደሚመለስ በጉጉት እየተጠባበቁ ይኖሩ ነበር (ማቴ 24፥42 እና ማብ፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)። በየቀኑ ያንን ታላቅ ተስፋ በመጠባበቅ እየኖሩ በጌታ ዳግም ምጽአት እውነታ ላይ እምነታቸውን በማጽናት ቆመው ነበር። ክርስቲያን የሚጠባበቀው በመጨረሻው ቀን በአጠቃላይ የሚፈጸሙትን ሁነቶች ሳይሆን፣ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በአካል ዳግም መምጣት እንደ ሆነ ልብ ይበሉ (ከ1ተሰ 1፥9-10፤ 4፥13-17፤ ከቲቶ 2፥13፤ ከዕብ 9፥28 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 824 ላይ፣ *"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**1፥12 እኔ የጳውሎስ ... የአጵሎስ ... የኬፋ ነኝ፤** በመሪዎች ስም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየት ተጀመረ፤ አንዳንዶቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሕይወታቸውን ከራሱ ከወንጌል ጋር ከማያያዝ ይልቅ ከተወሰኑ የወንጌል አገልጋዮች ጋር አጣብቀው ነበር። ከክርስቶስ በቀር እርሱም ሆነ ሌላው አገልጋይ እንዳልተሰቀሉላቸው በማሳሰብ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን አስተሳሰብ አወገዘ። ይህንን የመሰለ ስህተት ዛሬም ቢሆን ይደረጋል። አንዳንድ አማኞች ክርስቶስንና ቃሉን አጥብቀው ከመያዝ ይልቅ ከአንድ መጋቢ ወይም ከአንድ ወንጌላዊ ጋር ራሳቸውን ያጣብቃሉ። እንዲህ ዐይነቱ ዝንባሌ የክርስትና መርሖችን እንዲክዱ ብሎም ቤተ ክርስቲያንን እንዲከፋፍሉ ያደርጋቸዋል። ምን ጊዜም ቢሆን ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ይልቅ ፍቅራችንንና ታማኝነታችንን በአገልጋይ ወይም በሰው ላይ ከማድረግ ልንጠነቀቅ ይገባል።

**1፥12 እኔስ የክርስቶስ ነኝ፤** "የክርስቶስ ነኝ" የሚለው ቡድን አባላት ምናልባት በመንፈሳዊነትም ሆነ "በጥበብ" እበልጣለሁ የሚሉ የሐዋርያው ተቃዋሚ የሆኑ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ያካተተ ሳይሆን አይቀርም (4፥18-19)። እነርሱም ዕውቀታቸው (8፥1) ከሕግ ቍጥጥር (6፥12፤ 10፥23) እና ከግብረገባዊነት ጥያቄ (5፥2) በላይ ለመሆን ነጻነትን እንዳመጣላቸው ያምናሉ። በተጣመመው ወንጌላቸውም ቤተ ክርስቲያንን ለማሸነፍ ይጥሩ ነበር (2ቆሮ 11፥4:20-21)። ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሲታገል የነበረው ከእንዲህ ዐይነት ሰዎችና ከተከታዮቻቸው ጋር ነው።

**1፥17 ክርስቶስ የላከኝ ... እንዳጠምቅ አይደለም፤** ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲናገር ኢየሱስ

እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም፤
የክርስቶስም መስቀል ከንቱ እንዳይሆን፣
በሰዎች የንግግር ጥበብ አልሰብክም።

## ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ

18 የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ ሞኝነት ነው፤
ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል
ነው፤ 19 እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
"የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤
የዐዋቂዎችንም ዕውቀት ከንቱ
አደርጋለሁ።"
20 ጠቢብ የት አለ? ሊቅስ የት አለ?
የዘመኑስ ፈላስፋ የት አለ? እግዚአብሔር
የዓለምን ጥበብ ሞኝነት አላደረገምን?
21 ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሣ ዓለም በገዛ
ጥበቧ እግዚአብሔርን ማወቅ ስላ ተሳናት፣
በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ያድን
ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአል።
22 መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን
ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን
ይሻሉ፤ 23 እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን
እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናክል፣
ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው። 24 እግዚአብሔር
ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪ ኮች፣
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም
ጥበብ ነው። 25 ምክንያቱም ከሰው ጥበብ
ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፤
ከሰውም ብርታት ይልቅ የእግዚአብሔር ድካም
ይበረታል።
26 ወንድሞች ሆይ፤ በተጠራችሁ ጊዜ
ምን እንደ ነበራችሁ እስቲ አስቡ። በሰው
መስፈርት ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ዐዋቂዎች
አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ኀያላን
አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ከትልቅ
ቤተ ሰብ አልተወለዳችሁም። 27 ነገር ግን
እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን
ሞኝ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔር ብርቱዎችን
ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ።
28 እግዚአብሔር የተከበረውን እንደሌለ
ለማድረግ፣ በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና
የተናቀውን ነገር፣ ቢታም ያልተሰጠውን
ነገር መረጠ፤ 29 ይኸውም ማንም ሰው
በእርሱ ፊት እንዳይመካ ነው። 30 በክርስቶስ
ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ
ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣
ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም
ሆኖአል። 31 እንግዲህ፣ እንዲህ ተብሎ እንደ
ተጻፈ ነው፤ "የሚመካ በጌታ ይመካ።"

2 ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ በመጣሁ
ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር* በረቀቀ

1፥18 ቍ 21:23:24:25፤ ሐሥ2፥47፤ ሮሜ1፥16፤ 1ቆሮ2፥14፤ 2ቆሮ2፥15፤ 4፥3፤ 2ተሰ2፥10
1፥19 ኢሳ29፥14
1፥20 ቍ 27፤ ኢዮ12፥17፤ ኢሳ19፥11:12፤ 44፥25፤ ኤር8፥9፤ ሮሜ1፥22፤ 1ቆሮ2፥6:8፤ 3፥18:19፤ 2ቆሮ4፥4፤ ገላ1፥4
1፥21 ቍ 27:28፤ ሮሜ3፥22፤ 11፥14፤ 1ቆሮ6፥2፤ 11፥32
1፥22 ማቴ12፥38፤ ዮሐ2፥11፤ 4፥48
1፥23 ቍ 18፤ ሉቃ2፥34፤ 1ቆሮ2፥2፤ ገላ3፥1
1፥24 ቍ 18:30፤ ሮሜ1፥16፤ 8፥28፤ ቈላ2፥3
1፥25 ቍ 18፤ 2ቆሮ13፥4
1፥26 ቍ 20፤ ሮሜ8፥28
1፥27 ቍ 20፤

1፥27 ሮሜ፥22፤ 1ቆሮ3፥18:19፤ ያዕ2፥5
1፥28 ሮሜ4፥17 1፥29 ኤፌ2፥9 1፥30 ኤር23፥5:6፤ 33፥16፤ ሮሜ3፥24፤ 16፥3፤ 1ቆሮ1፥2፤ 2ቆሮ5፥21፤ ፊል3፥9 1፥31 መዝ34፥2፤ 44፥8፤ ኤር9፥23:24፤ 2ቆሮ10፥17 2፥1 ቍ 4:13፤ 1ቆሮ1፥17

*2፥1 *አንዳንድ ቅጆች ስለ እግዚአብሔር ይላሉ*

ስለ ጥምቀት ያስተማረውን ትምህርት (ማቴ 28፥19) ማጣጣሉ አይደለም:: ነገር ግን ክርስቶስና (ዮሐ 4፥1-2) ጴጥሮስ (ሐሥ 10፥47-48) እንዳደረጉት ጳውሎስ የጥ ምቀትን ሥርዐት ማካሄድ ለረዳቶቹ አሳልፎ መስጠቱን በግልጽ መናገሩ ነበር:: ሐዋርያው በእርሱ ትምህርት የተለወጡት ሰዎች "በጳውሎስ ስም" እንደተጠመቁ (ቍ 13) ያስቡ ዘንድ የሚያደርግን አጋጣሚ እንዲያገኙ አልፈለገም:: ጳውሎስ ራሱ ትኩረት ያደረገው ወንጌልን በመስበክ ላይ ነበር:

**1፥18 የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤** የመስቀሉ መልእክት የሚያካትተው ጥበብንና እውነትን ብቻ ሳይሆን ለማዳን፣ ለመፈወስ፣ አጋንንትን ለማስወጣትና ከኀጢአት ኀይል ነጻ ለማውጣት እየሠራ ያለውንና ከላይ የሚመጣውን እግዚአብሔርን ኀይል ይጨምራል (በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**1፥20 የዓለምን ጥበብ፤** የዓለም ጥበብ በሰው ብቃት ላይ የሚያተኩር፣ ለሰው ሥልጣን ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን መገለጥ የማይቀበልና ከሁነቶች ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያስወግድ ጥበብ ነው:: (1) በዚህ ጥበብ ሰዎች ወደ እውነት ሊደርሱ ወይም ፈጣሪያቸውን ሊያውቁ ስላልቻሉ (ቍ 21)፣ እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን ጥበብ ሞኝነት ይለዋል (3፥19-20):: (2) አማኙ የሰውን ጥበብም ሆነ ዓለማዊ አመለካከት እግዚአብሔር እንደሚንቀው ሊንቀው ይገባል (ቍ 18-31፤ 2፥1-16፤ ሐሥ 17፥18፤ ሮሜ 1፥20-32፤ ቈላ 2፥8 እና ማብ፤ 2ተሰ 2፥10-12፤ 2ጢሞ 3፥1-9፤ 2ጴጥ 2፥1-3፥7፤ ይሁ 1፥4-19):: ወንጌሉና የመስቀሉ መልእክት ከፍልስፍና፣ ከሳይንስ ወይም ከማንኛውም የሰው ጥበብ ከተባለ ነገር ጋር አብረው ሊሄዱ አይችሉም (2፥4-5፤ ገላ 6፥14)::

**1፥21 በስብከት ሞኝነት፤** በዚህ ስፍራ ሞኝነት የተባለው የስብከቱ ዘዴ አይደለም፤ ነገር ግን የተሰቀለውንና ከሙታን የተነሣውን የክርስቶስን ጌትነት የሚሰብከው መልእክት ነው::

**1፥27 እግዚአብሔር ... ሞኝ ነገር መረጠ፤** በቍ 25-29 የእግዚአብሔር የጽድቅ መንገድ መስፈርቶችና ፋይዳዎች ዓለም ከምትቀበላቸው መንገዶች የተለዩ መሆናቸውን በማመልከት ጳውሎስ በአጽንዖት ተናግሮአል፤ እግዚአብሔር አሁን የተሳሳተውን የዓለምን የሕይወት መስፈርትና ጥበብ በማፍረስ ሂደት ላይ ነው::

**1፥28 የተከበረውን እንደሌለ ለማድረግ፤** በኢየሱስ ስቅለትና ትንሣኤ (ቍ 18:23) እንዲሁም የዓለምን ሞኝ ነገር በመምረጥ (ቍ 26-27) እግዚአብሔር በዚህ ዓለም የተከበረውን ነገር ከንቱ አደረገ:: እግዚአብሔር አሁን የሰውን ፍልስፍና፣ የሥነ ልቡና ዕውቀትንና ሌላውንም የዓለም ሥርዐት ሁሉ እንዲያበቃ ለማድረግ በሂደት ላይ ይገኛል::

**1፥30 በክርስቶስ ኢየሱስ ... ጥበባችን፤** አማኝ በክርስቶስ አማካይነት፣ በክርስቶስ በመኖርና ከክርስቶስ ጋር በመሆን የእግዚአብሔርን ጥበብ ይቀበላል እንዲሁም ጽድቅን (ከሮሜ 4 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በቅድስና ይኖራል (2ተሰ 2፥13-15)፤ ቤዛነትንም (ሮሜ 3፥24፤ ኤፌ 4፥30) ያገኛል:: ከክርስቶስ ጋር እስከተጣበቅን ድረስ ክርስቶስ ራሱ የእነዚህ በረከቶች ምንጭ ይሆንልናል (ዮሐ 15፥1-6 እና በክርስቶስ ስለመኖር የተጠቀሰውን ማብ ይመ)::

**2፥1 በላቀ ጥበብ ... አልመጣሁም፤** የሐዋርያው ጳውሎስ የስብከት ይዘት በዓለም ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አዲሱን የሰው "ጥበብ" የተመረከዘ አልነበረም:: ነገር ግን ትኩረት ያደረገው በወንጌል ማዕከላዊ እውነት ማለትም ቤዛነትን በክርስቶስ በኩል ማግኘትና የመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሚሠራው ሥራ ላይ

የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ
ልገልጥላችሁ አልመጣሁም። 2በመካከላችሁ
ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም
የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ
እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና። 3ወደ እናንተ
የመጣሁት በድካምና በፍርሀት፣ እንዲሁም
በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር። 4ቃሌም ስብከቴም
የመንፈስን ኀይል በመግለጥ እንጂ፣
በሚያባባል የጥበብ ቃል አልነበረም፤
5ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኀይል
እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት
ነው።

## ከመንፈስ የተገኘ ጥበብ

6በበሰሉ ሰዎች መካከል ግን ጥበብን
እን ናገራለን፤ ይሁን እንጂ የዚችን ዓለም
ጥበብ ወይም የሚጠፉትን የዚችን ዓለም
ገገሮች ጥበብ አይደለም። 7ነገር ግን ተሰውሮ
የነበ ረውን የእግዚአብሔርን ምስጢር ጥበብ
ነው፤ ይህም ጥበብ እግዚአብሔር ከዘመናት
በፊት ለክብራችን አስቀድሞ የወሰነው ነው።
8ከዚህ ዓለም ገገሮች አንዳቸውም ይህን
ጥበብ አልተረዱትም፤ ቢረዱትማ ኖሮ
የክ ብርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር። 9ይሁን
እንጂ፣ እንደ ተጻፈው፣
"ዐይን ያላየውን፣
ጆሮ ያልሰማውን፣
የሰውም ልብ ያላሰበውን፣
እግዚአብሔር ለሚወዱት
አዘጋጅቶአል፤"
10እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ
አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል።
መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ
ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል። 11በውስጡ
ካለው ከራሱ መንፈስ በስተቀር ከሰው
መካከል የአንድን ሰው ሐሳብ የሚያውቅ
ማን አለ? እንደዚሁም ከእግዚአብሔር
መንፈስ በስተቀር፣ የእግዚአብሔርን ሐሳብ
የሚያውቅ ማንም የለም። 12ከእግዚአብሔር
የሆነውን መንፈስ እንጂ፣ የዓለምን መንፈስ
አልተቀበልንምና፤ ይህም እግዚአብሔር
በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው። 13እኛ
የምንናገረው ይህን ነው፤ ከሰው ጥበብ
በተማር ነው ቃል ሳይሆን፣ ከመንፈስ
በተማር ነው ቃል እንናገራለን፤ መንፈሳዊ

2፥2 1ቆሮ1፥23፤ ገላ6፥14
2፥3 ሐሥ18፥1-18፤ 1ቆሮ4፥10፤ 9፥22፤ 2ቆሮ7፥15፤ 11፥29:30፤ 12፥5:9:10፤ 13፥9
2፥4 ቊ 1፤ ሮሜ15፥13
2፥5 2ቆሮ4፥7፤ 6፥7
2፥6 ቊ 8፤ መዝ146፥4፤ 1ቆሮ1፥20፤ ኤፌ4፥13፤ ፊል3፥15፤ ቈላ4፥12፤ ዕብ5፥14፤ 6፥1፤ ያዕ1፥4
2፥7 ቊ 1፤ ሮሜ16፥25
2፥8 ቊ 6፤ መዝ24፥7፤ ሐሥ7፥2፤ 1ቆሮ1፥20፤ ያዕ2፥1
2፥9 ኢሳ64፥4፤ 65፥17
2፥10 ማቴ13፥11፤ ዮሐ14፥26፤

2፥10 2ቆሮ12፥1:7፤ ገላ1፥12፤ 2፥2፤ ኤፌ3፥3:5 2፥11 ምሳ20፥27፤ ኤር17፥9 2፥12 ሮሜ8፥15፤ 1ቆሮ1፥20:27፤ ያዕ2፥5 2፥13 ቊ 1:4፤ 1ቆሮ1፥17

---

ነበር (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)። እርሱም ሰብዓዊ ውስንነቱን፣ ብቁ አለመሆኑን፣ የውስጥ ፍርሃቱንና ድንጋጤውን ያውቅ ነበር። ስለዚህ የሚተማመነው በራሱ ሳይሆን፣ በመልእክቱና በመንፈስ ቅዱስ ነበር (ቊ 4)። ይህም የመንፈስ ቅዱስን ሥራና ኀይል በእጅጉ እንዲገለጥ አድርጎአል።

**2፥4 የመንፈስን ኀይል በመግለጥ፤** የመንፈስ ቅዱስን ኀይል በሚገልጥበት ጊዜ (1፥18:24) የጳውሎስ ስብከት የሚከተሉትን የሚያካትት ነው፤ (ሀ) ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን መውቀሱ እንዲሁም ከሙታን የተነሣውን የክርስቶስ የማዳን ኀይል መመስከሩ (ከምዕ 5—6 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዮሐ 16፥8 እና ማብ፤ ሐሥ 2፥36-41 ይመ)፣ (ለ) የሰዎችን ሕይወት የሚለውጥ ኀይል መሆኑ (1፥26-27 ይመ፤ ከሐሥ 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (ሐ) በአማኝ ሕይወት ውስጥ ቅድስናን የሚያመጣ ኀይል መፍሰሱ (5፥3-5) እና (መ) የእግዚአብሔር ኀይል በምልክቶችና በድንቆች መገለጡ (ሐሥ 2፥29-33፤ 4፥29-30፤ 5፥12፤ 14፥3፤ 2ቆሮ 12፥12)።

(2) ሌሎች አያሌ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የወንጌል ስብከት ልዩ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ጋር እንደተገለጠ በአጽንዖት ያመለክታሉ ማር 16፥17-18፤ ሉቃ 10፥19፤ ሐሥ 28፥3-6፤ ሮሜ 15፥19፤ 1ቆሮ 4፥20፤ 1ተሰ 1፥5፤ ዕብ 2፥4።

(3) የወንጌል አገልጋዮች ሁሉ በአገልግሎታቸው የሚከተሉት እንዲሆን መጸለይ አለባቸው፡ (ሀ) ሰዎች እንዲድኑ (ሐሥ 2፥41፤ 11፥21:24፤ 14፥1)፣ (ለ) አዳዲስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ (ሐሥ 2፥4፤ 4፥31፤ 8፥17፤ 19፥6)፣ (ሐ) ክፉ መናፍስት እንዲወጡ (ሐሥ 5፥16፤ 8፥7፤ 16፥18)፣ (መ) በሽተኞች እንዲፈወሱ (ሐሥ 3፥6፤ 4፥29-30፤ 14፥10) እና (ሠ) ደቀ መዛሙርት የክርስቶስን ጻድቅ መስፈርቶችና ትምህርቶች እንዲማሩ (ማቴ 28፥18-21፤ ሐሥ 11፥23:26 እንዲሁም በገጽ 1527 ላይ፣ "*አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ ቊ 42)።

**2፥12 እናውቅ ዘንድ፤** እግዚአብሔር ለሚወዱት ሁሉ ያዘጋጀላቸው (ቊ 9) በመንፈስ ቅዱስ መገለጥና አብርሆት አማካይነት በአማኞች ይታወቃል (ቊ 10-16)። እነርሱም መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበትና በሚያጠኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ያውቁ ዘንድ ያበራላቸዋል። ከዚህም በላይ መንፈስ ቅዱስ ታማኝ ለሆኑ አማኞች ቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ መሠረት እንዳላቸው በሚገባ ያረጋግጥላቸዋል (ዮሐ 16፥13፤ ኤፌ 1፥17)።

**2፥13 ከመንፈስ በተማርነው ቃል፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ስብከቱ መለኮታዊ መሠረት እንዳለው ቢጽፍም፣ ከቊ 9-13 ያለው ክፍል ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጻፍ ረገድ መንፈስ ቅዱስ ደረጃ በደረጃ የገለጠውን ያመለክታል፤

ደረጃ 1 - እግዚአብሔር ጥበቡን ለሰው ልጅ ማስተላለፍ ፈለገ (ቊ 7-9)፤ ይህ ጥበብ ድነታችንን የሚመለከት ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነውን ክርስቶስን ማእከል ያደረገ ነው (ከ1፥30፤ 2፥2:5 ጋር ያነጻጽሩ)።

ደረጃ 2 - የእግዚአብሔር እውነትና ጥበብ ለሰው የተገለጠው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው (ቊ 10)። የእግዚአብሔርን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ ነው (ቊ 11)።

ደረጃ 3 - የእግዚአብሔር መገለጥ ለተመረጡት አማኞች የሚሰጠው በውስጣቸው ባደረው በመንፈስ ቅዱስ ሀልዎት ነው (ቊ 12 ይመ፤ ከሮሜ 8፥11:15 ጋር ያነጻጽሩ)።

ደረጃ 4 - የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች የጻፉት ከመንፈስ ቅዱስ የተማሩትን ቃል ነው (ቊ 13)፤ እነዚህን መጻሕፍት በሚጽፉበት ጊዜ ምርጥ ቃላት እንዲጠቀሙ የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ከዘፀ 24፥4፤ ከኢሳ 51፥16፤ ከኤር 1፥9፤ 36፥28:32፤ ከሕዝ 2፥7፤ ከማቴ 4፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። በተመሳሳይ ሁኔታም መለኮታዊ የሆነውን እውነት ከመግለጽ አኳያ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሰውን ተሳትፎ የሚያስቀር አይደለም፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የእያንዳንዱን ሰው የቃላት ችሎታና የግል ብልሃት ይጠቀማል።

እውነት ንም የምንገልጸው በመንፈሳዊ ቃል
ነው።[ም] 14መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር
መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤
ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ
ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር
ስለሆነ፣ ሊረዳው አይችልም። 15መንፈሳዊ
ሰው ግን ሁሉንም ነገር ይመረምራል፤ ራሱ
ግን በማንም አይመረመርም።

16"ያስተምረው ዘንድ፣
የጌታን ልብ ማን ዐወቀው?"
እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።

*2ቆሮ 6፥14–7፥1*

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሠተ መለያየት

3 ወንድሞች ሆይ፤ በክርስቶስ ገና ሕፃናት
እንደ መሆናችሁ፣ እንደ ሥጋውያን
እንጂ እንደ መንፈሳውያን ልናገራችሁ
አልቻልሁም። 2ገና ስላልጠነከራችሁ ወተት
እንጂ ጠንካራ ምግብ አልመገብኋችሁም፤
አሁንም ቢሆን ገና ናችሁ። 3አሁንም
ሥጋውያን ናችሁ፤ በመካከላችሁ
ቅናትና ክርክር አለ፤ ታዲያ፣ ሥጋውያን
መሆናችሁ አይደለምን? ተግባራችሁስ
እንደ ማንኛውም ሰው ተግባር መሆኑ
አይደለምን? 4ምክንያቱም አንዱ፣ "እኔ
የጳውሎስ ነኝ"፣ ሌላው ደግሞ፣ "እኔ
የአጵሎስ ነኝ" ቢል፣ ሰብአዊ ፍጡር ብቻ
መሆናችሁ አይደለምን?

5ለመሆኑ አጵሎስ ምንድን ነው? ጳውሎ
ስስ ምንድን ነው? ጌታ ለእያንዳንዳቸው
በሰጣቸው መጠን የሚሠሩ አገልጋዮች
ናቸው፤ እናንተም ወደ እምነት የመጣችሁት
በእነ ርሱ አማካይነት ነው። 6እኔ ተከልሁ፤
አጵ ሎስ ውሃ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን
እግዚአብሔር ነው። 7ስለዚህ የሚያሳድግ
እግዚአብሔር እንጂ፣ የሚተክልም ሆነ ውሃ
የሚያጠጣ ምንም አይደለም። 8የሚተክልም
ሆነ የሚያጠጣ አንድ ናቸው፤ እያንዳንዱም
እንደ ሥራው መጠን የራሱን ሽልማት
ይቀበ ላል። 9እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን
የም ንሠራ ነንና፤ እናንተም የእግዚአብሔር
ዕርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንጻ ናችሁ።

2፥14 ዮሐ14፥17፤ 1ቆሮ1፥18
2፥15 1ቆሮ3፥1፤ ገላ6፥1
2፥16 ኢሳ40፥13፤ ዮሐ15፥15፤ ሮሜ11፥34
3፥1 ሮሜ7፥14፤ 1ቆሮ2፥14፡15፤ 14፥20
3፥2 ዮሐ16፥12፤ ዕብ5፥12-14፤ 1ጴጥ2፥2
3፥3 ሮሜ13፥13፤ 1ቆሮ1፥11፤ ገላ5፥20
3፥4 1ቆሮ1፥12
3፥5 ሐሥ18፥24፤ 1ቆሮ4፥1፤ 2ቆሮ6፥4፤ ኤፌ3፥7፤ ቈላ1፥23፡25
3፥6 ሐሥ18፥4-11፤ 1ቆሮ4፥15፤ 9፥1፤ 15፥1
3፥8 ቍ14፤ መዝ18፥20፤ 62፥12፤ ማቴ25፥21፤
3፥8 1ቆሮ9፥17 3፥9 ኢሳ61፥3፤ ማር16፥20፤ 2ቆሮ6፥1፤ ኤፌ2፥20-22፤ 1ተሰ3፥2፤ 1ጴጥ2፥5

[ም]*2፥13 ወይም መንፈሳዊ እውነትንም ለመንፈሳዊ ሰው እንገልጻለን*

---

ደረጃ 5 - በመለኮታዊ ኀይል የተዘጋጀ ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈሳዊ አማኞች ሊታወቅ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት የመጽሐፉን ይዘት ሲመረምሩ ነው (ቍ 14-16)::

ስለዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ሐሳብም ሆነ ቋንቋ ሁለቱም በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተገኙ ናቸው:: የትኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሓፊ ሐሰተኛ ቃል ወይም ሐረግ አልተናገረም:: የእግዚአብሔር ቃል ከሕጸጽና ከሐሰት የተጠበቀውም በመንፈስ ቅዱስ ነው (በገጽ 1080 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር ቃል"* በሚልና በገጽ 1941 ላይ፣ *"መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)::

2፥14 **መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው፤** የዚህን ጥቅስ ዝርዝር ሐሳብ ለመረዳት በገጽ 1782 ላይ፣ *"ሦስት ዐይነት ሰዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

2፥16 **የክርስቶስ ልብ አለን፤** የክርስቶስ ልብ አለን ማለት የእርሱን ፈቃድ፣ የቤዛነት ዕቅዱንና ዐላማውን ማወቅ ማለት ነው (ቍ 9-10):: ይኸውም እግዚአብሔር ለነገሮች ግምት እንደሚሰጥና እንደሚመለከታቸው ማየትን፣ ዋጋ የሚሰጣቸውን ዋጋ መስጠትን፣ የሚወዳቸውን መውደድና የሚጠላቸውን መጥላት ማለት ነው (ቍ 15፤ ዕብ 1፥9):: የእግዚአብሔርን ቅድስናና የኀጢአትን አስጸያፊነት ማወቅ ማለትም ነው:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን መቀበልና መንፈስ ቅዱስን መከተል (ቍ 12) የአማኙን አስተሳሰብና እርሱም ዓለምን የሚያይበት አመለካከት ከዘመኑ መንገድና ጥበብ ፈጽሞ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል (ከፊል 2፥5-8 ጋር ያነጻጽሩ)::

3፥1 **እንደ መንፈሳውያን ልናገራችሁ አልቻልሁም፤** የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ችግር ከሆኑት አንዱ፣ ቤተ ክርስቲያኗ ራሷን ከዓለም የክፋት መንገድ ለመለየት ሳትፈቅድ የእግዚአብሔር በረከት በእርሷ እንዲገለጥ ጥረት ማድረጓ ነው (በገጽ 2022 ላይ፣ *"ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: (1) የቆሮንቶስ ቤ ተ ክርስቲያን እረኞችና መሪዎች፣ የክፋት ድርጊታቸውን ሳይተዉ አማኞች ነን የሚሉትን ወደ ጉባኤያቸው እንዲቀላቀሉ ይፈቅዱ ነበር:: የቆሮንቶስ ምእመናን የሚከተሉት ሁኔታዎች በኅብረታቸው ውስጥ እያሉ በቸልታ ያልፉ ነበር፤ በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ መለያየት (11፥18)፣ የዓለም ፍልስፍና (1፥18-25፤ 3፥19)፣ ቅናትና ክርክር (3፥3)፣ ትምክህት (3፥21፤ 4፥7)፣ ኢግብረገባዊነት (5፥1)፣ በሚረባውና በማይረባው ነገር በፍርድ ፊት መካሰስ (6፥1-8)፣ በጣዖት አምልኮ ግብዣዎች መሳተፍ (ምዕ 8፤ 10)፣ የሐዋርያትን ትምህርት መቃወም (14፥36-37):: የቆሮንቶስ ምእመናን ሐዋርያት ያስተማሩትን እውነት፣ ፍቅርና የጽድቅ ሕይወት መለኪያ (6፥9-10፡13) ፍጹም አስፈላጊነት ማየት ለላቃታቸው፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችንና (ምዕ 12፤ 14) የጌታን እራት (11፥20-34) አረከሱ፤ እንዲሁም የወንጌልን እውነት አጣመሙ (1፥18-31)::

(2) በኅብረትዋ ውስጥ የዓለምን የረከሰ ልምምድ የምትፈቅድ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ሲጣመም ቸል የምትል ማንኛዋም ቤተ ክርስቲያን (ራእ 2፥20 እና ማብ ይመ) በእርሱ እንደምትናቅና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥም ሊኖራት የሚገባትን ስፍራ እንደምታጣ (ከራእ 2፥5፡16፤ 3፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በማስጠንቀቂያ ተናግሮአል:: እንዲህ ዐይነትዋ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም እንድትለይና (2ቆሮ 6፥16-18) እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናዋን ፍጹም እንድታደርግ (2ቆሮ 7፥1) እንዲሁም በእውነተኛ ንስሓ ኀጢአቷን እንድትናዘዝ (5፥2) መንፈስ ቅዱስ ጥሪ ያቀርብላታል::

3፥3 **አሁንም ሥጋውያን ናችሁ፤** በዓለማዊና በመንፈሳዊ ክርስቲያኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት በገጽ 1782 ላይ፣ *"ሦስት ዐይነት ሰዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

# ሦስት ዐይነት ሰዎች

*1ቆሮ 2፥14-15 "መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ፣ ሊረዳው አይችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉንም ነገር ይመረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም።"*

---

**መሠረታዊ አከፋፈል፤** መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን ሁሉ በአጠቃላይ በሁለት ይከፍላል።

(1) *ተፈጥሮአዊ ወይም መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው* (ግሪክ፡ "ሱኪኮስ"፣ 1ቆሮ 2፥14) ዳግም ልደት ያላገኘን ሰው ያመለክታል፤ ይኸውም በተፈጥሮአዊ ስሜት ብቻ የሚመራ ማለት ነው (2ጴጥ 2፥12)። በእንዲህ ዐይነቱ ሰው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የለም (ሮሜ 8፥9)፤ እርሱም በሰይጣን ቍጥጥር ሥር (ሐሥ 26፥18) ስለሆነ፣ ለሥጋውና ለስሜቱ ባሪያ ነው (ኤፌ 2፥3)። እርሱ ከዓለም ስለሆነ፣ የዓለም ወዳጅ ነው (ያዕ 4፥4)፤ ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስን የጽድቅ መንገድ ይቃወማል (1ቆሮ 2፥14)። መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው እግዚአብሔርንና መንገዱን ሊረዳ አይችልም፤ ነገር ግን በሰብአዊ አስተሳሰብ ወይም ስሜት ይመራል።

(2) *መንፈሳዊ ሰው* (ግሪክ፡ "ኑማቲኮስ"፤ 1ቆሮ 2፥15፣ 3፥1) ዳግም ልደት ያገኘን ሰው ያመለክታል፤ ይኸውም መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ማለት ነው። ይህ ሰው አስተሳሰቡ መንፈሳዊ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር የሚያስበውን ነገር ያስባል (1ቆሮ 2፥11-13)፤ በእግዚአብሔርም መንፈስ ይኖራል (ሮሜ 8፥4-17፤ ገላ 5፥16-26)። እንዲህ ዐይነቱ ግለሰብ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናል፤ በውስጡ ያደረውን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመከተል ይጥራል፤ ለሥጋ ስሜትና ለኀጢአት ተገዥ መሆንን ይቃወማል (ሮሜ 8፥13-14)።

አንድ ሰው መንፈሳዊ ሰው ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተሰጠውን ድነት በእምነት ሲቀበል ዳግም ልደትን ያገኛል፤ መንፈስ ቅዱስም መለኮታዊ ሕይወትን በግለሰቡ ሕይወት በማስቀመጥ አዲስ ተፈጥሮን ያስተላልፍለታል (2ጴጥ 1፥4 ይመ እንዲሁም (በገጽ 1646 ላይ፣ "የዶቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን መቀበል" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህ ሰው ዳግም የተወለደ (ዮሐ 3፥3፡5፡7)፣ የታደሰ (ሮሜ 12፥2)፣ አዲስ ፍጥረት የሆነ (2ቆሮ 5፥17) እንዲሁም በክርስቶስ ባለ እምነት (ፊል 3፥9) የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚቀበል ነው።

**በክርስቲያኖች ሕይወት የሚታይ ሌላው ልዩነት፤** ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አዲስ ሕይወት ቢቀበሉም ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ከክፉ ዝንባሌው ጋር በውስጣቸው ሊኖር ይችላል (ገላ 5፥16-21)። በውስጣቸው ያለውን ኀጢአተኛ ተፈጥሮ መልካም እንዲሆን ማድረግ አይቻልም፤ ሊገደል እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ጸጋ ሊሸነፍ ይገባል (ሮሜ 8፥13)። ይህንን ተፈጥሮ አማኞች ሊያሸንፉ የሚችሉት ራሳቸውን ዕለት ዕለት በመካድ (ማቴ 16፥24፤ ሮሜ 8፥12-13፤ ቲቶ 2፥12)፣ ሸክምን ሁሉ ወይም ኀጢአትን በማስወገድ (ዕብ 12፥1) እንዲሁም ወደ ኀጢአት የሚመራቸውን ፈተና ሁሉ በመቋቋም ነው (ሮሜ 13፥14፤ ገላ 5፥16፤ 1ጴጥ 2፥11)። በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አማኞች ራሳቸው በኀጢአተኛ ተፈጥሮ ላይ ጠርነትን ያውጃሉ (ሮሜ 8፥13-14፣ ገላ 5፥16-18)፤ ሥጋንና ክፉ መሻቱን ይሰቅሉታል (ገላ 5፥24) እንዲሁም ዕለት ዕለት ይገድሉታል (ቈላ 3፥5)። ራስን በመካድና ለመንፈስ ቅዱስ የመቀደስ ሥራ ራስን በመስጠት ሂደት፣ ለኀጢአተኛ ተፈጥሮአቸው ባሪያ ከመሆን ነጻ ወጥተው መንፈሳዊ ክርስቲያን በመሆን ይኖራሉ (ሮሜ 6፥13፤ ገላ 5፥16)።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህንን ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ ለማሸነፍ ተገቢውን ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍላቸው አንዳንዶች እንደ ዓለማዊ ወይም መንፈሳዊ እንዳልሆነ ሰው (ግሪክ፡ "ሳርኪኮስ") በመጥፎ ባሕርይ እየተመላለሱ መሆናቸውን አመልክቶአቸዋል፤ የራሳቸውን የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ዝንባሌ ባለማቋረጥ ሙሉ በሙሉ ከመቃወም ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ ለአንዳንዶቹ ስሜቶቻቸው ተገዥ ሲሆኑ ይታያሉ። በዐመፃቸው ጸንተው ባይኖሩም፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን ሆነው መቈየትን እየፈለጉ በአንዳንድ የሕይወታቸው ክፍል ከዓለም፣ ከኀጢአተኛ ተፈጥሮና ከዲያብሎስ ጋር በመተባበር ሂደት ውስጥ ይገኛሉ (10፥21፤ 2ቆሮ 6፥14-18፤ 11፥3፤ 13፥5)።

(1) *የሥጋዊ ክርስቲያኖች ሁኔታ፤* ኀጢአትንና ዐመፅን ማድረግ የሕይወታቸው መርሕ ባይሆንም ወይም ከእግዚአብሔር መንግሥት በሚለያቸው አስከፊ ኢግብረገባዊነትና ርኵሰት

ውስጥ ገብተው ባይገኙም (1ቆሮ 6፥9-11 *ይመ*፣ ከገላ 5፥21፣ ከኤፌ 5፥5 *ጋር ያነጻጽሩ*)፣ እነዚህ *ሥጋዊ* ክርስቲያኖች በክርስቶስ የተገኘው ድነት የሚጠይቀውን ነገር ገና እንዳልተረዱ እንደ አዲስ አማኞች ባለ ባሕርይ በመመላለስ ከእንግዲህ በጸጋ ሊያድጉ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ገብተው ነበር (1ቆሮ 3፥1-2)። *ሥጋዊነታቸው* በሚያደርጉት ቅናትና ክርክር ተገልጸአል (3፥3)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ኢግብረገባዊነት በግዴለሽነት ወይም በቸልታ የሚያልፉ ነበሩ (5፥1-13፣ 6፥13-20)። የእግዚአብሔርን ቃል ወይም የእግዚአብሔርን ሐዋርያ በብርቱ አልፈለጉም (4፥18-19)። ከባድ ችግር ቢያጋጥማቸውም እንኳ ራሳቸው መፍትሔ ሊፈልጉ ሲገባ በማይረባ ነገር እርስ በርሳቸው ተካስሰው ወደ ፍርድ ቤት ይሄዱ ነበር (6፥6)። ኢግብረገባዊ ወሲብ የፈጸሙት ወይም በሌሎች ከባድ ኀጢአቶች ውስጥ የገቡትን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ከተገኘው ድነት ሙሉ በሙሉ መውጣት እንደሚገባቸው የሚያስብ መሆኑን ልብ ይበሉ (1ቆሮ 5፥1፡9-11፣ 6፥9-10)።

(2) *በሥጋዊ ክርስቲያኖች ላይ ያለው አደገኛ ሁኔታ*፣ እነዚህ *ሥጋዊ* የሆኑ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ሊሰጡት ከሚገባቸው አክብሮት ፈቀቅ በማለትና (2ቆሮ 11፥3) ዓለምን በይበልጥ በመምሰል አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ይገኙ ነበር (2ቆሮ 6፥14-18)። በዚህም ምክንያት ጌታ ይቀጣቸዋል፤ ይፈርድባቸዋልም፤ ዓለምን በመምሰል ቢቀጥሉ፣ በመጨረሻ ከእግዚአብሔር *መንግሥት ይወገዳሉ* (1ቆሮ 6፥9-10፣ 11፥31-32)። *ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚወስድ ግልጽ* የሆነ ኀጢአትን በመሥራት አንዳንዶቹ በትክክል *መንፈሳዊ ሞትን ሞተዋል* (1ዮሐ 3፥15 *ማ*፣ 5፥17 *ማብ ይመ*፣ ከሮሜ 8፥13፣ ከ1ቆሮ 5፥5፣ ከ2ቆሮ 12፥21፣ 13፥5 *ጋር ያነጻጽሩ*)።

(3) *ለሥጋዊ ክርስቲያኖች የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች*፤ (ሀ) *ሥጋዊ* ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ከማያስደስቱ ነገሮች ራሳቸውን ለማንጻት ፈቃደኛ ካልሆኑ በእምነት ከሚገኘው የሕይወት መንገድ የመውጣት አደጋ ውስጥ እንዳሉ ማወቅ አለባቸው (ሮሜ 6፥14-16፣ 1ቆሮ 6፥9-10፣ 2ቆሮ 11፥3፣ ገላ 6፥7-9፣ *ያዕ* 1፥12-16)፤ (ለ) በኀጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ካጠፋቸው ከእስራኤላውያን አሳዛኝ ምሳሌነት ትምህርት መውሰድ ይገባቸዋል (1ቆሮ 10፥5-12)፤ (ሐ) በአንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ነገርና የሰይጣንን ነገር ማድረግ እንደማይቻል መረዳት አለባቸው (*ማቴ* 6፥24፣ 1ቆሮ 10፥21)፤ (*መ*) ከዓለም ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን መለየት (2ቆሮ 6፥14-18) እንዲሁም እግዚአብሔርን በመፍራት ቅድስናቸውን ፍጹም ለማድረግ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳቸውን ማንጻት አለባቸው (2ቆሮ 7፥1)።

[10]ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ መጠን፣
እንደ አንድ ብልኅ ግንበኛ መሠረትን
ጣልሁ፤ ሌላውም በላዩ ላይ ይገነባል፤
ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ
መጠንቀቅ አለበት። [11]ምክንያቱም አንድ
ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ሌላ
መሠ ረት መጣል የሚችል ማንም የለም፤
ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
[12]ማንም በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ወይም
በብር፣ በከበረ ድንጋይ ወይም በዕንጨት፣
በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፤ [13]ሥራው
እንዴት እንደ ሆነ ይታያል፤ ምክንያቱም
ያ ቀን ወደ ብርሃን ያመጣዋል። በእሳት
ስለሚገለጥ እሳቱ የእያንዳንዱን ሰው ሥራ
ምንነት ይፈትናል። [14]ማንም የገነባው ሥራ
ቢጸናለት ሽልማ ቱን ይቀበላል፤ [15]ሥራው
የተቃጠለበት ግን ሽልማት ይቀርበታል፤
እርሱ ራሱ ግን ይድናል፤ ይሁን እንጂ
የሚድነው በእሳት ውስጥ በጭንቅ
እንደሚያልፍ ሆኖ ነው።
[16]እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም
መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር
አታውቁምን? [17]ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን
ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ
ነውና፤ ያም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ።
[18]ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ
ማንም በዚህ ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው፣
ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ራሱን እንደ ሞኝ
ይቍጠር። [19]የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር
ፊት ሞኝነት ነውና፤ እንዲህ ተብሎ
ተጽፎአልና፤ "እርሱ ጥበበኞችን በራሳቸው
ተንኰል ይይ ዛቸዋል፤" [20]በሌላ ስፍራ
ደግሞ፣ "ጌታ የጥ በበኞች ሐሳብ ከንቱ
መሆኑን ያውቃል" ተብሎ ተጽፎአል፤
[21]እንግዲህ ማንም በሰው አይመካ። ሁሉ

3፥10 ሮሜ12፥3፤ 15፥20፤ ኤፌ2፥20
3፥11 ኢሳ28፥16፤ ኤፌ2፥20
3፥13 ዘኍ31፥22፡23፤ ኤር23፥28፥29፤ ሚል3፥3፤ 1ቆሮ1፥8፤ 4፥5፤ 2ተሰ1፥7-10፤ 2ጢሞ1፥12፡18፤ 4፥8
3፥14 ቊ8
3፥15 ይሁ1፥23
3፥16 ሮሜ8፥9፤ 1ቆሮ6፥19፤ 2ቆሮ6፥16፤ ኤፌ2፥21፡22፤ ዕብ3፥6
3፥18 ኢሳ5፥21፤ 1ቆሮ1፥20፤ 8፥2፤ ገላ6፥3
3፥19 ቊ18፤ ኢዮ5፥13፤ ሮሜ1፥22፤ 1ቆሮ1፥20፡27
3፥20 መዝ94፥11
3፥21 ሮሜ8፥32፤ 1ቆሮ4፥6

**3፥15 ሽልማት ይቀርበታል፤** ቤዛነትን ያገኙ ሁሉ ከኵነኔ ፍርድ እግዚአብሔር ነጻ እንደሚያደርጋቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል (ዮሐ 5፥24፤ ሮሜ 8፥1፤ ዕብ 10፥14-17)፤ ይሁን እንጂ አማኞች (1ዮሐ 4፥17) በዚህ ምድር በሚኖሩበት ጊዜ ለእግዚአብሔርና ለተሰጣቸው ጸጋ ያላቸውን ታማኝነት በተመለከተ ወደፊት በፍርድ ፊት ይቀርባሉ (ቊ 10፤ 4፥2-5፤ 2ቆሮ 5፥10)። በዚያ ፍርድ አንድ አማኝ ድነትን ቢቀበልም እንኳ ታላቅ ጉዳት ሊደርስበት ይችላል (ግሪክ፡ «ዘሚዩ» - ሽልማት ማጣት ወይም መጐዳት ማለት ነው)።

ግዴለሽ የሆነው አማኝ በሚከተሉት መንገዶች ሽልማትን ሊያጣ ወይም ሊጐዳ ይችላል፤ (1) በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የማፈር ስሜት (2ጢሞ 2፥15፤ 1ዮሐ 2፥28)፣ (2) በሕይወት ዘመን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሠራን የሥራ ዋጋ ማጣት (ቊ 12-15)፣ (3) በእግዚአብሔር ፊት ክብርና ዝናን ማጣት (ከሮሜ 2፥7 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (4) የአገልግሎት ዕድልንና በመንግሥተ ሰማይ ያለንን ሥልጣን ማጣት (ማቴ 25፥14-30)፣ (5) በመንግሥተ ሰማይ ዝቅተኛ ስፍራን መያዝ (ማቴ 5፥19፤ 19፥30)፣ (6) ሽልማትን ማጣት (ከቊ 4-15 ጋር ያነጻጽሩ) እና (7) በሌሎች ላይ ለተፈጸመ በደል ብድራትን መክፈል (ቈላ 3፥24-25)። ታማኝ በመሆንና ለጌታችን ራስን መሥዋዕት አድርጎ በማገልገል ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እነዚህ ምንባቦች ያመለክታሉ (ከሮሜ 12፥1-2፤ ከፊል 2፥12፤ 4፥3 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1822 ላይ፣ «*በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥15 በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ፤** ይህ አባባል «በጭንቅ መዳን» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእያንዳንዱን ሰው በተለይም በዚህ ስፍራ የእያንዳንዱን አገልጋይ የሕይወት፣ የተግባር፣ የትምህርትና የሥራ ጥራት ይመዝናል። ሥራው የማይረባ ሆኖ ከተገኘ፣ ሽልማቱን ያጣል፤ እርሱ ራሱ ግን ሊድን ይችላል። ይህ ክፍል በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውስጥ ያለውንም የንስሐ ቦታ (መካነ ንስሐ) የሚያመለክት እንዳይደለ ልብ ይበሉ፤ ይህ ሐሳብ የሚገልጸው ሰውን ሞት ከሚገባው ኀጢአት ማንጻትን በተመለከተ ሳይሆን፣ ሥራን በሚመለከት ስለሚሰጠው ፍርድ ነው።

**3፥16 እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ፤** በዚህ ስፍራ አጽንዖት የተሰጠው የአማኞች ጉባኤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑን ነው (ከቊ 9፤ ከ2ቆሮ 6፥16፤ ከኤፌ 2፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። በቆሮንቶስ ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ብልሹ በሆነ ኅብረተሰብ መካከል ሲኖሩ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደመሆናቸው መጠን በዚያ ኅብረተሰብ ውስጥ በሚደረጉ ክፉቶች መሳተፍ አይገባቸውም ነበር፤ ነገር ግን ማንኛውንም ዐይነት ኢግብረገባዊነት መቃወም ይጠበቅባቸው ነበር። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ (ከ1ጴጥ 1፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 641 ላይ፣ «*ቤተ መቅደሱ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ መሆን አለበት (ቊ 17)።

**3፥17 እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤** የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የማነጽ ኀላፊነት ላለው ለማንኛውም ሰው ሐዋርያው ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት ጠንካራ ማስጠንቀቂያዎች አንዱን በዚህ ስፍራ ያቀርባል። ይህ ክፍል በማስተማርና በመምራት ኀላፊነት ላይ ላሉ ሁሉ የተለየ ጠቀሜታ አለው። ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ማለትም አጥቢያ ማኅበረ ምእመናን ወይም አያሌ ጉባኤዎችን ቢያረክስ ወይም ቢበክል እግዚአብሔር ራሱ ያንን ሰው በክፉ አደጋና በዘላለም ሞት ይቀጣዋል። ሰዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ሊበክሉና ሊያፈርሱ ይችላሉ፤ (1) ኢግብረገባዊ በሆነ ተግባር ውስጥ በመግባት (5፥1)፣ (2) ሐሰትን፣ ማጭበርበርን በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ የእድገት ምኞትን በማስፋፋት (ቊ 3 ይመ፤ ከሐሥ 5፥1-11 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (3) ሐሰተኛ አስተምህሮን በማበረታታት፣ ሐዋርያዊ መገለጥን በመቃወምና በቅዱሳት መጻሕፍት እውነት ላይ ቸልተኝነትን በማሳየት (1ጢሞ 4፥1፤ ይሁ 1፥4)፣ (4) በጉባኤ ውስጥ የተገለጠን ኀጢአትና ዓለማዊነትን በመቀበል (5፥1-2፡5-7፤ ራእ 3፥17)፣ (5) በዓለማዊ ጥበብ ወይም በተጣመመ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ በመሞከር (1፥18—2፥5፤ ፊል 1፥15-16)።

ነገር የእናንተ ነውና፤ [22]ጳውሎስም ሆነ
አጵሎስ ወይም ኬፋ[a]፣ ዓለምም ሆነ
ሕይወት ወይም ሞት፣ አሁን ያለውም ሆነ
ወደ ፊት የሚመጣው፣ ሁሉ የእናንተ ነው፤
[23]እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፤ ክርስቶስም
የእግዚአብሔር ነው።

## የክርስቶስ ሐዋርያት

**4** እንግዲህ ሰው ሁሉ እኛን እንደ ክርስ
ቶስ አገልጋዮችና እንደ እግዚአብሔር ምስ
ጢር ባለ ዐደራዎች ሊቈጥረን ይገባል፡
፡ [2]ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት
አለባቸው። [3]በእናንተም ሆነ በሰዎች የፍርድ
ሸንጎ ቢፈረድብኝ እኔ በበኩሌ ግድ የለኝም፤
እኔ እንኳ በራሴ ላይ አልፈርድም። [4]ኅሊናዬ
ንጹሕ ነው፤ ይህ ግን ጥፋት አልባ መሆኔን
አያረጋግጥም፤ በእኔ ላይ የሚፈ ርድ ጌታ
ነው። [5]ስለዚህ ጊዜው ሳይደርስ በምንም
ነገር አትፍረዱ፤ ጌታ እስኪመጣ ጠብቁ፡
፡ እርሱ በጨለማ ውስጥ የተሰወረውን ወደ
ብርሃን ያመጣዋል፤ በሰዎች ልብ ውስጥ
ያለውንም ሐሳብ ይገልጠዋል። በዚ ያን
1ቆሮ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው የሚገባውን ምስጋና
15፥23 ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል።

[6]እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ለእናንተ
ጥቅም ብዬ በዚህ ጕዳይ እኔን ራሴንና
አጵሎስን ምሳሌ አድርጌ አቅርቤላችኋለሁ፤
ይህ ንም ያደረግሁት፣ "ከተጻፈው አትለፍ"
የሚለውን ከእኛ እንድትማሩ ነው።
ስለዚህ አንዱን ሰው ከሌላው አብልጣችሁ
አትመኩበት። [7]ለመሆኑ፣ አንተን ከሌላው
እንድትበልጥ ያደረገህ ማን ነው?
ያልተቀበልኸው የራስህ የሆነ ነገር ምን
አለ? ከተቀበልህ ታዲያ፣ እንዳልተቀበልህ
ለምን ትመካለህ?

[8]አሁንስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ
አግኝታችኋል! ሀብታምም ሆናችኋል!
ከእኛም ተለይታችሁ ነግሣችኋል! በርግጥ
ብትነግ ሡማ እኛም ከእናንተ ጋር በነገሥን
ነበር፤ [9]ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን
ሐዋርያቱን፣ ሞት እንደ ተፈረደባቸው
ሰዎች ከሰው ሁሉ መጨረሻ ያሰለፈን
ይመስለኛል፤ ለዓለም ሁሉ፣ ለመላእክትም
ለሰዎችም ትርኢት ሆነናል። [10]እኛ ስለ
ክርስቶስ ብለን ሞኞች ነን፤ እናንተ ግን
በክርስቶስ ጥበበኞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች
ነን፤ እናንተ ግን ብርቱዎች ናችሁ፤ እናንተ
የተከበራችሁ ናችሁ፤ እኛ ግን የተዋረድን
ነን። [11]እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤
እንጠማለን፤ እንራቈታለን፤ እን ደበደባለን፤
ያለ መጠለያ እንንከራተታለን፤ [12]በገዛ
እጃችን እየሠራን እንደክማለን። ሲረግሙን
እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እን ታገሣለን፤
[13]ስማችንን ሲያጠፉ መልካም እንመልሳለን።
እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጕድፍ፣ የምድር
ጥራጊ ሆነናል።

[14]ይህን የምጽፍላችሁ እንደ ተወደዳችሁ
ልጆቼ አድርጌ ልመክራችሁ እንጂ
ላሳፍራችሁ ብዬ አይደለም። [15]ምንም
እንኳ በዐሥር ሺህ የሚቈጠሩ ሞግዚቶች
በክርስቶስ ቢኖሯችሁም፣ ብዙ አባቶች ግን
የሏችሁም፤ በወንጌል አማካይነት በክርስቶስ
ኢየሱስ ወልጃችኋለሁና። [16]ስለዚህ እኔን
እንድት መስሉ እለምናችኋለሁ። [17]እንግዲህ
በጌታ የተወደደውንና የታመነውን ልጄን
ጢሞቴዎስን የላክሁላችሁ በዚህ ምክንያት

3፥22 ቍ5:6፤ ሮሜ8፥38፤ 1ቆሮ1፥12
3፥23 1ቆሮ15፥23፤ 2ቆሮ10፥17፤ ገላ3፥29
4፥1 ሮሜ16፥25፤ 1ቆሮ3፥5፤ 9፥17፤ ቲቶ1፥7
4፥4 ሐሥ23፥1፤ ሮሜ2፥13፤ 2ቆሮ10፥18
4፥5 ኢዮ12፥22፤ መዝ90፥8፤ ማቴ7፥1:2፤ ሮሜ2፥29፤ 1ቆሮ3፥13፤ 1ተሰ2፥19
4፥6 1ቆሮ1፥12፡19፡31፤ 3፥4፡19፡20
4፥7 ዮሐ3፥27፤ ሮሜ12፥3፡6
4፥8 ራእ3፥17፡18
4፥9 መዝ71፥7፤ ሮሜ8፥36፤ ዕብ10፥33
4፥10 ሐሥ17፥18፤ 26፥24፤ 1ቆሮ1፥18፤ 2፥3፤ 3፥18፤ 2ቆሮ11፥19
4፥11 ሮሜ8፥35፤ 2ቆሮ11፥23-27
4፥12 ማቴ5፥44፤ ሐሥ18፥3፤ ሮሜ12፥14፤ 1ጴጥ3፥9
4፥13 ኤር20፥18፤ ሰቆ3፥45
4፥14 1ቆሮ6፥5፤ 15፥34፤

4፥14 1ተሰ2፥11፤ 2ተሰ3፥14 4፥15 ቍ14፤ 1ቆሮ9፥12፡14፤ 18:23፤ 15፥1 4፥16 1ቆሮ11፥1፤ ፊል3፥17፤ 4፥9፤ 1ተሰ1፥6፤ 2ተሰ3፥7:9
4፥17 ሐሥ16፥10፤ 1ቆሮ7፥17፤ 16፥10፤ 1ጢሞ1፥2

[a] *3፥22 ጴጥሮስ ማለት ነው*

**4፥5 በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውንም ሐሳብ ይገልጠዋል፤** የሰውን ሁሉ ምስጢራዊ ድርጊት እግዚአብሔር ወደ ብርሃን ያመጣል፡ ክፉም ሆነ ደግ እውነተኛ ሐሳባቸውንና በልባቸው ያለውን ምኞታቸውን ይገልጣል (ማቴ 6፥3-4:6፤ 1ጢሞ 5፥24-25 እንዲሁም በገጽ 1822 ላይ፣ "*በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: በሌላ አነጋገር የማንኛውም ሰው የውስጥ ሕይወት እንዳለ ይገለጣል፤ የሚሰወር ምንም ነገር አይኖርም (ማር 4፥22፤ ሉቃ 12፥2-3፤ ሮሜ 2፥16)::

**4፥7 ለምን ትመካለህ?** ለክርስቲያናዊ ትሕትና መሠረቱ ከተወለድንበት ሀገር የምናገኘው ወይም ያለን መንፈሳዊ ስጦታ የተገኘው ከእግዚአብሔር መሆኑን መረዳት ሲሆን፣ ይህም ለከፍተኛነት፣ ለሥልጣን ወይም ለትምክህት መሠረት ሊሆን እንደማይችል ማወቅ ነው:: ያለን ሁሉና የሆንነው ሁሉ ሊገኝ የቻለው በእግዚአብሔርና በሌሎች ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔርንና ሌሎችን ልናመሰግን እንጂ ለትምክህት ቦታ ሊኖረን አይገባም::

**4፥8 የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችኋል፤ ሀብታምም ሆናችኋል፤** በቆሮንቶስ ያሉት አንዳንዶች በጥበባቸው፣ ባላቸው ከፍተኛ ዕውቀትና መንፈሳዊ ስጦታዎች ታብየዋል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የታማኝ አማኝ እውነተኛ ሕይወት የመስቀል መንገድ እንደሆነና ከክብር በፊት ሥቃይ እንደሚቀድምም አሳይቶአል (ከሮሜ 8፥17 ጋር ያነጻጽሩ)::

**4፥9 ሐዋርያቱን ሞት እንደተፈረደባቸው፤** ከቍ 9-13 ይመልከቱ፡ በዚህ ስፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያት የተቀበሉትን መከራ በዝርዝር ጽፎአል:: "ትርኢት ሆነናል" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሐዋርያትን በዓለም፣ በመላእክትና በቤተ ክርስቲያን እንዲታዩ ሥቃይ ለሞላበት ሕይወት እንደመረጣቸው ያመለክታል:: (1) ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት በጻፈበት ጊዜ እንኳ እንደ ምግብ፣ መጠጥና ተገቢውን ልብስ የመሳሰሉ ነገሮችን አጥቶአል፤ ተንቆአል፤ ተሰድቦአል እንዲሁም መኖሪያ ቤት አልነበረውም:: በከባድ ሁኔታ ቀንና ሌሊት ይሠራ ነበር፤ ተረግሞአል፤ ተሰድዶአል፤ ተዘልፎአል እንዲሁም "የዓለም ጕድፍና የምድር ጥራጊ" ሆኖአል (ከ2ቆሮ 4፥8-9፤ 6፥4-5:8-10፤ 11፥23-29፤ 12፥10):: (2) ሥቃይ በአንድ በኩል የሐዋርያዊ አገልግሎት ልዩ ጥሪ ቢሆንም (ከሐሥ 9፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን የተባበሩ ኃጢአትን፣ ኢግብረገባዊነትን፣ ሰይጣንን፣ ዓለማዊ ክፋትንና ኢፍትሐዊነትን ለሚቃወሙ አማኞች ሁሉ የጋራ እጣ ፈንታ ነው:: ሥቃያቸው የክርስቶስን ሥቃይ እንደተካፈሉ ይቈጠራል (ሮሜ 8፥17፤ ፊል 1፥29፤ 3፥10፤ 1ተሰ 3፥3)::

ነው፤ እርሱም በየስፍራው በሚገኙ አብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ ከማስተምረው ትምህርት
ጋር የሚስማማውን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ
ያለውን የሕይወት አካሄዴን ያሳስባችኋል።
18ከእናንተ አንዳንዶቹ ወደ እናንተ
የማል መጣ መስሎአቸው ታብየዋል፤
19ይሁን እንጂ የጌታ ፈቃድ ቢሆን ፈጥኜ
ወደ እናንተ እመጣለሁ፤ ከዚያም እነዚህ
ትዕቢተኞች የሚናገሩትን ብቻ ሳይሆን፣
ምን ኀይል እንዳላቸውም ማየት እሻለሁ።
20ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት
የወሬ ጕዳይ ሳይሆን የኀይል ጕዳይ
ነው። 21ለመሆኑ የምትፈልጉት የቱን
ነው? በትር ይዤ ልምጣ? ወይስ በፍቅርና
በገርነት መንፈስ?

4፥18 ቍ21፤
ኤር43፥2
4፥19
ሐሥ18፥21፤
1ቆሮ16፥5:6፤
2ቆሮ1፥15:16
4፥20
ሮሜ14፥17፤
15፥13
4፥21 2ቆሮ1፥23፤
2፥1፤ 13፥2:10
5፥1 ዘሌ18፥8፤
ዘዳ22፥30፤
27፥20
5፥2 ቍ13፤
2ቆሮ7፥7-11
5፥3 ቈላ2፥5፤
1ተሰ2፥17
5፥4 2ተሰ3፥6
5፥5 ማቴ4፥10፤
ቆሮ1፥8፤
1ጢሞ1፥20

## አሳፋሪ ኀጢአት በቤተ ክርስቲያን

5 በመካከላችሁ የዝሙት ርኵሰት እንዳለ
በርግጥ ይወራል፤ እንዲህ ያለው
ርኵሰት በአረማውያን ዘንድ እንኳ ታይቶ
የማይታወቅ ነው፤ የአባቱን ሚስት ያገባ
ሰው አለና። 2ደግሞም ታብያችኋል!
ይልቅስ ሐዘን ተሰምቶአችሁ፣ ይህን
ድርጊት የፈጸመውን ሰው ከመካከላችሁ
ልታስወግዱት አይገባምን? 3ምንም እንኳ
እኔ በአካል አብሬያችሁ ባልሆንም፣
በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ልክ
አብሬያችሁ እንዳለሁ ሆኜ፣ ይህን
ባደረገው ሰው ላይ አሁኑኑ ፈርጄበታለሁ፡
፡ 4በምትሰበሰቡ በት ጊዜ እኔም በመንፈስ
ከእናንተ ጋር ስለ ምሆን፣ በጌታችን
በኢየሱስ ስምና በመካከላችሁ በሚገኘው
በጌታችን በኢየሱስ ኀይል፣ 5ሥጋው[a]

[a]5፥5 ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮው ወይም አካሉ

**4፥20 የእግዚአብሔር መንግሥት ... የኀይል ጕዳይ ነው፤** "የእግዚአብሔር መንግሥት" ራሱን በኀይል ይገልጣል። ስለዚህ የዚያ መንግሥት አባላት ከወሬና ከመልእክት በላይ የሆነ የሚታይ ነገር ሊኖራቸው ይገባል፤ የመንፈስ ቅዱስንም ኀይል መግለጥ አለባቸው (2፥4፤ ሐሥ 1፥8)። በአዲስ ኪዳን ይህ ሰዎችን ስለ ኀጠ አት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ የሚወቅሰውን (ዮሐ 16፥8)፣ ወደ ድነት የሚያመጣውን (ቍ 15፤ ሐሥ 26፥16-18)፣ ታምራት የሚያደርገውን (2፥4 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፣ የጽድቅ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን ኀይል የሚያመለክት ነው (ሮሜ 14፥17)።

**5፥1 በመካከላችሁ የዝሙት ርኵሰት፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ኢግብረገባዊነትና መሪዎች በደሉን በፈጸመው ሰው ላይ እርምጃ ስላለመውሰዳቸው ጽፎአል (ቍ 1-8)። ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሕዝብ ስብስብ እንደመሆኗ መጠን በአባላቱ መካከል ኢግብረገባዊ ድርጊት ሲፈጸም መፍቀድ ወይም መታገሥ እንደሌለባት አስታውቆአል። በደል በሚፈጽሙ አባላት ላይ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዐት እርምጃ የምትወስድበትን የሚከተሉትን ሦስት ምክንያቶች ሰጥቶአል፤

(1) በደል ለፈጸሙ ሰዎች ጥቅም (ቍ 5)። በደለኞች ከቤተ ክርስቲያን መወገዳቸው በኀጢአታቸው እንዲጸጸቱ እንዲሁም የምሕረትንና የመመለስን አስፈላጊነት እንዲረዱ ያደርጋል።

(2) ለቤተ ክርስቲያን ቅድስና (ቍ 6-8)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ክፋት መታገሥ ቀስ በቀስ የሌሎች ግብረገባዊ የሕይወት ደረጃ እጅግ ዝቅ እንዲል ያደርጋል።

(3) ለዓለም ጥቅም (ከቍ 1 ጋር ያነጻጽሩ)። ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ከመሰሉ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማርካ ማምጣት አትችልም (ከማቴ 5፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዐት የተጠቀሱትን ሌሎች የአዲስ ኪዳን ምንባቦችን ለማየት ማቴ 5፥22፤ 18፥15-17፤ 2ተሰ 3፥6 እና ራእ 2፥19-23 ይመልከቱ።

**5፥1 የአባቱን ሚስት ያገባ፤** ትክክለኛው ኀጢአት ምን እንደሆነ በግልጽ አልተጠቀሰም። ሐዋርያው ጳውሎስ "የአባቱን ሚስት" ብሎ ሲናገር ሰውየው ምናልባት ከእንጀራ እናቱ ጋር ወሲብ ሳይፈጽም አልቀረም። (1) ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዐይነቱን ኢግብረገባዊነት በመታገሷ ጳውሎስ ደስ ካለመሰኘትም በላይ ሁኔታው አስደንግጦታል፤ ይህ ችግር አንድ ግለሰብ ከሠራው ኀጢአት በላይ እጅግ የከፋ እንደሆነም ተመልክቶአል።

(2) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ልልነት አሁን ላለንበት ሁኔታ የሚናገረው ነገር አለ፤ ዛሬ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ምንዝርናንና ማናቸውንም ዐይነት ኢግብረገባዊ ወሲብን ጨምሮ በአባሎቻቸው መካከል ያለውን ኢግብረገባዊነት፣ ሲታገሡና በዝምታ ሲያልፉ ይታያል። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ወሲብ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ወጣቶች መካከል ሲከሠት በትዕግሥት መታለፉ ብቻ ሳይሆን፣ አንዳንድ ጊዜ የፍቅርና የቃል ኪዳን ማሰሪያ ነው በሚል ሽፋን ተቀባይነት አግኝቶ መነገሩ የሚያሳፍር ነው። ጥቂት የማይባሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዛሬ በወጣቶች መካከል የሚታየውን ቅጥ ያጣ የመተሻሼት ልማድን በክርስቶስ ስም መቃወም አልቻሉም። ልክ እንደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሕዝቡ በዙሪያው የሚኖረውን ኅብረተሰብ አኗኗር በይበልጥ እየተለማመደ ሲረክስ አዝነው ማልቀስ እንደሚገባቸው አላለቀሱም። እነዚህ መሪዎች በራሳቸው ነገር በመርካት "የዘመኑ ሰዎች ስለሆንን ፈራጅ ልንሆን አይገባንም" በማለት ኀጢአት መሥራትን ይፈቅዳሉ።

**5፥2 ሐዘን ተሰምቶአችሁ፤** በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች ቤተ ክርስቲያን በአባላቶቿ መካከል ኢግብረገባዊነት ሲገኝ ሊኖራት የሚገባውን ስሜት ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ገልጾአል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቅድስናና የእርሱንም ኀጢአትን የመጸየፍ ባሕርይ የሚጋሩ ሐዘንና ጸጸት ይሰማቸዋል (ከኢሳ 6 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ከመካከላቸውም ርኵሰትን ያስወግዳሉ (ቍ 2:4-5:7:13)።

**5፥5 እንደዚህ ዐይነቱ (ሰው) ለሰይጣን ይሰጥ፤** ለሰይጣን ይሰጥ ማለት ቤተ ክርስቲያን ኢግብረገባዊ የሆነውን ሰው ከኅብረትዋ በማስወገድ ወደ ሰይጣን ግዛት ትመልሰው ማለት ነው፡ ይህም ግለሰቡን አፍራሽ ለሆነው የሰይጣንና የኢጋንንት ሥራ እንዲጋለጥ ያደርገዋል (ቍ 7:13)። (1) ይህ የሥነ ሥርዐት እርምጃ ሁለት ዐላማዎች አሉት፤ (ሀ) በደልን የፈጸመው ሰው ችግርና አካላዊ ሥቃይ ሲያጋጥመው ንስሓ ሊገባ፣

ጠፍቶ መንፈሱ በጌታ ቀን ትድን
ዘንድ፣ እንደዚህ ዐይነቱ ለሰይጣን ይሰጥ።
[6]መመካታችሁ መልካም አይደለም።
ጥቂት እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካው
አታውቁምን? [7]አሁን ያለ እርሾ እንደ
ሆናችሁ ሁሉ አዲስ ሊጥ እንድትሆኑ
አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ የፋሲካ በጋችን
የሆነው ክርስ ቶስ ተሠውቶአልና። [8]ስለዚህ
በዓሉን ግፍና ክፋት በሞላበት እርሾ፣
በአሮጌ እርሾ ሳይሆን፣ እርሾ በሌለበት ቂጣ
በቅንነትና በእውነት እናክብር።
[9]ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ
በመልእክቴ ጽፌላችሁ ነበር፤ [10]እንዲህም
ስል በጠቅላላው ከዚህ ዓለም ሴሰኞች ወይም
ስግብ ግቦችና ቀማኞች፣ ወይም ከጣዖት
አምላኪዎች ጋር አትተባበሩ ለማለት
አይደለም፤ እንደዚያማ ቢሆን ከዚህ ዓለም
ጨርሶ መለ የት ያስፈልጋችሁ ነበር። [11]ነገር
ግን አሁን የጻፍሁላችሁ፣ "ወንድም ነኝ"
እያለ ከሚሴስን ወይም ከሚስገበገብ ወይም
ጣዖትን ከሚያመልክ ወይም ከሚሳደብ
ወይም ከሚሰክር ወይም ከሚቀማ ጋር
እንዳትተባበሩ ነው፤ ከእንደዚህ ዐይነቱ ሰው
ጋር ምግብ እንኳ አትብሉ።
[12]ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ባሉት ሰዎች
ላይ ለመፍረድ እኔን ምን አገባኝ? በቤተ
ክርስቲያን ውስጥ ባሉት ሰዎች ላይ እና ንተ
አትፈርዱምን? [13]ከቤተ ክርስቲያን ውጪ
ባሉት ላይ የሚፈርድ ግን እግዚአብሔር ነው፤
እንግዲህ፣ "ክፉውን ሰው ከመካ ከላችሁ
አስወግዱት።"

## መካሰስ በክርስቲያኖች መካከል

6 ከመካከላችሁ አንድ ሰው ከሌላው ጋር
ሙግት ቢኖረው፣ ጕዳዩን በቅዱሳን ፊት
በማቅረብ ፈንታ እንዴት ደፍሮ በማያምኑ
ሰዎች ፊት ለመፋረድ ያቀርባል? [2]ቅዱሳን
በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን?
በዓለም ላይ የምትፈርዱ ከሆነ፣
እንግዲያው፣ በትንሹ ነገር ላይ ለመፍረድ
አትበቁምን? [3]በምድራዊ ሕይወት
ጕዳይ ቀርቶ፣ በመ ላእክት ላይ እንኳ
እንደምንፈርድ አታውቁ ምን? [4]እንግዲህ
እንዲህ ያለ ጕዳይ ሲያጋጥማችሁ፣ በቤተ
ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጅ

5፥6 ማቴ16፥6:12፤ ገላ5፥9፤ ያዕ4፥16
5፥7 ዘፀ12፥3-6:21፤ ማር14፥12፤ 1ጴጥ1፥19
5፥8 ዘፀ12፥14:15፤ ዘዳ16፥3
5፥9 ኤፌ5፥11፤ 2ተሰ3፥6:14
5፥10 1ቆሮ10፥27
5፥11 ሮሜ7፥1፤ 16፥17፤ 1ቆሮ10፥7:14
5፥12 ቍ3-5፤ ማር4፥11፤ 1ቆሮ6፥1-4
5፥13 ዘዳ13፥5፤ 17፥7፤ 19፥19፤ 22፥21:24፤ 24፥7፤ መሳ20፥13
6፥1 ማቴ18፥17
6፥2 ማቴ19፥28፤ ሉቃ22፥30፤ 1ቆሮ5፥12

---

በመጨረሻም ሊድን ይችላል (ከሉቃ 15፥11-24 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ለ) የእግዚአብሔርም ሕዝብ አዲሱን የቂጣ በዓል በቅንነትና በእውነት ያከብር ዘንድ (ቍ 8)፣ ቤተ ክርስቲያን አሮጌውን እርሾ እንድታስወግድ (ቍ 7 ኀጢአት መሥራትን ማለት) ነው:: (2) የክርስትናን ሕይወት በመተው ወደ ዓለም የተመለሰውን ሰው ለማዳን የምትሻው የዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ እርምጃ ልትወስድ ይገባታል (ከ1ጢሞ 1፥20 ጋር ያነጻጽሩ)::

**5፥6 ጥቂት እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካው፤** በመጽሐፍ ቅዱስ "እርሾ" (ሊጥ እንዲቦካ የሚያደርግ) ፍጹም ወደ ሆነ ነገር ዘልቆ በመግባት እውነትን፣ ጽድቅንና፣ መንፈሳዊ ሕይወትን የሚበክል ነገር ምሳሌ ነው (ገላ 5፥7-9፤ ዘፀ 13፥7 እና ማብ፤ ማር 8፥15 እና ማብ ይመ):: ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል እርሾን ኀጢአትና ርኵሰት ብዙዎች እስኪበከሉበት ድረስ ቀስ በቀስ ወደ ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ከሚሠራጭበት ሁኔታ ጋር ያነጻጽረዋል:: በአባላቷ መካከል በተገለጠ ወሲባዊ ኢግብረገባዊነት ላይ ቈራጥ እርምጃ የማትወስድ ማንኛዋም ቤተ ክርስቲያን ክፋት በኅብረትዋ እየተሠራጨና ብዙዎችን እየጠቃ ያለበት ሁኔታ ውስጥ ራሷን ታስገባለች:: ኀጢአት በጥብቅ ተወግዞ መወገድ አለበት፤ አለበለዚያ መላው ክርስቲያናዊ ኅብረት ይበከልና መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ይጠፋል (ራእ 2-3 እና ማብ ይመ)::

**5፥12 በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉት ... አትፈርዱምን?** አማኞች በሌላው አማኝ ላይ ጥራዝ ነጠቅ የሆነ ወይም ፍትሐዊ ያልሆነ ፍርድ ማስተላለፍ የለባቸውም (ከማቴ 7፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ):: ይሁን እንጂ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ በአባላት መካከል ከባድ ኀጢአት፣ ኢግብረገባዊነት ወይም የማያቋርጥ ርኵሰት ሲከሠት ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃልና በጽድቅ መስፈርት መሠረት መፍረድ እንዳለባት አመልክቶአል:: እንዲህ ዐይነት የርኵሰት ድርጊቶች ሲፈጸሙ በደል የፈጸመውን ሰው ሕይወት ለማስተካከል፣ የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና ለመጠበቅ በዓለም ውስጥ ሊገለጥ የሚገባውን የክርስቶስን ምስክርነት ለማሳየት ፍርድንና የሥነ ሥርፀት እርምጃን መፈጸም ተገቢ ይሆናል (ቍ 1 እና ማብ ይመ)::

**6፥1 በማያምኑ ሰዎች ፊት፤** በክርስቲያኖች መካከል ግጭቶች ሲነሡ (ቍ 2) በሕግ ፊት ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍርድ ሊሰጥባቸው ይገባል:: ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ የሆነውንና ያልሆነውን በመለየት ፍርድ መስጠት ትችላለች፤ ውሳኔ በመስጠትም እንደ አስፈላጊነቱ የሥነ ሥርዐት እርምጃ መውሰድ አለባት (ማቴ 18፥15 እና ማብ ይመ):: (1) ይህ ትምህርት አማኝ ካላመነ ሰው ጋር እጅግ ከባድ የሆነ ጠብ ቢያጋጥመው፣ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ማድረስ የለበትም ለማለት አይደለም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ ይግባኝ ለማለት ከአንድ ጊዜ በላይ ፍርድ ቤት ተመላልሶአል (ሐሥ 16፥37-39፤ 25፥10-12)::

(2) በሌላም በኩል ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን መበለቶችን፣ ሕፃናትን ወይም ደካሞችን የመሳሰሉ ምስኪን አባሎቿ ያለ ሕግ ሲበደሉ ወይም ጉዳት ሲደርስባቸው መፍቀድ አለባት ማለቱ አይደለም:: ነገር ግን ጳውሎስ ትክክለኛ የሆነውንና ያልሆነውን ነገር በግልጽ ለማወቅ ያልተቻለባቸውን ጕዳዮች ማለቱ ነው:: በድፍረት የሚሠሩ ኀጢአቶችን በትዕግሥት ማለፍ ተገቢ አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በማቴ 18፥15-17 ላይ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት እርምጃ ሊወስድባቸው ይገባል::

(3) ከዚህም በላይ "ወንድም ነኝ" ባይ ሚስቱን የፈታበትና ቤተ ሰቡን የተወበት እንዲሁም ለሚስቱና ለልጆቹ ተገቢውን አበል ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነበት ዐይነት ችግር ሲያጋጥም፣ እናትየው በቀና ልቦና ልጆቿን ለማሳደግ የሚያስፈልጋትን ተቈራጭ ለማስከበር ጉዳዩን ፍርድ ቤት ልታቀርብ ትችላለች:: ሐዋርያው ጳውሎስ ሕግን በመጣስ የሌላውን ሰው ሕይወት ወይም ደህንነት ለመጉዳት የሚያጭበረብሩትንና ጥቃት የሚያደርሱትን አያበረታታም:: በቍ 8 ላይ የተናገረው ጥቅስ በአነስተኛ ስሕተት ሳቢያ የተፈጠረ ግጭት በትዕግሥት ሊታለፍ ወይም ሊታረም እንደሚገባ ያመለክታል::

አድርጋችሁ ሹሙ[ሀ]! 5ይህንንም የም ለው
ላሳፍራችሁ ብዬ ነው። ለመሆኑ ከመካከ
ላችሁ ወንድሞችን ለማስታረቅ የሚበቃ
አስተዋይ ሰው የለምን? 6ነገር ግን ወንድም
ወንድሙን ለመክሰስ ፍርድ ቤት ይሄዳል፤
ያውም በማያምኑ ሰዎች ፊት!
7እንግዲህ በመካከላችሁ መካሰስ መኖሩ
ራሱ ውድቀታችሁን ያሳያል። ብትበደሉ
አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? 8እና
ንተ ግን ራሳችሁ ትበድላላችሁ፤ ታታልላ
ላችሁም፤ ያውም ወንድሞቻችሁን።
9ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እን
ደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አት
ታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመ
ንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማው
ያን፣ 10ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራ
ሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን
መንግሥት አይወርሱም። 11ከእናንተ
አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤
አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና
በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳ
ችኋል፤ ጸድቃችኋል።

## የዝሙት ኀጢአት

12"ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤" ይሁን
እንጂ ሁሉም ነገር አይጠቅምም፤ "ሁሉ
ነገር ተፈ ቅዶልኛል፤" ይሁን እንጂ ምንም
ነገር በእኔ ላይ አይሠለጥንም። 13ደግሞም፣
"ምግብ ለሆድ ነው፤ ሆድም ለምግብ ነው፤"
እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም ያጠፋቸዋል። ሰው
ነት ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤
ጌታም ለሰውነት ነው። 14እግዚአብሔር ጌታን
ከሙታን አንዳስነሣው፣ እኛንም ደግሞ በኀ
ይሉ ከሙታን ያስነሣናል። 15ሰውነታችሁ
የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች እንደ ሆነ
አታውቁምን? ታዲያ፣ የክርስቶስን ብልቶች
ወስጄ ከዝሙት አዳሪ ሴት ብልቶች ጋር
አንድ ላድርገውን? ከቶ አይገባም! 16ወይስ
ከዝ ሙት አዳሪ ጋር የሚተባበር ሰው ከእርሷ
ጋር አንድ ሥጋ እንደሚሆን አታውቁምን?
"ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ" ተብሎአልና፡
፡ 17ነገር ግን ከጌታ ጋር የሚተባበር ከእርሱ
ጋር አንድ መንፈስ ይሆናል።
18ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚሠራው
ኀጢአት ሁሉ ከአካሉ ውጭ ነው፤ ዝሙትን
የሚፈ ጽም ግን በገዛ አካሉ ላይ ኀጢአት
ይሠራል። 19ለመሆኑ፣ ሰውነታችሁ

6፥5 ሐሥ1፥15፤ 1ቆሮ4፥14
6፥6 ሮሜ7፥1፤ 2ቆሮ6፥14:15፤ 1ጢሞ 5፥8
6፥7 ማቴ5፥39:40
6፥8 1ተሰ4፥6
6፥9 ዘሌ18፥20:22፤ ዘዳ22፥22፤ ኢዮ13፥9፤ ማቴ25፥34፤ 1ቆሮ15፥33፤ ገላ6፥7፤ ያዕ1፥16
6፥10 1ጢሞ1፥10፤ ራእ21፥8፤ 22፥15
6፥11 ሐሥ22፥16፤ ሮሜ4፥25፤ 1ቆሮ1፥2፤ ኤፌ2፥2
6፥12 1ቆሮ10፥23
6፥13 ቆላ15፥19፤ ሮሜ12፥1፤ ቆላ2፥22
6፥14 ሐሥ2፥24፤ ሮሜ6፥5፤ ኤፌ1፥19:20፤ 1ተሰ4፥16
6፥15 ሮሜ12፥5
6፥16 ዘፍ2፥24፤ ማቴ19፥5፤ ኤፌ5፥31
6፥17 ዮሐ17፥21-23፤ ሮሜ8፥9-11፤ ገላ2፥20 6፥18 ቆላ9፤ ሮሜ6፥12፤ 1ቆሮ5፥1፤ 2ቆሮ12፥21፤ ቆላ5፥19፤ ኤፌ5፥3፤ 1ተሰ4፥3:4፤ ዕብ13፥4 6፥19 ዮሐ2፥21፤ ሮሜ14፥7:8

*[ሀ]6፥4 ወይም በቤተ ክርስቲያን የተናቁ ሰዎችን ፈራጅ አድርጋችሁ ትሾማላችሁ?*

**6፥9 ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ፤** በቆሮንቶስ የነበሩት አንዳንዶች ከክርስቶስ ጋር የነበራቸውን ኅብረት ቢያፈርሱ፣ ቢክዱት፣ በኢግብረገባዊነትና በኢፍትሐዊነት ቢኖሩ እንኳ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያላቸው ድኅነትና ርስት ተጠብቆ እንደሚቆይላቸው በማመን በሐሳባቸው ተታለው ነበር:: (1) ይሁን እንጂ, መንፈሳዊ ሞት ኀጢአትን አዘውትረው ለሚሠሩት ሰዎች ለክርስቲያኖች እንኳ ቢሆኑ የማይቀር ውጤት እንደ ሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ተናግሮአል (ከሮሜ 8፥13 ጋር ያነጻጽሩ):: ማንም ኢግብረገባዊ ፍላጎቱን በመፈጸም እየኖረ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይችልም (ከሮሜ 6፥16፤ ከያዕ 1፥15 ጋር ያነጻጽሩ፤ 1ዮሐ 2፥4 እና ማብ፤ 3፥9 እና ማብ ይመ):: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ዋና ትምህርት በመደጋገም አስተምሮአል (ለምሳሌ ገላ 5፥21 እና ኤፌ 5፥5-6):: ይህ መርሕ በብሉይ ኪዳን ነቢያት በተደጋጋሚ ይነገር እንደነበር ልብ ይበሉ (ኤር 8፥7 እና ማብ፤ 23፥17 እና ማብ፤ ሕዝ 13፥10 እና ማብ)::

(2) የሐዋርያው ጳውሎስ ማስጠንቀቂያ መላውን የክርስቲያን ኅብረተሰብ የሚመለከት ነው:: መታለል አይገባንም፤ ክፉዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱምና:: ያለመንፈስ ቅዱስ የዳግም ልደት ሥራና የመቀደስ ሥራ ድነት በጳውሎስ የሥነ መለኮት ትምህርት ውስጥ ስፍራ የለውም::

**6፥11 በአምላካችን መንፈስ … ጸድቃችኋል፤** መጽደቅ ጌታ ኢየሱስ የሠራውን የቤዛነት ሥራ የሚያካትት ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚሠራውንም ይጨምራል (በገጽ 1735 ላይ፣ *"ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**6፥12 ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤** ይህ ዐረፍተ ነገር የጳውሎስ ተቃዋሚዎች ሥነ መለኮታዊ አቋም እንደሆነ በግልጽ ማወቅ ይቻላል:: የፈለጉትን ሁሉ የማድረግ መብት እንዳላቸው ያስቡ ነበር::

**6፥15 የክርስቶስን ብልቶች፤** ሐዋርያው በግብረገባዊ ልልነት ላይ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ዝሙት በአማኝ ላይ የሚያመጣውን የከፋ ውጤት አመልክቶአል:: አንድ አማኝ አካሉን ከአመንዝራ ሴት አካል ጋር አንድ ሲያደርግ፣ የክርስቶስ መስቀል የቀደሰውን በማርከስና (ቁ. 15) ራሱን ከእግዚአብሔር መንግሥት በመቍረጥ (ቁ. 9) በእርስዋ ቍጥጥር ሥር ለመሆን ከእርስዋ ጋር አንድ ሥጋ ይሆናል (ቁ. 16 ይመ፤ ከዘፍ 2፥24 ጋር ያነጻጽሩ):: በዝሙት ሰዎች ብልቶቻቸውን ከኢግብረገባዊና ከረከሱ ሰዎች ጋር አንድ በማድረግ ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር ከነበራቸው ኅብረት ዘወር ያደርጋሉ ማለት ነው::

**6፥18 ከዝሙት ሽሹ፤** በተለይ ዝሙት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ አስጸያፊ ነው:: ከማንኛውም ኀጢአት ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ወይም ቤተ መቅደስ የሆነውን ሥጋ ያረክሳል (ቁ. 15-20):: ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ከዝሙት መሸሽ እንደሚገባ በማስጠንቀቅ ምክር ይሰጣል:: የተጠቀሰው ሐረግ በአሁን ጊዜያት መቅረቡ፣ ክርስቲያን ከዚህ ኀጢአት በተደጋጋሚ መሸሽ እንዳለበት ለማሳሰብ ነው (ከዘፍ 39፥12 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 1980 ላይ፣ *"ሩካቤ ሥጋ የሚገዛበት ሥነ ምግባር"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**6፥19 ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ፤** ክርስቲያን እንደመሆናችሁ መጠን ሰውነታችሁ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው (እኛ የእግዚአብሔር መሆናችንን የሚያረጋግጠውን የመንፈስ ቅዱስን ምልክት በሮሜ 8፥11 ይመ):: መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ስለሚኖር እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ፤ በክፉት ወይም በርኩሰት፣ በኢግብረገባዊ ሐሳብም ሆነ ፍላጎት፣ በድርጊቶች፣ በፊልሞች፣ በመጻሕፍት ወይም

በውስጣችሁ የሚኖ ረው የመንፈስ ቅዱስ
ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? ይህም
መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው።
እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፤ 20በዋጋ
ተገዝታችኋልና፤ ስለዚህ በሰውነታችሁ
እግዚአብሔርን አክብሩ።

## ጋብቻን በተመለከተ

7 ስለ ጻፋችሁልኝ ጉዳይ፣ ሰው ወደ
ሴት ባይደርስ መልካም ነው[a]፤ 2ነገር
ግን ከዝሙት ለመጠበቅ፣ እያንዳንዱ ሰው
የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም
ሴት የራሷ ባል ይኑራት። 3ባል ለሚስቱ
የሚገባትን ሁሉ ያድርግላት፤ ሚስትም
እንዲሁ ለባሏ የሚገ ባውን ሁሉ
ታድርግለት። 4ሚስት አካሏ የራሷ ብቻ
አይደለም፤ የባሏም ነው፤ እንዲሁም ባል
አካሉ የራሱ ብቻ አይደለም፣ የሚስቱም
ነው። 5በጸሎት ለመትጋት ተስማምታችሁ
ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ እርስ
በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን
ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ
እንደ ገና አብራችሁ ሁኑ።
6ይህን የምለው ግን እንደ ትእዛዝ ሳይ
ሆን እንደ ምክር ነው። 7ሰው ሁሉ እንደ እኔ
ቢሆን ምኞቴ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው
ከእግዚአብሔር የተቀበለው የራሱ የሆነ ስጦታ
አለው፤ አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ ሲኖረው፣
ሌላው ደግሞ ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው።
8ላላገቡና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች
ግን እንዲህ እላለሁ፤ ሳያገቡ እንደ እኔ
ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው። 9ነገር ግን
ራሳቸውን መግዛት ካልቻሉ ያግቡ፤ በም
ኞት ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና።
10ላገቡት ይህን ትእዛዝ እሰጣለሁ፤
ይህም ትእዛዝ የጌታ እንጂ የእኔ አይደለም።
ሚስት ከባሏ አትለያይ፤ 11ብትለያይ ግን
ሳታገባ ትኑር፤ አለዚያ ከባሏ ጋር ትታረቅ፤
ባልም ሚስቱን አይፍታት።
12ለሌሎች ደግሞ እንዲህ እላለሁ፤
ይህንም የምለው እኔ እንጂ ጌታ አይደለም።
ያላመ ነች ሚስት ያለው ወንድም ቢኖርና
ሚስቱ አብራው ለመኖር የምትፈቅድ ከሆነ፣
ሊፈ ታት አይገባውም። 13ያላመነ ባል ያላት
ሴት ብትኖርና እርሱም አብሮአት ለመኖር
የሚፈ ቅድ ከሆነ፣ ልትፈታው አይገባትም።
14ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፤
ያላመነችም ሚስት በሚያምን ባሏ
ተቀድሳለች፤ አለዚያማ ልጆቻችሁ ርኩሳን
በሆኑ ነበር፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።

6፥20 መዝ74፥2፤ ማቴ20፥28፤ ሐሥ20፥28፤ 1ቆሮ7፥23፤ ፊል1፥20፤ ራእ5፥9፤ 14፥4
7፥1 ቍ8፡26
7፥3 ዘፀ21፥10፤ 1ጴጥ3፥7
7፥5 ዘፀ19፥15፤ 1ሳሙ21፥4፡5፤ ማቴ4፥10፤ 1ተሰ3፥5
7፥6 2ቆሮ8፥8
7፥7 ቍ8፤ ማቴ19፥11፡12፤ ሮሜ12፥6፤ 1ቆሮ9፥5፤ 12፥4፡11
7፥8 ቍ1፡26
7፥9 1ጢሞ5፥14
7፥10 ሚል2፥14-16፤ ሉቃ16፥18
7፥11 ቍ39፤ ሮሜ7፥2፡3
7፥12 ቍ6፡10፤ 2ቆሮ11፥17
7፥14 ሚል2፥15
7፥15 ሮሜ14፥19፤ 1ቆሮ14፥33

*[a] 7፥1 ወይም ሰው ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባያደርግ መልካም ነው*

---

በመጽሔቶች ሰውነታችሁ መርከስ የለበትም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሰውነታችሁ እግዚአብሔርን በሚያከብርበትና ደስ በሚያሰኝበት መንገድ መኖር ይገባችኋል (ቍ 20)፡፡

**7፥1 ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው፤** ሰባተኛው ምዕራፍ በአጠቃላይ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጋብቻ ግንኙነትን በተመለከተ ላቀረበችው ጥያቄ ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጠው ምላሽ ነው፡፡ መመሪያዎቹ፣ “አሁን ካለው ችግር የተነሣ ባላችሁበት ሁኔታ ብትኖሩ መልካም ይመስለኛል” ከሚለው በቍ 26 ላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ አንጻር ሊታዩ ይገባል፡፡ ለጥንት ክርስቲያኖች የችግርና የስደት ጊዜ እየመጣባቸው ነው፤ በዚህ ሁኔታም ውስጥ በትዳር መጠመድ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

**7፥3 ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ ያድርግላት፤** የጋብቻ ቃል ኪዳን የሚያመለክትው እያንዳንዱ የትዳር ጓደኛ የየራሱን አካል ልዩ መብት በመተው ሌላው ባለመብት እንዲሆን ፈቃድ መስጠቱን ነው፡፡ ይኸውም የትኛውም የትዳር ጓደኛ የሌላውን ተገቢ የሆነ ወሲባዊ ፍላጎት ለማክበር ይቸገር ይሆናል ማለት ነው፡፡ በጋብቻ ውስጥ ያሉ እንዲህ ዐይነት ፍላጎቶች ተገቢና ከእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው፤ የትዳር ጓደኛን ፍላጎት ለማሟላት ፈቃደኛ አለመሆን ጋብቻን ሰይጣን ለሚያመጣው የምንዝርና ፈተና የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል (ቍ 5)፡፡

**7፥11 ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር፤** በቍ 10 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ጋብቻን የመሠረተው ዘላቂነት ይኖረው ዘንድ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ጠቅሶአል፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የጋብቻ ግንኙነት ሲበላሽ ሊሸከሙት የማይቻል ስለሚሆን ከትዳር ጓደኛ መለያየት አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ እንዳለም ተገንዝቦአል፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ይህን ሲናገር በዝሙት ምክንያት (ማቴ 19፥9) ወይም ያላመነ ወገን መለያየትን ቢፈልግ (ቍ 15 ማብ ይመ) የሚፈቀደውን ፍቺ ማመልከቱ አይደለም፤ ከዚያ ይልቅ ያለ ሕጋዊ ፍቺ የሚደረገው መለያየት በተመለከተ መናገሩ ነው፡፡ ምናልባትም አንዱ የትዳር ጓደኛ በሌላው የትዳር ጓደኛ እንዲሁም በልጆቻቸው አካላዊና መንፈሳዊ ሁኔታ ላይ ዐደጋ የሚያደርስበት ሥጋት ካለ ከመለያየት በቀር ሌላ አማራጭ አለመኖሩን ለማመልከት ይሆናል፡፡ እንዲህ ዐይነት ችግር ሲከሠት ከትዳር ጓደኛሞቹ አንዱ ከቤት ወጥቶ ሳያገባ ቢኖር የተሻለ ይሆናል፡፡ አንዱ የትዳር ጓደኛ በሌላው የትዳር ጓደኛው እንዲሁም በልጆቻቸው ላይ ተደጋጋሚ አካላዊ ጉዳት ወይም ውርደት እያደረሰ መቀመጡን ሐዋርያው ጳውሎስ ይደግፋል ማለት የሚታመን አይደለም፡፡

**7፥12 እንዲህ እላለሁ፤ ይህንም የምለው እኔ እንጂ ጌታ አይደለም፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የራሱን አስተያየት ብቻ እየሰጠ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ ሊጽፈው ስላሰበው ጉዳይ ከኢየሱስ ገና ማረጋገጫ አለማግኘቱን ለማመልከት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሲጽፍ ይህን ሥልጣን እንዳለውና በመለኮታዊ ምሪት ሥር መሆኑንም ርግጠኛ በመሆን ነው (ከቍ 25:40፤ 14፥37 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

**7፥14 ባል ... ሚስት ... ልጆቻችሁ፤** አማኝ ክርስቶስን ለመከተል ከመወሰኑ በፊት ካላመነ ሰው ጋር ጋብቻን መሥርቶ ቢሆን፣ ጋብቻውም ሆነ ከጋብቻው የተገኙ ልጆች ጉዳይ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ይህ አማኝ ካላመነው ሰው ጋር መኖር አለበት እንጂ ጋብቻውን ወይም ቤቱን ለማፍረስ መሻት የለበትም፡፡ ከዚህም በላይ ያመነው ሰው ያላመነውን የትዳር ጓደኛውን ወደ ክርስቶስ ለመምራት አመቺ ሁኔታ ይኖረዋል (ከ1ጴጥ 3፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

**7፥15 የታሰሩ አይደሉም፤** ያላመነው የትዳር ጓደኛ አማኝ የሆነውን የትዳር ጓደኛውን የሚተውበት

[15]ነገር ግን የማያምነው ወገን መለየት
ከፈለገ ይለይ፤ አንድ ወንድም ወይም እኅት
በዚህ ሁኔታ የታሰሩ አይደሉም፤ እግዚአብሔር
የጠራን በሰላም እንድንኖር ነው። [16]አንቺ
ሴት፤ ባልሽን ታድኚው እንደ ሆን ምን
ታውቂያለሽ? ወይስ አንተ ሰው፤ ሚስትህን
ታድናት እንደ ሆን ምን ታውቃለህ?
[17]ብቻ እያንዳንዱ ሰው ጌታ እንደ
ወሰነ ለት፣ እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደ
ጠራው በዚያው ይመላለስ። በአብያተ
ክርስቲያናትም ሁሉ የምንደነግገው ይህንኑ
ነው። [18]አንድ ሰው ተገርዞ ሳለ ቢጠራ፣
እንዳልተገረዘ ሰው አይሁን፤ ሳይገረዝም
ተጠርቶ ከሆን አይገረዝ። [19]መገረዝም ሆነ
አለመገረዝ አይጠቅምም፤ ዋናው ነገር
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸሙ ነው።
[20]እያንዳንዱ ሰው በተጠራበት ሁኔታ ጸንቶ
ይኑር። [21]በተጠራህ ጊዜ ባሪያ ነበር ህን?
በዚህ አትጨነቅ፤ ነጻነትህን ማግኘት ከቻልህ
ግን ነጻነትህን ተቀበል። [22]ምክንያቱም
ባሪያ ሆኖ ሳለ በጌታ የተጠራ፣ የጌታ ነጻ
ሰው ነው፤ እንዲሁም ሲጠራ ነጻ የነበረ ሰው
የክርስቶስ ባሪያ ነው። [23]በዋጋ ተገዝታች
ኋል፤ ስለዚህ የሰው ባሪያዎች አትሁኑ። [24]ወን
ድሞች ሆይ፤ እያንዳንዱ ሰው በተጠራበት
ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ጸንቶ ይኑር።
[25]ስለ ደናግል፣ ከጌታ የተቀበልሁት
ትእዛዝ የለኝም፤ ይሁን እንጂ፣ ከጌታ
ምሕረት የተነሣ እንደ ታማኝ ሰው፣
ምክሬን እሰጣ ለሁ። [26]አሁን ካለው ችግር
የተነሣ ባላችሁበት ሁኔታ ብትኖሩ መልካም
ይመስለኛል። [27]አግብተህ ከሆነ መፋታትን
አትሻ፤ ካላገባህም ሚስት ለማግባት
አትፈልግ። [28]ብታ ገባ ግን ኀጢአት
አልሠራህም፤ ድንግሊቱም ብታገባ ኀጢአት
አላደረገችም። ነገር ግን የሚያገቡ ሰዎች
በዚህ ዓለም ብዙ ችግር ይገ ጥማቸዋል፤
እኔም ይህ እንዳይደርስባችሁ እወዳለሁ።
[29]ወንድሞች ሆይ፤ ሐሳቤ እንዲህ ነው፤

7፥16
ሮሜ11፥14፤
1ጴጥ3፥1
7፥17 ሮሜ12፥3፤
1ቆሮ4፥17፤
14፥33፤
2ቆሮ8፥18፤
11፥28
7፥18
ሐሥ15፥1:2
7፥19 ሮሜ2፥25-
27፤ ገላ5፥6፤
6፥15፤ ቈላ3፥11
7፥20 ቍ24
7፥22
ዮሐ8፥32:36፤
ሮሜ6፥22
7፥23 1ቆሮ6፥20
7፥24 ቍ20
7፥25 ቍ6፤
2ቆሮ8፥8፤
2ቆሮ4፥1፤
1ጢሞ1፥13:16
7፥26 ቍ1:8
7፥27 ቍ20:21
7፥28 ቍ36
7፥29 ቍ31፤
ሮሜ13፥11:12
7፥31 ቍ29፤
ዕብ12፥27
7፥32 1ጢሞ5፥5
7፥34 ሉቃ2፥37
7፥35 መዝ86፥11
7፥36 ቍ28
7፥38 ዕብ13፥4
7፥39 ሮሜ7፥2:3፤
2ቆሮ6፥14

ዘመኑ ዐጭር ነው፤ ከእንግዲህ ሚስት ያላ
ቸው እንደሌላቸው ሆነው ይኑሩ። [30]የሚያ
ለቅሱ እንደማያለቅሱ፣ ደስተኞች ደስ
እንደማይላቸው ይሁኑ፤ ዕቃ የሚገዙም
የገዙት ነገር የእነርሱ እንዳልሆነ ይቍጠሩ፤
[31]በዚህ ዓለም ነገር የሚጠቀሙም እንደ
ማይጠቀሙበት ይሁኑ፤ የዚህ ዓለም መልክ
ዐላፊ ነውና።
[32]እኔስ ያለ ሥጋት እንድትኖሩ
እወዳለሁ። ያላገባ ሰው ጌታን ደስ ለማሰኘት
ስለ ጌታ ነገር ያስባል፤ [33]ያገባ ሰው ግን ሚስቱን
ደስ ለማሰኘት የዚህን ዓለም ነገር ያስባል፤
[34]በዚህም ልቡ ተከፍሎአል። ያላገባች ሴት
ወይም ድንግል ስለ ጌታ ነገር ታስባለች፤
ዐላማዋም በሥጋና በመንፈስ ለጌታ መቀደስ
ነው። ያገባች ሴት ግን ባሏን ደስ ለማሰኘት
የዚህን ዓለም ነገር ታስባለች። [35]ይህንም
የምለው ለእናንተ የሚበጃችሁን ነገር በማ
ሰብ እንጂ ላስጨንቃችሁ አይደለም፤
ዐላማዬም ልባችሁ ሳይከፈል በጌታ
ጸንታችሁ በአግባብ እንድትኖሩ ነው።
[36]አንድ ሰው ያጫትን ድንግል በአግባቡ
ካልያዘ፣ እርሷም በዕድሜ እየገፋች ከሄደች፣
ሊያገባት ካሰበ የወደደውን ያድርግ፤
ኀጢአት የለበትምና ይጋቡ*። [37]ነገር ግን
በዚህ ጕዳይ ልቡን አረጋግቶ፣ ሳይገደድ ወጥ፣
ራሱንም በመግዛት ድንግሊቱን ላለማግባት
የወሰነ ሰው መልካም አድርጎአል። [38]ስለዚህ
ድንግሊቱን ያገባ መልካም አደረገ፤ ያላገባም
የተሻለ አደረገ*።
[39]አንዲት ሴት ባሏ በሕይወት እስካለ
ድረስ ከእርሱ ጋር የታሰረች ናት፤ ባሏ

*7፥36-38 ወይም አንድ ሰው ድንግል የሆነችውን ልጁን በሚገባ እንዳልያዛት ካሰበና እርስዋም በዕድሜ እየገፋች ከሄደች፣ ማግባት እንዳለባት ካሰበ የወደደውን ያድርግ፤ ኀጢአት የለበትምና እንድታገባ ሊፈቅድላት ይገባል። [38]ስለዚህ ድንግል የሆነችውን ልጁ ለጋብቻ የሰጠ መልካም አደረገ፤ ለጋብቻ ያልሰጣትም የተሻለ አደረገ።

ወይም የሚፈታበት ሁኔታ ሲከሠት፣ የጋብቻ ግንኙነቱ ይፈርሳል፤ አማኙም ከጋብቻ ግዴታው በመላቀቅ ነጻ ይሆናል። “በዚህ ሁኔታ የታሰሩ አይደሉም” የሚለው ቃል አማኙ ከጋብቻው ውል ነጻ ወጥቶአል ማለት ነው። “የታሰሩ” (ግሪክ፡ “ዶኡሎ”) ማለት ቃል በቃል ሲተረጐም “ባሪያ የሆኑ” ማለት ነው፤ ስለዚህ ለትዳሩ ታማኝ የነበረው አማኝ ከእንግዲህ በጋብቻው ጊዜ ለገባው ቃለ መሐላ እስረኛ አይሆንም። በእንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ የተፈታው አማኝ ከሌላ ክርስቲያን ጋር ጋብቻን እንደ ገና ሊመሠርት ይችላል (ቍ 39፤ በማቴ 19፥9 ስለ ፍቺ የተሰጠውን ማብ ይመ)።

**7፥19 የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸሙ፤** ድነት በእምነት እንደሚገኝ አጥብቆ የሚናገረው ጳውሎስ (ሮሜ 3—4)፣ እንዴት ዋናው ነገር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ነው ይላል? ይህንን ያለው በእምነት የሚገኘው ድነት እግዚአብሔርን ወደ መታዘዝ፣ መውደድና ማገልገል መምራት ስላለበት ነው። ከመታዘዝ የጐደለ ማንኛውም ነገር በአዲስ ኪዳን ለተገለጠው ወደ ድነት ለሚያደርሰው እምነት የሚያበቃ አይሆንም (ከገላ 5፥6፤ 6፥15 ጋር ያነጻጽሩ)።

**7፥31 በዚህ ዓለም ነገር የሚጠቀሙም፤** የዓለም ነገሮች ሁሉ ወደ ፍጻሜ በሚፋጠኑበት ዘመን እንኖራለን፤ ከዚህም የተነሣ በዚህ ዓለም ያለው ሕይወት ትልቁ ትኩረታችን ሊሆን አይገባም፤ ትልቁ ትኩረታችን ወደ ሰማያዊ ቤታችን ለመግባት መሆን አለበት (ከዕብ 11፥13-16 ጋር ያነጻጽሩ)።

**7፥34 ያላገባች ሴት፤** መጽሐፍ ቅዱስ አለማግባት በምንም ዐይነት መንገድ ከማግባት ያነሠ ሁኔታ መሆኑን አይገልጽም። በእርግጥ ባልተከፈለ ልብ እግዚአብሔርን ለማገልገል አለማግባት ከሁሉ የተሻለ ነው። ያላገባ ሰው (ቍ 32-33) ወይም ያላገባች ሴት (ቍ 34) ካገቡት ይልቅ በእግዚአብሔር ነገር ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይችላል። “በሥጋና በመንፈስ ለጌታ መቀደስ” ማለት ሥነ ምግባራዊ ብቃትን የሚያመለክት አይደለም፤ ነገር ግን ከቤተሰብ ኀላፊነት፣ ከችግርና ከሌሎች ጕዳዮች ጫና ነጻ በመሆን ለእግዚአብሔር በበለጠ የመሰጠት ሁኔታን የሚያመለክት ነው። ያላገቡ ሰዎች ከሌላው ነገር ነጻ በመሆን ራሳቸውን ከስጦታዎቻቸው ሁሉ ጋር ለእግዚአብሔር በመስጠት ሙሉ በሙሉ በጌታና በቃሉ ጕዳይ ላይ ብቻ ማተኮር ይችላሉ።

ቢሞት ግን፣ የፈለገችውን ሰው ለማግባት
ነጻነት አላት፤ ሰውየው ግን በጌታ መሆን
አለበት። [40]እንደ እኔ ከሆነ ግን ሳታገባ
እንዲሁ ብትኖር ይበልጥ ደስተኛ ትሆናለች፤
እኔም ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ
ያለ ይመስለኛል።

## ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ

8 ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ ደግሞ ይህን
እላለሁ፤ ሁላችንም ዕውቀት እንዳለን
እናውቃለን[a]። ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር
ግን ያንጻል። [2]ዐውቃለሁ የሚል ሰው፣
ማወቅ የሚገባውን ያህል ገና አላወቀም።
[3]እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ግን በእግዚአብሔር
ዘንድ የታወቀ ነው።
[4]እንግዲህ፣ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ስለ
መብላት እንዲህ እላለሁ፤ በዚህ ዓለም ጣዖት
ከንቱ እንደሆነና ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር
ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን። [5]መቼም
ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ በሰማይም
ሆነ በምድር አምላክ ተብለው የሚጠሩ
አማልክት ቢኖሩም፤ [6]ለእኛ ግን ሁሉም ነገር
ከእርሱ የሆነ፣ እኛም ለእርሱ የሆን አንድ
አምላክአብአለን፤ደግሞምሁሉምነገርበእርሱ
አማካይነት የሆነ፣ እኛም በእርሱ አማካይነት
የሆን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።
[7]ነገር ግን ይህን የሚያውቁ ሁሉም
አይደሉም፤ አንዳንድ ሰዎች እስከ አሁን
ድረስ ጣዖትን ማምለክ ስለ ለመዱ፣ እንዲህ
ያለውን ሥጋ ሲበሉ በርግጥ ለጣዖት እንደ
ተሠዋ ያስባሉ፤ ኅሊናቸውም ደካማ ስለሆነ
ይረክሳል። [8]ነገር ግን ምግብ ወደ እግዚአብሔር
አያቀርበንም፤ ባንበላ የሚጐድልብን

7፥40 ቍ25
8፥1 ቍ4፡7፡10፤
ሐሥ15፥20፤
ሮሜ15፥14
8፥2 1ቆሮ3፥18፤
13፥8፡9፡12፤
1ጢሞ 6፥4
8፥3 ኤር1፥5፤
ሮሜ8፥29፤ ገላ4፥9
8፥4 ቍ1፡6፡7፡10፤
ዘፀ34፥15፤
ዘዳ6፥4፤
መዝ86፥10፤
ሐሥ14፥15፤
1ቆሮ10፥19፤
ገላ4፥8፤ ኤፌ4፥6፤
1ጢሞ2፥5
8፥5 2ተሰ2፥4
8፥6 ቍ4፤
ሚል2፥10፤
ዮሐ1፥3፤
ሮሜ11፥36፤
ኤፌ4፥5
8፥7 ቍ1፤
ሮሜ14፥14፤
1ቆሮ10፥28
8፥8 ሮሜ14፥17
8፥9 ሮሜ14፥1፤
2ቆሮ6፥3፤
ገላ5፥13
8፥10 ቍ1፡4፡7
8፥11
ሮሜ14፥15፡20
8፥12 ማቴ18፥6፤
25፥40፡45
8፥13 ማቴ5፥29
9፥1 ቍ19፤
1ቆሮ1፥1፤ 3፥6፤
4፥15፤ 15፥8፤
2ቆሮ12፥12
9፥2 2ቆሮ3፥2፡3

ነገር የለም፤ ብንበላም የምናተርፈው ነገር
አይኖርም።
[9]ነገር ግን ከነጻነታችሁ የተነሣ
የምታደርጉት ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆን
ተጠንቀቁ። [10]አንተ ይህን የመሰለ ዕውቀት
ኖሮህ፣ ደካማ ኅሊና ያለው ሰው በቤተ
ጣዖት ስትበላ ቢያይህ፣ ለጣዖት የተሠዋውን
ምግብ ለመብላት አይደፋፈርምን? [11]ስለዚህ
ክርስቶስ የሞተለት ይህ ደካማ ወንድም
በአንተ ዕውቀት ምክንያት ጠፋ ማለት ነው።
[12]በዚህ መንገድ ወንድሞቻችሁን በመበደልና
ደካማ ኅሊናቸውን በማቍሰል፣ ክርስቶስን
ትበድላላችሁ። [13]ስለዚህ እኔ የምበላው ነገር
ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፣ ወንድሜን
ላለማሰናከል ስል ከቶ ሥጋ አልበላም።

## የሐዋርያ መብት

9 እኔ ነጻ ሰው አይደለሁምን? ሐዋርያስ
አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስን
አላየሁትምን? እናንተስ በጌታ የድካሜ
ፍሬዎች አይደላችሁምን? [2]ለሌሎች
ሐዋርያ ባልሆን እንኳ ለእናንተ ግን
በርግጥ ሐዋርያ ነኝ፤ ምክንያቱም በጌታ
የሐዋርያነቴ ማኅተም እናንተ ናችሁ።
[3]ለሚመረምሩኝ የምሰጠው መልስ ይህ
ነው። [4]ለመሆኑ፣ የመብላትና የመጠጣት
መብት የለንምን? [5]እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት፣
እንደ ጌታ ወንድሞችና እንደ ኬፋ† ሁሉ፣

9፥4 ቍ14፤ ሐሥ18፥3 9፥5 ማቴ12፥46፤ 1ቆሮ1፥12፤
7፥7፡8

*[a]8፥1 ወይም እናንተ እንደምትሉት «ሁላችንም
እውቀት አለን»*
*†9፥5 ጴጥሮስ ማለት ነው*

8፥1 **ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ፤** የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ ገዝቶ መብላት ይገባ አይገባ እንደሆነ እንዲሁም በጣዖት ቤተ መቅደስ ውስጥ በሚደረግ ግብዣ መሳተፍን በተመለከተ ላቀረቡት ጥያቄ ጳውሎስ የሰጠው ምላሽ ከምዕራፍ 8—10 ባለው ክፍል ተጠቅሶአል (ቍ 10)። (1) ለዚህ ጉዳይ ምላሽ በመስጠት በሁሉም ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊኖሩበት የሚገባውን ዋና መርሕ ገልጾአል። ይህ መርሕ አንዳንድ አማኞችን በኀጢአት እንዲፈተኑ ሊያደርጓቸው የሚችሉትንና ወደ መንፈሳዊ መፈራረስ (ቍ 11) የሚመሯቸውን አጠያያቂ ድርጊቶች የሚመለከት ነው። መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ አማካይነት ክርስቲያኖች ሁል ጊዜ ለሌሎች አማኞች ራስን መካድ በሚጠይቅ ፍቅር ሁሉን ነገር ማከናወን እንዳለባቸው አቅጣጫን ሰጥቶአቸዋል።

(2) ራስን መካድ ማለት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ላይ ሕይወታቸውን የመሠረቱትን ቅን የሆኑ ክርስቲያኖችን ላለመጉዳት ወይም ላለማድከም የራስን ነጻነት በመወሰንና ሁሉንም አጠያያቂ ድርጊቶች ወደ ጎን በመተው መኖር ማለት ነው። ራስን የመካድ ተቃራኒው ሌሎች ራሳቸውን ወደሚጐዱበት መንገድ አታሎ በመሳብ አጠያያቂ በሆኑ ድርጊቶች ለመግባት ለራስ መብት መከራከር ነው (ከሮሜ 14፥1—15፥3፤ ከሐሥ 15፥29 ማብ፤ ከ1ቆሮ 9፥19 ማብ ጋር ያነጻጽሩ)።
8፥2 **ገና አላወቀም፤** አንዳንድ አጠያያቂ ነገሮችን ለመፈጸም መብታቸውን በራሳቸው «ዕውቀት» እና «በበሰለ መረዳታቸው» ላይ የሚመሠረቱ እንደ እውነቱ ከሆነ ማወቅ የሚገባቸውን ያህል አለማወቃቸውን ያሳያሉ። በዚህ ሕይወት ያለን ዕውቀት ምንጊዜም ቢሆን ፍጹምና ትክክለኛ አይደለም። ስለዚህ ድርጊታችን በመጀመሪያ መመሥረት ያለበት ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ሰዎች ባለን ፍቅር ላይ ነው። ፍቅር ዋና ትኩረታችን ከሆነ፣ አንድን አማኝ እንኳ የሚያሰናክልና ለዘላለም ጥፋት የሚዳርግን ማናቸውንም ዐይነት ድርጊት መፈጸምን ወይም የሚፈጽሙትን ማደፋፈርን የምንቃወም ሰዎች እንሆናለን። በፍቅር ሕግ የሚኖሩ «በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቁ» ናቸው (ቍ 3)።
8፥12 **ክርስቶስን ትበድላላችሁ፤** በመጥፎ ምሳሌነታቸው ሌላውን አማኝ ወደ ኀጢአትና ወደ መንፈሳዊ ጥፋት የሚመሩ (ቍ 11)፣ ኀጢአት የሚሠሩት በዚያ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በራሱ በክርስቶስም ላይ ነው። ትልቅ ኀጢአት ተሠርቶአል፤ ይኸውም ክርስቶስ የሞተበት ዓላማ በግል ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ ከተፈጸመ ነገር ጋር ሲነጻጸር እጅግ አነስተኛ ግምት እንደተሰጠው በማመልከቱ ነው (ማቴ 18፥7 እና ማብ ይመ)።
9፥1 **ሐዋርያስ አይደለሁምን?** ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ወንጌል ላለማደናቀፍ እንደ ሐዋርያነቱ የሚገባውን መብት እንኳ በፈቃደኝነት ወደ ጐን በመተው (ቍ 12፤ 9፥19 እና ማብ ይመ) በ8፥13 ላይ የተሰጠውን መርሕ በምሳሌነት ያሳያል (8፥1 እና ማብ ይመ)።

እኛስ አማኝ ሚስት ይዘን የመዞር መብት
የለንምን? 6ወይስ ጥሪን ግሪን መኖር
ያለብን እኔና በርናባስ ብቻ ነን?
7ለመሆኑ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚ
ያገለግል ማን ነው? ወይን ተክሎ ፍሬውን
የማይበላ ማን ነው? መንጋ እየጠበቀ የከብ
ቱን ወተት የማይጠጣ ማን ነው? 8ይህን የም
ናገረው እንደ ሰው አስተሳሰብ ነውን? የኦሪ
ትስ ሕግ ይህንኑ ይል የለምን? 9በሙሴ
ሕግ፣ "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር"
ተብሎ ተጽፎአልና። ለመሆኑ፣ እግዚአብሔርን
ያሳሰ በው የበሬ ጉዳይ ነውን?
10ይህን የተናገረው በርግጥ ስለ እኛ አይደለ
ምን? የተጻፈው በትክክል ስለ እኛ ነው፤
ዐራሹ የሚያርሰው፣ አበራዩ የሚያበራየው
ከምርቱ ድርሻ እንዳለው ተስፋ በማድረግ
ነውና። 11እኛ በእናንተ መካከል መንፈሳዊ
ዘር ዘር ተን ከሆነ ለሥጋ የሚሆን ነገር
ብናጭድ ትልቅ ነገር መሆኑ ነውን? 12ሌሎች
ይህን መብት ከእናንተ ማግኘት ከቻሉ፣ እኛ
ይበ ልጥ ማግኘት አይገባንምን? እኛ ግን
በዚህ መብት አልተጠቀምንም፤ ይልቁንም
ለክርስቶስ ወንጌል ዕንቅፋት እን ዳንሆን
ሁሉንም ነገር እንታገሣለን። 13በቤተ መቅደስ
የሚያገለግሉ ምግባቸውን ከቤተ መቅደስ
እንደሚያገኙ፣ በመሠዊያውም የሚያገ
ለግሉ ከመሥዋዕቱ እንደሚካፈሉ አታውቁ
ምን? 14እንደዚሁም ወንጌልን የሚሰብኩ
ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲ
ቀበሉ ጌታ አዞአል።
15እኔ ግን ከእነዚህ መብቶች በአንዱ
እንኳ አልተጠቀምሁም፤ አሁንም ይህን
የምጽፍላችሁ እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች
ታደርጉልኛላችሁ በሚል ተስፋ አይደለም፤
ማንም ትምክሕቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ
ሞት ይሻለኛልና። 16ወንጌልን መስበኬ አያ
ስመካኝም፤ የምሰብከው ግዴታዬ ስለ ሆነ
ነው፤ ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ።
17በፈቃደኝነት ብሰብክ ሽልማት አለኝ፤ በፈ
ቃደኝነት ካልሆነ ግን፣ የምፈጽመው ተግባር
የተጣለብኝን ዐደራ መወጣት ብቻ ይሆናል።
18ታዲያ ሽልማቴ ምንድን ነው? ሽልማቴማ
ወንጌልን ስሰብክ በመብቴ ሳልጠቀም
ወንጌልን ያለ ክፍያ መስበክ ነው።
19እኔ ነጻ ሰው ነኝ፤ የማንም ባሪያ
አይደለሁም፤ ነገር ግን ብዙዎችን እመልስ
ዘንድ ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ።
20አይሁድን እመልስ ዘንድ ከአይሁድ ጋር
እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ፤ እኔ ራሴ ከሕግ
በታች ሳልሆን፣ ከሕግ በታች ያሉትን
እመልስ ዘንድ ከሕግ በታች እንዳሉት
ሆንሁ። 21እኔ ራሴ ከእግዚአብሔር ሕግ ነጻ
ያልሆን ሁና፣ ለክርስቶስ ሕግ የምገዛ
ብሆንም፣ ሕግ የሌላቸውን እመልስ ዘንድ፣
ሕግ እንደሌለው ሰው ሆንሁ። 22ደካሞችን
እመልስ ዘንድ፣ ከደካሞች ጋር እንደ ደካማ
ሆንሁ። በሚቻለኝ ሁሉ አንዳንዶችን አድን
ዘንድ፣ ከሁሉም ጋር ሁሉን ነገር ሆንሁ።
23ይህን ሁሉ የማደርገው፣ ከወንጌል በረከት
እካፈል ዘንድ፣ ስለ ወንጌል ብዬ ነው።
24በሩጫ ውድድር የሚሮጡ ብዙዎች
እንደ ሆኑ፣ ሽልማቱን የሚቀበለው ግን
አንዱ ብቻ እንደ ሆነ አታውቁምን? ስለዚህ
ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ። 25ለውድ
ድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም
ነገር ራሱን ይገዛል፤ እነርሱ ዐላፊ ጠፊ
የሆነውን አክሊል ለማግኘት ይደክማሉ፤
እኛ ግን ለዘላለም የማይጠፋውን አክሊል
ለማግ ኘት እንደክማለን። 26ስለዚህ እኔ
ግብ እንደ ሌለው ሰው በከንቱ አልሮጥም፤
ደግሞም ነፋስን እንደሚጐስም ሰው
እንዲያው አልታገልም፤ 27ነገር ግን
ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ እኔ ራሴ ውድቅ

9፥6 ሐሥ4፥36
9፥7 ዘዳ20፥6፤ ምሳ27፥18፤ 1ቆሮ3፥6፡8፤ 2ጢሞ2፥3፡4
9፥9 ዘዳ22፥1-4፤ 25፥4፤ ምሳ12፥10፤ 1ጢሞ5፥18
9፥10 ምሳ11፥25፤ ሮሜ4፥23፡24፤ 2ጢሞ2፥6
9፥11 ቍ 14፤ ሮሜ15፥27፤ ገላ6፥6
9፥12 ቍ 15፡18፤ ሐሥ18፥3፤ 2ቆሮ6፥3፤ 11፥7-12
9፥13 ዘሌ6፥16፡26፤ ዘዳ18፥1
9፥14 1ጢሞ5፥18
9፥15 ቍ 12፡18፤ ሐሥ18፥3፤ 2ቆሮ11፥9፡10
9፥16 ሐሥ9፥15፤ 26፥16-18፤ ሮሜ1፥14
9፥17 1ቆሮ3፥8፡14፤ 4፥1፤ ገላ2፥7፤ ቈላ1፥25
9፥18 ቍ 12፡15፤ 2ቆሮ11፥7፤ 12፥13
9፥19 ቍ 1፤ ማቴ18፥15፤ 2ቆሮ4፥5፤ ገላ5፥13፤ 1ጴጥ3፥1
9፥20 ሐሥ16፥3፤ 21፥20-26፤ ሮሜ2፥12፤ 11፥24
9፥21 ሮሜ2፥12፡14፤ ገላ6፥2
9፥22 ሮሜ11፥14፤ 14፥1፤ 1ቆሮ2፥3፤ 10፥33
9፥24 ቍ 25፡26፤
9፥24 ገላ2፥2፤ 5፥7፤ ፊል 2፥16፤ 3፥14፤ ቈላ2፥18፤ 2ጢሞ4፥7፤ ዕብ12፥1 9፥25 2ጢሞ2፥5፤ 4፥8፤ ያዕ1፥12፤ 1ጴጥ5፥4፤ ራእ2፥10፤ 3፥11 9፥26 ቍ 24፤ 1ጢሞ6፥12 9፥27 ቍ 24፤ ሮሜ8፥13

**9፥14 ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ፤** ብሉይ ኪዳን (ዘዳ 25፥4፤ ከዘሌ 6፥16፡26፤ 7፥6 ጋር ያነጻጽሩ) እና አዲስ ኪዳን (ማቴ 10፥10፤ ሉቃ 10፥7) ሁለቱም የእግዚአብሔር ቃል በመስበክ ሥራ ላይ ያሉት ከአገልግሎቱ መንፈሳዊ በረከት በሚያገኙ ሰዎች መደገፍ እንዳለባቸው ያስተምራሉ (ገላ 6፥6-10 እና ማብ፤ 1ጢሞ 5፥18 ይመ)።

**9፥19 ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን ስለ ሌሎች ሲል ራስን የመካድ መርሕ ምሳሌ አድርጎ አቅርቦአል (8፥1 እና ማብ ይመ)። አገልግሎቱንና ወንጌልን ላለማደናቀፍ ሲል (ቍ 12) ሌሎች ይለወጡ ዘንድ ርኅራኄ ከማድረጉ የተነሣ የግል መብቱን በፈቃዱ ተወ (ሮሜ 14፥15-21)። ይህ ማለት ጳውሎስ የሌሎችን ሐሳብ ወደ ራሱ የመሳብ ዐላማን ይዞ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ክርስቲያናዊ መርሖችን ጣለ ማለት አይደለም (ገላ 1፥8-10)። እርሱ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር ክርስቲያናዊ መርሖች ሳይጣሉ እየረዳቸው ካሉት ሰዎች ሐሳብ ጋር ራሱን ለማስማማት የተዘጋጀ እንደ ሆነ ነው። ኀሊናቸው የተቀበለውን እምነት ችላ ብሎ ቢያስቈጣቸው፣ ስለ ክርስቶስ ሲል የሚሰጣቸውም አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ ዕንቅፋት ሊያጋጥመው እንደሚችል ተረድቶአል (ቍ 12፡19-23፤ 8፥1 እና ማብ ይመ)።

**9፥24 ሽልማቱን፤** "ሽልማት" ይኸውም "ለዘላለም የማይጠፋው አክሊል" (ቍ 25) የሚያመለክተው የክርስትና ሕይወት የከበረ ግብ የሆነውን የዘላለም ድነት ማሸነፍ ነው (ከ1፥8፤ 4፥5፤ 6፥2፡9-10፤ 15፥12-19 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ግብ ሊፈጸም የሚችለው ስለሌሎች ስንል አንዳንዱን መብታችንን አሳልፈን ስንሰጥ (8፥7-13) እና ከእሽቅድምድም ውጪ የሚያደርጉንን ነገሮች በሙሉ ስንቃወም ብቻ ነው (10፥5-22)።

**9፥24 ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ፤** ራስን መግዛትን፣ ራስን መካድንና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ፍቅርን መግለጽ ባንችል እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንደማናገኝ የሚያመለክትን መርሕ ሐዋርያው ጳውሎስ ሥዕላዊ በሆነ መንገድ ገልጾልናል (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

**9፥27 እኔ ራሴ ውድቅ ሆኜ እንዳልቀር፤** "ውድቅ ሆኜ እንዳልቀር" (ግሪክ፡ "አዶኪሞስ") የሚለው ቃል "ፈተናውን መውደቅ" ወይም "ተቀባይነትን

ሆኜ እንዳልቀር፣ ሰውነቴን እየጐሰምሁ
እንዲገዛልኝ አደርገዋለሁ።

## በእስራኤል የደረሰው እንዳይደርስብን እንጠንቀቅ

10 ወንድሞች ሆይ፤ አባቶቻችን ሁሉ
ከደመናው በታች እንደ ነበሩና
በባሕሩ ውስጥ እንደ ተሻገሩ ታውቁ ዘንድ
እፈልጋለሁ። 2እነርሱ ሁሉ ከሙሴ ጋር
ለመተባበር በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤
3ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ ምግብ በሉ፤
4ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤
ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዐለት ጠጥ
ተዋልና፤ ያ ዐለት ክርስቶስ ነበረ። 5ይሁን
እንጂ እግዚአብሔር በብዙዎቹ ደስ ስላልተሰኘ
በበረሓ ወድቀው ቀሩ።
6እነርሱ ክፉ እንደ ተመኙ፣ እኛም
ደግሞ እንዳንመኝ እነዚህ ነገሮች ምሳሌ
ሆነውልናል። 7"ሕዝቡ ሊበሉና ሊጠጡ
ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ" ተብሎ እንደ
ተጻፈ፣ ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት
ጣዖት አምላኪዎች አትሁኑ። 8ከእነርሱ
አንዳንዶቹ ዝሙት ፈጽመው በአንድ ቀን
ሃያ ሦስት ሺህ ሰው እንደ ረገፈ፣ እኛም
ዝሙት አን ፈጽም። 9ከእነርሱ አንዳንዶቹ
ጌታን እንደ ተፈታተኑና በእባብ ተነድፈው
እንደ ጠፉ፣ እኛም ጌታን አንፈታተን።
10ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳጕረመረሙና
በአጥፊው እንደ ጠፉ፣ አታጕረምርሙ።
11ይህ ሁሉ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በእነርሱ ላይ
ደረሰ፤ የዘመናት ፍጻሜ የደረሰብንን እኛን
ለማስጠንቀቅም ተጻፈ። 12ስለዚህ ተደላድዬ
ቆሜአለሁ የሚል ቢኖር እንዳይወድቅ ይጠን
ቀቅ። 13በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ
ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ

10፥1 ዘፀ13፥21፤ 14፥22፡29፤ መዝ66፥6፤ 105፥39፤ ሮሜ11፥25
10፥2 ሮሜ6፥3
10፥3 ዮሐ6፥31
10፥4 ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥11፤ መዝ78፥15፤ 105፥41
10፥5 ዘኍ14፥29፤ ዕብ3፥17፤ ይሁ1፥5
10፥6 ቍ11
10፥7 ቍ14፤ ዘፀ32፥4፡6፡19
10፥8 ዘኍ25፥1-9
10፥9 ዘፀ17፥2፤ ዘኍ21፥5፡6፤ መዝ78፥18፤ 95፥9፤ 106፥14
10፥10 ዘፀ12፥23፤ ዘኍ16፥41፡49፤ 17፥5፡10፤
10፥10 1ዜና21፥15፤ ዕብ11፥28 10፥11 ቍ6፤ ሮሜ4፥24፤ 13፥11 10፥12 ሮሜ11፥20፤ 2ቆሮ1፥24
10፥13 1ቆሮ1፥9፤ 2ጴጥ2፥9

ማጣት» የሚለውን ሐሳብ ይገልጻል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ 13፥5 ላይ ፈተናውን በወደቀ ሰው (ግሪክ፡ "አዶኪሞይ") ላይ ክርስቶስ እንደማይኖር ሲገለጽ ይህንኑ ተመሳሳይ ቃል ጠቅሶአል:: ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው የአገልግሎት ሽልማትን ስለማጣት ጉዳይ ብቻ አይደለም:: እየገለጸ ያለው አንድ ሰው የቅድስና ሕይወት መኖርን፣ ራስን መግዛት መለማመድንና ስለ ክርስቶስም በመከራ መጽናትን (ቊ 25-27) ቢያቆም የዘላለም ድነት ሽልማትን (ቊ 24-25) ማለትም የዘላለም ርስቱን ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታ እንደሚኖር ነው::

**10፥1 ታውቁ ዘንድ እፈልጋለሁ፤** አንድ ሰው ቤዛነትን አግኝቶና የመለኮታዊ ጸጋ ተካፋይ ሆኖ ነገር ግን በኋላ በኀጢአት ከመጠመዱ የተነሣ (9፥27 እና ማብ ይመ) በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ሊያጣ እንደሚችል አሁን በእስራኤላውያን ሕይወት በታየው ምሳሌ ተገልጾአል (ቊ 1-12)::

**10፥5 በበረሓ ወድቀው ቀሩ፤** እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር ሲወጡ የእግዚአብሔርን ጸጋ በሕይወታቸው አይተዋል:: ከባርነት ነጻ ወጥተዋል (ቊ 1)፤ ተጠምቀዋል (ቊ 2)፤ ከክርስቶስ ጋር የቀረበ ኅብረት በማድረግም በምድረበዳ በመለኮታዊ ኀይል ተጠብቀዋል (ቊ 3-4):: ነገር ግን እነዚህን መንፈሳዊ በረከቶች ቢያገኙም እንኳ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አልቻሉም፤ ስለዚህም በምድረ በዳ በእርሱ ጠፉ:: በእግዚአብሔር የመመረጣቸውን መብት አጡ፤ ከዚህም የተነሣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊገቡ አልቻሉም (ከዘኍ 14፥30 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 321 ላይ፣ "*እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ኪዳን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: የሐዋርያው ጳውሎስ ዋና ነጥብ የሚከተለው ነው፤ እግዚአብሔር የእስራኤልን ባዕድ አምልኮ፣ ኀጢአትና ኢግብረገባዊነት መታገሥ እንዳልቻለ ሁሉ፣ በአዲስ ኪዳን ያሉ አማኞችንም ኀጢአት እንዲሁ መታገሥ አይችልም::

**10፥6 እነዚህ ነገሮች ምሳሌ ሆነውልናል፤** ዐመፀኞች በሆኑት እስራኤላውያን ላይ እግዚአብሔር የሰጠው ከባድ ፍርድ በአዲስ ኪዳን ያሉት ክፉን ነገር እንዳይመኙ በምሳሌነትና በማስጠንቀቂያነት ያገለግላል:: የቆሮንቶስ ሰዎች እስራኤላውያን እንዳደረጉት ታማኝ ሳይሆኑ ቢቀሩ (ቊ 7-10) እነርሱም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላሉ፤ በተስፋ ወደምትጠበቀው ሰማያዊ አገርም እንዳይገቡ ይደረጋሉ::

**10፥11 እኛን ለማስጠንቀቅም ተጻፈ፤** በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የፈረደው የፍርድ ታሪክ የተጻፈበት ምክንያት በአዲስ ኪዳን ያሉት በኀጢአትና ከጸጋ በመውደቅ ሳቢያ እንዳይጐዱ በቂ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ነው::

**10፥12 እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፤** እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ምርጥ በመሆናቸው ያለምንም ሥጋት በኀጢአት፣ በባዕድ አምልኮና በኢግብረገባዊነት ውስጥ መንቦራጨቅ እንደሚችሉ ያስቡ ነበር፤ ነገር ግን በፍርድ ፊት ወደቁ:: ስለዚህ ያለምንም ሥጋት ዓለም በምትሰጠው ደስታ ውስጥ መኖር ይቻላል ብለው የሚያምኑ፣ ፍርድ እንዲሚጠብቃቸው ሊያውቁ ይገባል::

**10፥13 እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤** እውነተኛ አማኞች ሰው ስለሆኑና ፍጹማን ስላልሆኑ ወይም በዚህ ዓለም ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች በቃል፣ በሐሳብና በድርጊት ኀጢአትን በመሥራት ሊኖሩ ይችላሉ በሚል አስተሳሰብ ኀጢአት ማድረግን በይቅርታ ሳያልፉት ይችላሉ (ከሮሜ 6፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: በተመሳሳይ ሁኔታም ሐዋርያው ጳውሎስ እውነተኛ አማኝ ከእግዚአብሔር ጸጋ መውደቅ እንደሌለበት ለቆሮንቶስ ሰዎች በማስረገጥ ተናግሮአል::

(1) እግዚአብሔር ለልጆቹ ማንኛውንም ፈተና ሊያሸንፉ የሚያስችላቸውን በቂ ጸጋ እንደሚሰጣቸውና ኀጢአትንም መቃወም እንደሚችሉ (ከራእ 2፥7፡17፡26 ጋር ያነጻጽሩ) መንፈስ ቅዱስ በግልጽ በማረጋገጥ ተናግሮአል:: እግዚአብሔር ታማኝነቱን በሚከተሉት ሁለት መንገዶች ገልጾአል፤ (ሀ) እግዚአብሔር ልንሸከመው ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አይፈቅድም፤ (ለ) ከፈተናውም ጋር የፈተናውን መውጫና ኀጢአትን የምናሸንፍበትን መንገድ እግዚአብሔር ይሰጠናል (ከ2ተሰ 3፥3 ጋር ያነጻጸሩ)::

(2) የእግዚአብሔር ጸጋ (ኤፌ 2፥8-10፤ ቲቶ 2፥11-14)፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም (ኤፌ 2፥13፤ 1ጴጥ 2፥24)፣ የእግዚአብሔር ቃል (ኤፌ 6፥17፤ 2ጢሞ 3፥16-17)፣ በውስጥ የሚያድረው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል (ቲቶ 3፥5-6፤ 1ጴጥ 1፥5) እና ክርስቶስ በሰማይ

ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ
አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት
ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣
መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።

## ከጣዖት ጋር አለመተባበር

[14]ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፤ ከጣዖት አምልኮ
ሽሹ። [15]ይህን የምናገረው አስተዋይ ለሆኑ
ሰዎች ነው፤ ስለምናገረው ነገር እናንተው
ፍረዱ። [16]የምንባርከው የበረከት ጽዋ
ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው
አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ
ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው
አይደለምን? [17]እን ጀራው አንድ እንደ ሆነ፣
እኛም ብዙዎች ሆነን ሳለ አንድ አካል ነን፤
ሁላችን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።
[18]እስቲ የእስራኤልን ሕዝብ አስቡ፤
መሥዋዕቱን የሚበሉት ከመሠዊያው ጋር
ኅብረት አልነበራቸውምን? [19]ታዲያ፣ ለጣዖት
የተሠዋ ነገርም ሆነ ጣዖቱ ራሱ ዋጋ ያለው
ነገር ነው ማለቴ ነውን? [20]አይደለም፤ አሕዛብ
የሚሠዉት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋንንት
ነው፤ ከአጋንንት ጋር እንድትተባበሩም
አልሻም። [21]**የጌታን** ጽዋና፣ የአጋንንትን
ጽዋ በአንድ ላይ መጠጣት አትችሉም፤
**ከጌታ** ማእድና ከአጋንንት ማእድ ተካፋይ
መሆን አትችሉም። [22]**ጌታን** እናስቀናውን?
በብርታትስ ከእርሱ እንበልጣለንን?

## የአማኞች ነጻነት

[23]"ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል"፤ ነገር ግን
ሁሉም ነገር አይጠቅምም፤ "ሁሉም ነገር
ተፈቅዶአል"፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር
አያንጽም። [24]እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን
ጥቅም እንጂ የራሱን ብቻ አይፈልግ።
[25]በኀሊና ምርምር ውስጥ ሳትገቡ፣ በሥጋ
ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ብሉ፤ [26]ምድርና
በውስጧ ያለው ሁሉ **የጌታ** ነውና።
[27]የማያምን ሰው ጋብዞአችሁ ለመሄድ
ብትፈልጉ በኀሊና ምርምር ውስጥ ሳትገቡ
የቀረበላችሁን ሁሉ ብሉ። [28]ነገር ግን አንዱ፣
"ይህ ለጣዖት የተሠዋ ነው" ቢላችሁ፣ ይህን
ስለ ነገራችሁ ሰውና ለኅሊናችሁ ስትሉ
አትብሉ*። [29]ይህን የምለውም ስለዚያ ሰው
ኅሊና እንጂ ስለ ኢንተ አይደለም፤ ነጻነቴስ
በሌላ ሰው ኅሊና ለምን ይመዘን? [30]ምግቡን
በምስጋና የምበላ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን
ባመሰገንሁበት ነገር ለምን እወቀሳለሁ?
[31]እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣
ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣

10፥14 ቍ7፤ ዕብ6፥9፤ 1ጴጥ2፥11፤ 1ዮሐ2፥7፤ 5፥21፤ ይሁ1፥3
10፥16 ማቴ14፥19፤ 26፥26-28፤ 1ቆሮ11፥23-25
10፥17 ሮሜ12፥5
10፥18 ዘሌ7፥6፡14፡15
10፥19 1ቆሮ8፥4
10፥20 ዘዳ32፥17፤ መዝ106፥37፤ ራእ9፥20
10፥20 ዘሌ17፥7
10፥21 2ቆሮ6፥15፡16
10፥22 ዘዳ32፥16፡21፤ 1ነገ14፥22፤ መዝ78፥58፤ መክ6፥10፤ ኢሳ45፥9፤ ኤር44፥8
10፥23 1ቆሮ6፥12
10፥24 ቍ33፤ ሮሜ15፥1፡2፤ 1ቆሮ13፥5፤ ፊል2፥4፡21
10፥25 ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ8፥7
10፥26 ዘፀ9፥29፤ 19፥5፤ ኢዮ41፥11፤ መዝ24፥1፤ 50፥12፤ 1ጢሞ4፥4 10፥27 ሉቃ10፥7 10፥28 1ቆሮ8፥7፡10-12
10፥29 1ቆሮ9፥1፡19 10፥30 ሮሜ14፥6
10፥31 ዘካ14፥21፤ ቈላ3፥17፤ 1ጴጥ4፥11

*10፥28 አንዳንድ ቅጆች አትብሉ፤ ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ የጌታ ናትና::

የሚያደርገው ምልጃ አማኝ ከኀጢአትና ከርኩሳን መንፈሳዊ ኀይላት ጋር በሚያደርገው ውጊያ (ኤፌ 6፥10-18፤ ዕብ 7፥25) በቂ ኀይልን ያስገኙለታል::

(3) ክርስቲያኖች በኀጢአት ቢሸነፉ፣ ክርስቶስ የሰጣቸው ጸጋ በቂ ስላልሆነ አይደለም፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የራሳቸውን ኀጢአተኛ ተፈጥሮ መቃወም ስላልቻሉ ነው (ሮሜ 8፥13-14፤ ገላ 5፥16፡24፤ ያዕ 1፥13-15):: እግዚአብሔር፣ «ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል» (2ጴጥ 1፥3)፤ በክርስቶስ አማካይነት በተሰጠን ድነትም ለጌታ እንደሚገባ ልንኖርና በሁሉም ነገር ደስ ልናሰኘው እንችላለን፤ ይኸውም በመልካም ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራን፣ እግዚአብሔርን በማወቅ እያደግን፣ ታላቅ ጽናትና ትዕግሥት ይኖረን ዘንድ እንደ ክቡር ጉልበቱ መጠን በኀይል ሁሉ በመበርታት ነው (ቈላ 1፥10-11 እና ፈተናን እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል የተጠቀሰውን በማቴ 4፥1 ላይ ያለውን ማብ ይመ):: የእግዚአብሔርን ኀይል ለማግኘትና በእርሱም ታማኝነት ለመደገፍ ከሆነ፣ ማንኛውንም ፈተና መሸከምና መውጫ መንገዱንም ማግኘት እንችላለን::

**10፥16 የበረከት ጽዋ፤** በጌታ እራት ጊዜ የምንወስደው ጽዋ የክርስቶስን ሞትና እርሱም ለኀጢአተኞች ሲል በመሥዋዕትነት የተቀበለውን ሥቃይ ያመለክታል:: «ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው» የሚለው ቃል አማኝ በክርስቶስ ሞት የተገኘውን ድነት የሚካፈልበትን ሁኔታ ያመለክታል (ከ11፥25 ጋር ያነጻጽሩ):: መጽሐፍ ቅዱስ እንጀራውንና የወይኑን ፍሬ ጭማቂ እውነተኛው የክርስቶስ ሥጋና ደም ሆኖ እንደሚለወጥ አያስተምረንም (11፥24-25 እና በጌታ እራት ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)::

**10፥20 የሚሠዉት ... ለአጋንንት፤** ባዕድ አምልኮ አጋንንት ማምለክንም ይጨምራል (ከዘዳ 32፥17፤ ከመዝ 106፥35-38 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 428 ላይ፣ «*የጣዖት አምልኮ ባሕርይ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ እንዲሁም ከክፉ ምኞት ወይም ከመጐምጀት ጋር የተያያዘ ነው:: ስለዚህ የአጋንንት ኀይላት ዓለማዊ ብልጥግናን፣ ክብርን ወይም ሥልጣንን ከመውደድ ጀርባ የሚሠሩ ናቸው::

**10፥21 የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ፤** የጌታን እራት መካፈል ክርስቶስ በሚሰጠው ቤዛነት መካፈል እንደሆነ ሁሉ፣ በባዕድ አምልኮ ግብዣዎችም ውስጥ መሳተፍ ከአጋንንት ጋር መካፈል ነው (ቍ 20):: በቆሮንቶስ ባሉት በአንዳንዶቹ ዘንድ ችግር የሆነው በጽድቅና በርኵሰት፣ ቅዱስ በሆነውና በረከሰው፣ የክርስቶስ በሆነውና የአጋንንት በሆነው መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ያለማወቅ ነው:: የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቅንአትና (ቍ 22 ይመ፤ ከዘፀ 20፥5፤ ከዘዳ 4፥24፤ ከኢሱ 24፥19 ጋር ያነጻጽሩ) ከዓለም ጋር መተባበር የሚያመጣውን ከባድ ቅጣት ገና ዐላወቁም:: ክርስቶስ ራሱ ይህን አደገኛ ስህተት በሚመለከት፣ «አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም» (ማቴ 6፥24) ብሎአል::

**10፥31 ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት፤** የአማኝ ሕይወት ዋና ዐላማ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ ነው (በገጽ 1205 ላይ፣ «*የእግዚአብሔር ክብር*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ክብር ሲባል የማይደረግ ነገር ሁሉ ማለትም ለጌታችን፣ ለፈጣሪያችንና ለቤዛችን ክብርና ምስጋና የማይውል ማንኛውም ነገር ፈጽሞ ሊሠራ አይገባም:: እግዚአብሔርን ማክበር የምንችለው በመታዘዝ፣ ምስጋናን በማቅረብ፣ በእርሱ በመደገፍ፣

ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።
[32]ለአይሁድም ሆነ ለግሪኮች ወይም
ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መሰናክል
አትሁኑ፤ [33]እኔ ሰውን ሁሉ በማንኛውም
ረገድ ለማስደሰት እንደምጥር እናንተም
እንዲሁ አድርጉ፤ ብዙዎችም ይድኑ ዘንድ፣
ለራሴ የሚጠቅመውን ሳይሆን፣ ለእነርሱ
የሚጠቅመውን እሻለሁና።

11 እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል
እናንተም የእኔን ተከተሉ።

10፥32 ማቴ5፥29፤ ሐሥ20፥28፤ 24፥16፤ 1ቆሮ1፥2፤ 11፥16፡22፤ 15፥9፤ 2ቆሮ6፥3፤ 1ጢሞ3፥5፡15
10፥33 ቍ 24፤ ሮሜ11፥14፤ 15፥2፤ 1ቆሮ9፥22
11፥1 ሮሜ15፥3፤ 1ቆሮ4፥16፤ 1ጴጥ2፥21

## ሥርዐት ያለው አምልኮ

[2]በሁሉም ነገር ስለምታስቡልኝና ከእኔ
የተቀበላችሁትን ትምህርት[a] አጥብቃችሁ
ስለ ያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ።
[3]ነገር ግን ይህን እንድታውቁ እወዳለሁ፤
የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው፤ የሴትም
ራስ ወንድ ነው፤ የክርስቶስም ራስ

11፥2 ቍ 17፡22፡23፤ 1ቆሮ4፥17፤ 15፥2፡3፤ 2ተሰ2፥15፤ 3፥6 11፥3 ዘፍ3፥16፤ 1ቆሮ3፥23፤ ኤፌ1፥22፤ 5፥23

[a] 11፥2 ወይም ወግ

በጸሎት፣ በእምነትና በታማኝነት ነው። "ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት" የሚለው ትእዛዝ የሕይወታችን የመጀመሪያ አቅጣጫ፣ የባሕርያችን መምሪያና የድርጊታችን መመዘኛ መሆን አለበት።

**11፥1 የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል፤** እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ያለ አማኝ የክርስቶስን ምሳሌ እንዲከተልና ክርስቶስን እንዲመስል ተጠርቶአል (ከሮሜ 13፥14፤ ከገላ 3፥27 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስን መምሰል ምንድነው?

(1) ክርስቶስን መምሰል ማለት ከሁሉም በፊት እግዚአብሔርንና ሌሎችን መውደድ ነው (ማቴ 22፥37-39፤ ሉቃ 10፥27)። አማኝ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ሌሎችን እንዲወድ ያነሣሣዋል እንዲሁም ይመራዋል (1ዮሐ 4፥20-21)፤ ይህም ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር የመጀመሪያው እንደ ሆነ እንዲሁም ለሌሎች ያለውም ፍቅር ከዚህኛው በታች እንደ ሆነና ለአብም ባለው ፍቅር ላይ እንደ ተመሠረተ ነው (ከማቴ 22፥37-39፤ ከዮሐ 17፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ክርስቶስ ለአባቱ ያለው ፍቅር የተገለጠው ለእግዚአብሔር ክብር (ማቴ 6፥9፤ ዮሐ 12፥28፤ 17፥4)፣ ፈቃድ (ማቴ 26፥42፤ ዮሐ 4፥34፤ ዕብ 10፥7-12)፣ ቃል (ማቴ 26፥54፤ ዮሐ 8፥28፤ 17፥14፡17)፣ ህልዎት ቅርብ መሆን (ሉቃ 5፥16፤ ዮሐ 17፥21) በነበረው ግድ መሰኘት ነው። ይህን ፍቅሩን ያየነው ለእግዚአብሔር ባለው ታማኝነት (ዕብ 3፥2) እና እኛን ለመቤዠት ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎ በመስጠት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በገለጠው ፈቃደኝነቱ ነው (ማቴ 26፥42፤ ዮሐ 3፥16-17፤ ዕብ 10፥4-9)። በተጨማሪም ክርስቶስ ለአባቱ ያለውን ፍቅር የገለጸው ጽድቅን በመውደዱና ኀጢአትን በመጥላቱ ነው (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)።

(3) ክርስቶስ ለሰዎች ያለው ፍቅር የተገለጸው በርኅራኄው (ማቴ 9፥36፤ 14፥14፤ 15፥32፤ 20፥34፤ ከሉቃ 15፥11-24 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በቸርነቱ (ማቴ 8፥3፡16-17፤ 9፥22)፣ በእንባው (ዮሐ 11፥35)፣ በትሕትናው (ማቴ 11፥29)፣ በበጎ ሥራው (ሐሥ 10፥38)፣ በገርነቱ (ማቴ 11፥29)፣ በይቅር ባይነቱ (ሉቃ 23፥34)፣ በትዕግሥቱ (ሉቃ 13፥34) እና በምሕረቱ (ማቴ 15፥22-28፤ ይሁ 1፥21) ነው። እንደዚሁም ኀጢአትን በገሠጸበት ጊዜ (ማቴ 16፥23፤ ማር 9፥19፤ 10፥13-14)፤ ጨካኞች በሆኑት፣ ስለ ሌሎች ሥቃይ ወይም ፍላጎት ግድ በሌላቸው ወይም ልበ ቢሶች በሆኑትም ላይ ቍጣውን ሲገልጽ (ማር 3፥5 እና ማብ ይመ)፤ ስለ ገሃነም ባስጠነቀቀን ጊዜና (ማቴ 5፥29-30፤ ሉቃ 12፥5)፤ ራሱንም መሥዋዕት አድርጎ ሲያቀርብ (ማቴ 26፥38፤ ዮሐ 10፥11፡17-18፤ 13፥1) ፍቅሩን አሳይቶአል ።

**11፥2 ትምህርት፤** ትምህርቶች የተባሉት ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ሥልጣን ለአብያተ ክርስቲያናት ያስተላለፋቸው ከአስተምህሮ፣ ከግብረገባዊ መለኪያዎችና ከጠባይ ሕጎች ጋር የተያያዙ መመሪያዎች ናቸው። በምዕራፍ 11 ላይ የተጠቀሱት መመሪያዎች ውጫዊ አለባበስን፣ ልከኝነትን፣ መልክንና ተገቢ የሆነውን ጠባይ በተመለከተ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው የፈቃዱ ዝርዝር እንደሆነ ልብ ይበሉ። እግዚአብሔር የሚያተኩረው በውስጣዊ የሕይወት ለውጥ ላይ ብቻ እንጂ "በውጫዊ" ሁኔታ ላይ አይደለም ብሎ ማስተማር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከተጠቀሰው ከእግዚአብሔር ግልጽ እውነት መራቅ ይሆናል። በመጠንና ራስን በመግዛት የሚደረግ ተገቢ አለባበስ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ውስጥ በዘላቂነት የሚጠቀስ ተቀባይነት ያለው ትምህርት ነው (1ጢሞ 2፥9 እና ማብ)።

**11፥3 የወንድ ሁሉ ራስ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በወንድና በሴት መካከል ሊኖር በሚገባ ትክክለኛ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርጓል፤ ይህ ግንኙነት በእግዚአብሔር የተሰጠ ስለሆነ በሚገባ መያዝ እንዳለበትም መሻቱን ገልጾአል። (1) ወንድና ሴት የእግዚአብሔር ጸጋ ወራሽ እንደመሆናቸው መጠን በክርስቶስ ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ እኩልነት እንዳላቸው በአጽንዖት ጠቅሶአል፤ ነገር ግን ሥልጣንን በተመለከተ የበላይና የበታች መሆን ስላለ፣ ይህ እኩልነት ይህን ሥርዐት ያካተተ ነው (ገላ 3፥28 እና ማብ ይመ)። እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ እንደሆነ ሁሉ፣ ክርስቶስ የወንድ ራስ ነው፤ ወንድም የሴት ራስ ነው። "ራስ" የሚለው ቃል ሥልጣንንና መለኮታዊ ሥርዐትን የሚያመለክት ነው (ከ3፥23፤ 11፥8፡10፤ 15፥28፤ ከመሳ 10፥18፤ ከኤፌ 1፥21-22፤ 5፥23-24፤ ከቈላ 1፥18፤ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ሐዋርያው ጳውሎስ የወንድን ራስነት ለመግለጽ መሠረት ያደረገው ባሕላዊ ጕዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት አይደለም፤ ነገር ግን ሴት የወንድ ረዳት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር እርሷን ከፈጠረበት ከመፍጠር ሥራውና ዐላማው አንጻር ነው (ቍ 8-9፤ ዘፍ 2፥18 እና ማብ፤ 1ጢሞ 2፥13 እና ማብ ይመ)።

(3) ከሥልጣን አንጻር የበታች መሆን ማለት የራስን ማንነት ማቃለል ማለት አይደለም፤ መጨቈንን ወይም መረገጥን አያመለክትምና። ይልቁንስ ባል በሚስቱ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን ከፍተኛ ዋጋ በመረዳት በቤትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትፈጽመው ዘንድ እግዚአብሔር በሕይወቷ ያስቀመጠውን ዐላማ እንድታከናውን መንገድን እያመቻቸ በመንከባከብና በመምራት የተሰጠውን ኀላፊነት እንዲወጣ ያሳስባል።

(4) አባቱ ራስ ከመሆኑ የተነሣ ክርስቶስ የበታች ወይም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ እንዳልሆነ ሁሉ፣ ወንድ የሴት ራስ ከመሆኑ የተነሣ ሴትም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለች አይደለችም። ከዚህም በላይ መሪነት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ፈጽሞ "ታላቅ" መሆንን አያመለክትም። አገልጋይነትና ታዛዥነት በእግዚአብሔር

እግዚአብሔር ነው። 4ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ
ወይም ትንቢት የሚናገር ማንኛውም ወንድ
የእርሱን ራስ ያዋርዳል፤ 5ራሷን ሳትሸፍን
የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር
ማን ኛዋም ሴት የእርሷን ራስ ታዋርዳለች፤
ጠጕሯን እንደ ተላጨች ይቈጠራልና።
6ሴት ራሷን የማትሸፍን ከሆነ፣ ጠጕሯን
ትቈረጥ፤ ጠጕሯን መቈረጥ ወይም
መላጨት የሚያሳፍር መስሎ ከታያት ግን
ራሷን ትሸፈን። 7ወንድ ራሱን መከናነብ
የለበትም፤ ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና
ክብር ነውና፤ ሴት ግን የወንድ ክብር
ናት፤ 8ምክንያቱም ሴት ከወንድ ተገኘች
እንጂ ወንድ ከሴት አልተገኘም። 9ደግሞም
ሴት ለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ
ለሴት አልተፈጠረም። 10በዚህ ምክንያት፣
በመላእክትም ምክንያት፣ ሴት በሥልጣን
ሥር መሆኗን የሚ ያሳይ ምልክት በራሷ
ላይ ታድርግ።

11በጌታ ዘንድ ግን ሴት ያለ ወንድ፣
ወንድም ያለ ሴት አይሆንም። 12ሴት
ከወንድ እንደ ተገኘች ሁሉ፣ ወንድም
ከሴት ይወለዳልና፤ ነገር ግን የሁሉም
መገኛ እግዚአብሔር ነው። 13እስቲ እናንተ
ፍረዱ፤ ሴት ራሷን ሳትሸፍን ወደ
እግዚአብሔር መጸለይ ይገባታልን? 14ወንድ
ጠጕሩን ቢያስረ ዝም ነውር እንደሚሆንበት

11፥4 ሐሥ11፥27
11፥5 ዘዳ21፥12፤ ሐሥ21፥9
11፥7 ዘፍ1፥26፤ 5፥1፤ 9፥6፤ ያዕ3፥9
11፥8 ዘፍ2፥21-23፤ 1ጢሞ2፥13
11፥9 ዘፍ2፥18
11፥12 ሮሜ11፥36
11፥16 1ቆሮ7፥17፤ 10፥32
11፥17 ቍ 2:22
11፥18 1ቆሮ1፥10-12፤ 3፥3
11፥19 1ዮሐ2፥19

ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራችሁምን?
15ሴት ግን ጠጕሯን ብታስረዝም ክብሯ
አይደለምንን? ረጅም ጠጕር የተሰጣት
መጐናጸፊያ እንዲሆናት ነውና። 16እንግዲህ
ማንም በዚህ ጒዳይ ላይ መከራከር
ቢፈልግ፣ እኛም ሆን የእግዚአብሔር አብያተ
ክርስቲያናት ከዚህ የተለየ ልማድ የለንም።

## የጌታ እራት

*11፥23-25 ተዓ — ምብ ማቴ 26፥26-28፤*
*ማር 14፥22-24፤ ሉቃ 22፥17-20*

17ነገር ግን በምትሰበሰቡበት ጊዜ
ለሚጐዳ እንጂ ለሚጠቅም ስላልሆነ፣ ይህን
ትእዛዝ ስሰጥ እያመሰገንኋችሁ አይደለም።
18ከሁሉ አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን
በምትሰበሰቡበት ጊዜ በመካከላችሁ
መለያየት እንዳለ ሰምቻለሁ፤ ይህም ሊሆን
እንደሚችል በከፊል አምናለሁ። 19ከእናንተ
መካከል እውነተኞቹ ተለይተው ይታወቁ

*11፥4-7 ወይም የራሱን ጠጕር አስረዝሞ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ማንኛውም ወንድ ራሱ የሆነውን ያዋርዳል፤ 5ራሷን ሳትከናነብ የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ማንኛ ዋም ሴት ራሷ የሆነውን ታዋርዳለች፤ ጠጕራቸውን ከተ ላጩ ሴ ቶች እንዷ ትመሰላለችና። ሴት ራሷን የማትከናነብ ከሆነ፣ ጠጓሯን ታሳጥር፤ ጠጕሯን መቈረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ስለሆነ ግን እንደገና ታሳድገው። 7ወንድ ጠጕሩን ማስረዘም የለበትም፤*

መንግሥት ውስጥ ታላቅ ለመሆን የሚያስችሉ ዋና ነገሮች ናቸው (ማቴ 20፥25-28፤ ፊል 2፥5-9)። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የወንድና የሴትን ግንኙነት በተመለከተ ያቀረበው ሐሳብ፣ በጋብቻ ውስጥ የባልና የሚስትን ኀላፊነት በተመለከተ ካቀረበው ሐሳብ ጋር ተያይዞ መጠናት አለበት (ኤፌ 5፥21-23 እና ማብ ይመ)።

**11፥6 ራስዋን ትሸፍን፤** በሐዋርያው ጳውሎስ ዘመን ሴት ራስዋን የምትሸፍነው ትሕትናዋንና ታዛዥነትዋን ለባልዋ ለማሳየት እንዲሁም ክብሯን ለመግለጽ ነበር። የመሸፈኛው ትርጒም ሴት እንደ መሆኗ መጠን ልትከበርና ልትወደድ እንደሚገባ ለማመልከት ነው። ሴት ራስዋን ባትሸፍን ክብር አይኖራትም፤ ወንዶች መሸፈኛ ያላደረጉ ሴቶችን አያከብሩም፤ ይኸውም ያለኀፍረት በሕዝብ ፊት ልታይ ልታይ ስለሚሉ ነው። ስለዚህ የመሸፈኛው አገልግሎት ሴት እግዚአብሔር እንደፈጠራት የሴትነትዋን ማንነትና ክብር ምን እንደ ሆነ የሚያሳይ ምልክት ነው።

መሸፈኛን ከማድረግ በስተጀርባ ያለው መርሕ ዛሬም ቢሆን አስፈላጊ ነው። ክርስቲያን ሴት በየትኛም ስፍራ ተከብራና ተፈርታ መንቀሳቀስ ትችል ዘንድ ሞገስ የሚሰጥና የሚያስከብራትን ልብስ በመልበስ በጭምትነትና በጥንቃቄ መመላለስ ይገባታል። ሴት በጨዋነትና ለእግዚአብሔር ክብር በሚገባ ሁኔታ ብትለብስ፣ እግዚአብሔር የሰጣትን የክብር ቦታና ደረጃ የበለጠ ታሳድገዋለች።

**11፥10 በሥልጣን ... የሚያሳይ ምልክት በራስዋ ላይ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ገና ሴት በሕዝብ ፊት ራስዋን መሸፈን እንዳለባት በአጽንዖት ተናግሮአል፤ ይህም በሥልጣን ሥር መሆንዋን የሚያሳይ ምልክት ነው (ቍ 3:6 እና ማብ ይመ)። “በመላእክት ምክንያት” የሚለው ሐረግ መላእክት ተገቢ በሆነ ሥርዐት ላይ እንደሚያተኵሩና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይስማማ ባሕርይ ከታየም እንደሚደናገጡ ለማመልከት ነው (ከ4፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

**11፥14 ወንድ ጠጕሩን ቢያስረዝም፤** እግዚአብሔር በወንድና በሴት መካከል ያለው የአካል ልዩነት በተፈጠሩበት ሁኔታ እንዲጠበቅ ይፈልጋል። (1) ሐዋርያው ጳውሎስ ጠጕርን በምሳሌነት ያቀረበው፣ በወንድና በሴት ጠጕር ርዝመት መካከል ያለው ልዩነት አንዱን ከሌላው ለመለየት እንደሚረዳ ለማሳየት ነው። የሴት ጠጕር ከወንድ ጠጕር ጋር ሲነጻጸር ረዥም መሆን አለበት፤ ይኸውም እግዚአብሔር ሴትን በሴትነትዋ እንደፈጠራት ያላትን ክብርና የሚሰጣትን ከፍተኛ ግምት በምሳሌነት የሚያሳይ ስለሆነ ነው (ቍ 6 እና ማብ ይመ)። የወንድ ጠጕር ከሴት ጠጕር ጋር ሲነጻጸር አጭር መሆን አለበት።

(2) በአዲስ ኪዳን ዘመን ጠጕርን ማስረዘም አሳፋሪና በአይሁድ ወንዶችም ሆነ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበሩ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ነገር ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ረዥም ጠጕር እንደነበረው ተደርጎ በስዕል መቅረቡ ሙሉ በሙሉ በመካከለኛው ዘመን ከነበሩ ሰዓሊዎች በመጣ አስተሳሰብ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ወይም ታሪካዊውን ማረጋገጫ መሠረት ያደረገ አይደለም፤ በሺዎች የሚቈጠሩ የአዲስ ኪዳን የስዕል ቅቦችና ቅርጻ ቅርጾች ይህን ያረጋግጣሉና። ኢየሱስ ክርስቶስ ጠጕሩን እንደ ሴቶች ቢያስረዝም ኖሮ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ “ወንድ ጠጕሩን ቢያስረዝም ነውር እንደሚሆንበት” ብሎ ባልጻፈ ነበር። ስለዚህ የጳውሎስ ቃል የሚጋጨው ከኢየሱስ የጠጕር ሁኔታ ጋር ሳይሆን፣ ከሰዓሊዎች ፈጠራ ጋር ነው (ከዘፀ 20፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

ዘንድ፣ ይህ መለያየት በመካከላችሁ
መኖሩ የግድ ነው። 20በምትሰበሰቡበት
ጊዜ የምትበሉት **የጌታን** እራት አይደለም፤
21በምትበሉበት ጊዜ አንዱ ሌላውን
ሳይጠብቅ ምግቡን ይበላልና፤ አንዱ
እየ ተራበ ሌላው ይሰክራል። 22ለመሆኑ
የምትበሉ በትና የምትጠጡበት ቤት
የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ቤተ
ክርስቲያን በመናቅ፣ ምንም የሌላቸውን
ታሳፍራላችሁን? እንግዲህ ምን ልበላችሁ?
በዚህ ነገር ላመስግናችሁን? ፈጽሞ
አላመሰግናችሁም።
23እኔ **ከጌታ** የተቀበልሁትን ለእናንተ አስ
ተላልፌአለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተ

11፥21
2ጴጥ2፥13፤
ይሁ1፥12
11፥22 ቆላ2:17፤
ቆሮ10፥32፤
ያዕ2፥6
11፥23 ቆላ2፤
ገላ1፥12
11፥24
1ቆሮ10፥16
11፥25
ሉቃ22፥20፤
1ቆሮ10፥16
11፥26 1ቆሮ1፥7
11፥27 ዕብ10፥29

ሰጠባት ሌሊት እንጀራን አንሥቶ 24ከባረከ
በኋላ ቈርሶ፣ "ይህ ስለ እናንተ የሚሆን
ሥጋዬ ነው፤ ለመታሰቢያዬም አድርጉት"
አለ። 25እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን
አንሥቶ፣ "ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ
ኪዳን ነው፤ ስለዚህ ከጽዋው በምትጠጡበት
ጊዜ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት"
አለ። 26ይህን እንጀራ በምትበሉበት
ጊዜ፣ ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ
ሁሉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን
ትናገራላችሁ።
27እንግዲህ ማንም ሳይገባው፣ ይህን
እንጀራ ቢበላ ወይም **የጌታን** ጽዋ ቢጠጣ፣
**የጌታ** ሥጋና ደም ባለ ዕዳ ይሆናል።

**11፥20 የጌታን እራት፤** የጌታ እራት በሚከተሉት አራት ክፍሎች ውስጥ ተጠቅሶአል፤ ማቴ 26፥26-29፤ ማር 14፥22-25፤ ሉቃ 22፥15-20፤ 1ቆሮ 11፥23-25። የጌታ እራት አስፈላጊነት ከአለፈው፣ ከአሁኑና ከወደፊቱ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው፤

(1) ስለ አለፈው ነገር ያለው አስፈላጊነት፤ (ሀ) የጌታ እራት አማኝ ከኀጢአትና ከእርግማን ቤዛነትን ያገኘ ዘንድ ክርስቶስ ለሞተው ሞት መታሰቢያ (ግሪክ፡ "አናምኔሲስ" ቍ 24-26፤ ሉቃ 22፥19) ነው። የጌታ እራት የሚያድነውን የክርስቶስ ሞትና ይህም ለሕይወታችን ቤዛነት አስፈላጊ እንደ ሆነ እንደገና በግልጽ እንድናስብና እንድናይ ያደርገናል። በኀጢአት ውስጥ ወድቀን እንዳንቀርና ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር እንድንርቅ (1ተሰ 5፥22) የሚያደርገን ዋናው ምክንያት የክርስቶስ ሞት ነው። (ለ) የጌታ እራት ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሥዋዕትነት በመሞቱ ስለተገኘው የእግዚአብሔር በረከትና ድነት የሚቀርብ ምስጋና (ግሪክ፡ "ዩካሪስትያ") ነው (ቍ 24፤ ማቴ 26፥27፤ ማር 14፥23፤ ሉቃ 22፥19)።

(2) አሁን ያለው አስፈላጊነት፤ የጌታ እራት ከክርስቶስ ጋር ኅብረት (ግሪክ፡ "ኮይኖንያ") ማድረግ፣ እርሱም የመሥዋዕትነትን ሞት በመሞቱ ምክንያት የተገኙትን በረከቶች መካፈልና በተጨማሪም የክርስቶስ አካል ከሆኑ አባላትም ጋር ኅብረት ማድረግ ነው (10፥16-17)። ከሞት ከተነሣው ጌታ ጋር የምንካፈለው ይህ እራት እርሱ ጋባዥ ሆኖ ልዩ በሆነ መንገድ በመካከላችን የሚገኝበት ነው (ከማቴ 18፥20፤ ከሉቃ 24፥35 ጋር ያነጻጽሩ)። (ለ) አዲስ ኪዳን የሚታወቅበትና የሚታወጅበት (ግሪክ፡ "ካይኔ ኪያቴኬ") ሲሆን፣ አማኞች የክርስቶስን ጌትነት የምናረጋግጥበት እንዲሁም ፈቃዱን ለማድረግ፣ በታማኝነት ለመሆር ኀጢአትን ለመቃወምና ከተልእኮው ጋር ራሳችንን ለማስተባበር ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር የምንሰጥበት ሁኔታ ነው (ቍ 25፤ ማቴ 26፥28፤ ማር 14፥24፤ ሉቃ 22፥20 እንዲሁም በገጽ 1970 ላይ፣ "*የቀደመው ኪዳንና አዲሱ ኪዳን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) የወደፊቱ አስፈላጊነት፤ (ሀ) የጌታ እራት የወደፊቱ የእግዚአብሔር መንግሥትና አማኞች ሁሉ ከጌታ ጋር አብረው የሚሆኑበት የወደፊቱ የመሲሑ ግብዣ የመጀመሪያ ቅምሻ ነው (ማቴ 8፥11፤ 22፥1-14፤ ማር 14፥25፤ ሉቃ 13፥29፤ 22፥17-18፡30)። (ለ) ክርስቶስ ለሕዝቡ በቅርብ የሚመለስበት ጊዜ (ቍ 26) በጉጉት እንዲጠበቅ የሚያመለክትና "መንግሥትህ ትምጣ" (ማቴ 6፥10 ይመ፤ ከራእ 22፥20 ጋር ያነጻጽሩ) የሚለውን ጸሎት በሚገባ የሚገልጽ ነው።

በጌታ እራት ሥርዐት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱት አስፈላጊ ነገሮች ትርጕም የሚኖራቸው በእግዚአብሔር ፊት በእውነተኛ እምነት፣ ልባዊ በሆነ ጸሎት እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ራሳችንን በመስጠት ስንቀርብ ብቻ ነው።

**11፥21 ሌላው ይሰክራል፤** "አንዱ እየተራበ ሌላው ይሰክራል" የሚለው "አንዱ እየተራበ ሌላው እጅግ ጠግቧል" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ከላይ የተሰጠው ትርጕም የተሻለ ሆኖ የተገኘው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤ (1) "ይሰክራል" (ግሪክ፡ "ሜቱኦ") የሚለው ቃል ሁለት ትርጕሞችን ይዟል፤ (ሀ) በመጠጥ መስከር ሊሆን ይችላል፤ ወይም (ለ) ስካርን ሳያመለክት መሞላት ወይም መርካት ይሆናል (ዮሐ 2፥10 እና በቃና በነበረው ሰርግ ይህን ቃል በተመለከተ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ)።

(2) ይህ ጥቅስ ያለበት ዐውድ በአጠቃላይ ከምግብ ጋር የተያያዘ ነው። የጌታን እራት ሥርዐት ከመፈጸማቸው በፊት የቆሮንቶስ ሰዎች የኅብረት ማእድ ለመብላት በአንድነት ሲሰበሰቡ (2ጴጥ 2፥13፤ ይሁ 1፥12)፣ አንዳንዶች በትናንሽ ቡድን ሆነው ለየት በማለት የየራሳቸውን ምግብ ይበሉ ነበር (ቍ 18-19)። ስለዚህ በምግቡ ላይ የራሳቸውን ድርሻ ማውጣት የማይችሉ ድኾች ችላ ተብለው ለራብ ይዳረጋሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚናገርበት ጒዳይ በመጠጥ የሚመጣ ስካርን በተመለከተ አይደለም፤ ያንን በተመለከተ አንሥቶ ቢሆን ኖሮ በዚህ መጽሐፍ በሌላ ስፍራ እንዳደረገው በርግጥ እዚህም ላይ አጥብቆ ባወገዘው ነበር (ከ6፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። እርሱ በመጠጥ መስከርን የሚያየው ሌሎችን ችላ እንደማለት ያህል የሚቈጠር ጒዳይ ብቻ እንደሆነ አድርጐ አይደለም፤ ነገር ግን እጅግ ከባድ ሁኔታ ከመሆኑ የተነሣ ሰውን ከእግዚአብሔር መንግሥትም ሊለይ የሚችል መሆኑንም ጭምር ነው (6፥10፤ ገላ 5፥21)።

**11፥24-25 ሥጋዬ ... በደሜ፤** እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት በሞት የተሰጠውን የክርስቶስን ሥጋና በመስቀል ላይ በመሥዋዕትነት የፈሰሰውን ደሙን ነው። ክርስቶስ እንጀራውን "ይህ ሥጋዬ ነው" ሲል፣ እንጀራው ሥጋውን ይወክላል ማለት ነው። "ጽዋው" የሚወክለው "አዲስ ኪዳንን" ለማጽደቅ የፈሰሰውን የክርስቶስን ደም ነው። ሥጋውን መብላትና ደሙን መጠጣት በክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት የተገኙትን በረከቶች መቀበልንና ማወጅን ያመለክታል (ቍ 26)።

**11፥27 ሳይገባው ... ቢበላ ... ቢጠጣ፤** ሳይገባው መብላት ማለት ከታወቀ ኀጢአት ለመራቅ ፍላጎት ወይም ዝንባሌ ሳይኖር እንዲሁም የጸጋውን ኪዳን ከተስፋዎቹና

28ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ከመብላቱና
ከዚህ ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት፣ ራሱን
ይመርምር፤ 29ምክንያቱም ማንም የጌታን
ሥጋ ሳይገባው* ቢበላና ቢጠጣ ፍርድ
የሚያመጣበትን ይበላል፤ ይጠጣል።
30ከእናንተ መካከል ብዙዎች የደከሙትና
የታመሙት፣ አንዳንዶችም ያንቀላፉት በዚህ
ምክንያት ነው። 31ራሳችንን ብንመረምር
ግን ባልተፈረደብን ነበር። 32ነገር ግን ጌታ
በሚፈርድብን ጊዜ እንገሠጻለን፤ ይኸውም
ከዓለም ጋር አብረን እንዳንኰነን ነው።
33ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፤ ለመብላት
በምትሰበሰቡበት ጊዜ እርስ በርሳችሁ
ተጠባበቁ። 34በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለፍርድ
እንዳይሆንባችሁ፣ ማንም የራበው ሰው
ቢኖር በቤቱ ይብላ። ስለቀረው ነገር ደግሞ
በምመጣበት ጊዜ እደነግጋለሁ።

11፥28 2ቆሮ13፥5
11፥30 ማቴ9፥24
11፥31 መዝ32፥5፤ 1ዮሐ1፥9
11፥32 መዝ94፥2፤ 118፥18፤ ምሳ3፥11፡12፤ የሐ15፥18፡19፤ ዕብ12፥7-10፤ ራእ3፥19
11፥34 ቍ21፡22፤ 1ቆሮ4፥19

## መንፈሳዊ ስጦታዎች

12 ወንድሞች ሆይ፤ አሁን ደግሞ
ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይህን

12፥1 ሮሜ1፥11፤ 11፥25፤ 1ቆሮ1፥7፤ 14፥1:37

ከግዴታዎቹ ሁሉ ጋር አምነው ሳይቀበሉ በግዴለሽነት፣ በራስ ወዳድነትና ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌለበት መንፈስ የጌታን እራት ማእድ መካፈል ማለት ነው:: በእንዲህ ዐይነቱ በማይገባ ሁኔታ የጌታን እራት የሚካፈሉ ሁሉ በጌታ ፊት ታላቅ ኀጢአት ይፈጽማሉ:: እንደዚህ ማድረጋቸው ክርስቶስን እንደ ገና መስቀላቸው ስለሆነ በደለኞች ናቸው፡ ወዲያውኑም በእግዚአብሔር ልዩ ፍርድ ሥር የሚወድቁና የእጃቸውን የሚቀበሉ ይሆናሉ (ቍ 29-32):: "የጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ" መሆን ለክርስቶስ ሞት ቡንላፊነት ተጠያቂ መሆን ማለት ነው::

**11፥32 እንገሠጻለን፤** የእግዚአብሔር ፍርድ ዐላማ (ከቍ 30 ጋር ያነጻጽሩ) ከዓለም ጋር ወደ ለዘላለም ኵነኔ ለመሄድ እንዳይፈረድብን ነው:: ይህ ምሕረት የተሞላበት ዐላማ የሚጠቅመው ራሳቸውን በሚገባ ለሚመረምሩና በትክክል ወደ እርሱ በንስሓ ለሚመለሱ ነው (ቍ 31)::

**12፥1 ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች፤** ከምዕራፍ 12—14 ባለው ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ለክርስቶስ አካል ስለተሰጡት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተናግሯል:: እነዚህ ስጦታዎች በጥንታዊቷዋ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነበሩ:: እግዚአብሔር እነዚህ ስጦታዎች ክርስቶስ ዳግም እስከሚመጣበትም ጊዜ ድረስ ሳይቋረጡ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እንዲገለጡ አስቦአል (1፥7 እና ማብ ይመ):: መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ እግዚአብሔር ያለውም ዐላማ እንደሚከተለው ተዘርዝሮአል:-

(1) በሕዝቡ መካከል በጋራ ስብሰባዎቻቸው፣ በየቤቶቻቸው፣ በየቤተሰቦቻቸውና በግል ሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ፣ ኀይልና ፍቅር ለመግለጽ (ቍ 4-7፤ 14፥25፤ ሮሜ 15፥18-19፤ ኤፌ 4፥8)::

(2) የወንጌል ስብከት ውጤታማ እንዲሆን ለመልእክቱ መለኮታዊ ማረጋገጫንና ማጽኛን ለመስጠት (ማር 16፥15-20፤ ሐሥ 14፥8-18፤ 16፥16-18፤ 19፥11-20፤ 28፥1-10)::

(3) የሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንና (ቍ 7:14-30፤ 14፥3:12:26) ግለሰብ አማኞችን (14፥4) በመንፈሳዊ ረገድ ለማበረታታትና ለማነጽ፤ ይኸውም "ከንጹሕ ልብ፣ ከበጎ ኅሊናና ከእውነተኛ እምነት በሚወጣ ፍቅር" (1ጢሞ 1፥5፤ ከ1ቆሮ 13 ጋር ያነጻጽሩ) አማኞችን ፍጹማን ማድረግ ነው::

(4) በሰይጣንና በክፉ ኀይላት ላይ ውጤታማ የሆነን መንፈሳዊ ጦርነት ለማወጅ (ኢሳ 61፥1፤ ሐሥ 8፥5-7፤ 26፥18፤ ኤፌ 6፥11-12):: የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በተመለከተ የሚጠቀሱ ምንባቦች ሮሜ 12፥3-8፤ 1ቆሮ 1፥7፤ 12፥14፤ ኤፌ 4፥4-16፤ 1ጴጥ 4፥10-11 የሚያካትቱ ናቸው::

**12፥1 መንፈሳዊ ስጦታዎች፤** ከቍ 1-6 ይመልከቱ:: መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ቃላት ልዩ ባሕርያቸውን ይገልጻሉ:: (1) "መንፈሳዊ ስጦታዎች" (ግሪክ፡ "ኑማቲካ" የሚለው ቃል የመጣው "ኑማ" ወይም "መንፈስ" ከሚለው ነው) የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በመሆን የሚከሠቱትን መለኮታዊ መገለጦች ነው:: እነዚህም ስጦታዎች ለጋራ ጥቅም በአማኞች መካከል የሚሠሩ ናቸው (ቍ 1:7፤ 14፥1)::

(2) "ስጦታዎች" ወይም "የጸጋ ስጦታዎች" (ግሪክ፡ "ካሪስማታ" የሚለው ቃል የመጣው "ካሪስ" ወይም "ጸጋ" ከሚለው ነው) የሚለው ቃል መንፈሳዊ ስጦታዎች ውስጣዊ መነሣሣትና አገልግሎት ለመፈጸም የሚያስችለው ኀይል ማለትም የተገኘው ችሎታ ሁለቱንም በአንድነት ያካተቱ መሆናቸውን ያመለክታል፤ ከመንፈስ ቅዱስም የምናገኛቸው እንደ ሆነ ያሳያል፤ እንዲህ ዐይነት ስጦታዎች በመንፈሳዊ ረገድ የክርስቶስን አካልና መንፈሳዊ ርዳታ የሚፈልጉትን ሰዎች ያበረታሉ (ቍ 4፤ ሮሜ 12፥6 እና ማብ፤ ኤፌ 4፥11፤ 1ጴጥ 4፥10 እንዲሁም በገጽ 1866 ላይ፣ "***የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(3) "አገልግሎት" ወይም "አገልግሎቶች" (ግሪክ፡ ዲያኮንያይ" የሚለው ቃል የመጣው "ዲያኮንያ" ወይም "አገልግሎት" ከሚለው ነው) የሚለው ቃል በአጽንዖት የሚያመለክተው አገልግሎት የሚሰጥባቸው የተለያዩ መንገዶች መኖራቸውን እንዲሁም የተወሰኑ ስጦታዎች ሌሎችን ለመርዳት ችሎታና ኀይል ያካተቱ መሆኑንም ጭምር ነው (ቍ 4-5:27-31፤ ኤፌ 4፥7:11-13):: ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያመለክተው ስጦታዎች የሚገለጡበት የአገልግሎት አቅጣጫ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን "የሎሌነት" አገልግሎት ማንጸባረቅ እንዳለበት ነው:: ስለዚህ በስጦታዎች የማገልገል ሁኔታ መታየት ያለበት የክርስቶስ ህልዎት በመካከላችን እንዳለና እርሱም በመካከላችን እየሠራ እንደ ሆነ ከማስብ አንጻር ነው (ከቍ 3፤ 1፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

(4) "አሠራር" ወይም "ውጤት" (በግሪክ፡ "ኢነርጌማታ" የሚለው ቃል የመጣው "ኢነርጌስ" ወይም "ንቁ፣ ብርቱ" ከሚለው ቃል ነው) የሚለው ቃል የሚያመለክተው መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚሠሩት በቀጥታ በእግዚአብሔር አብ ኀይል መሆኑንና አንድ ውጤትም እንደሚያመጡ ነው (ቍ 6:10)::

(5) "መንፈስ ቅዱስን መግለጥ" (ግሪክ፡ "ፋኔሮሲስ" የሚለው ቃል የመጣው "ፋኔሮስ" ወይም "መግለጥ" ከሚለው ቃል የመጣ ነው) የሚለው ሐረግ በአጽንዖት የሚያመለክተው መንፈሳዊ ስጦታዎች በጉባኤ ውስጥ በቀጥታ የመንፈስ ቅዱስ ሥራና ህልዎት መገለጫዎች እንደ ሆኑ ነው (ቍ 7-11)::

እንድ ታውቁ እፈልጋለሁ። 2አረማውያን
በነበራችሁበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ በመነዳት
ድዳ ወደ ሆኑ ጣዖታት እንደ ተወሰዳችሁ
ታውቃላችሁ። 3ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር
መንፈስ የሚናገር፣ "ኢየሱስ የተረገመ
ነው" የሚል የለም፤ እንደዚሁም በመንፈስ
ቅዱስ ካልሆነ በቀር፣ ማንም "ኢየሱስ ጌታ
ነው" የሚል እንደሌለ እነግራችኋለሁ።
4ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ
ግን አንድ ነው፤ 5አገልግሎትም ልዩ ልዩ
ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ 6አሠራርም
ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው
ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው።
7ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ
ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም
ነው። 8ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል
መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው
መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤
9ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት
ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ
መንፈስ የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤
10ለአንዱ ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው
ትንቢትን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ መና
ፍስትን የመለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ
ልሳን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ
ልሳን[ን] የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ
ይሰጠዋል። 11እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ
መን ፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ
ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል።

## አንድ አካል ብዙ ብልቶች

12አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ
አካል ነው፤ ነገር ግን ብልቶች ብዙ ቢሆኑም
አካል አንድ ነው። ክርስቶስም እንደ ዚሁ
ነው። 13አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች
ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣
እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ
መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አን ዱን
መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል።
14አካል የተሠራው ከብዙ ብልቶች እንጂ
ከአንድ ብልት አይደለም። 15እግር፣ "እኔ
እጅ ስላልሆንሁ የአካል ክፍል አይደለሁም"
ቢል ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ
ይቀራልን? 16ጆሮም፣ "እኔ ዐይን ስላልሆንሁ
የአካል ክፍል አይደለሁም" ቢል ይህን
በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን?
17አካል በሙሉ ዐይን ቢሆን ኖሮ፣ መስማት
ከየት ይገኝ ነበር? አካል በሙሉ ጆሮ ቢሆን
ኖሮ፣ ማሽተት ከየት ይገኝ ነበር? 18ነገር
ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ እያንዳንዱን
በየቦታው መድቦአል። 19ሁሉም አንድ
ብልት ቢሆን ኖሮ አካል ከየት ይገኝ ነበር?
20እንግዲህ ብልቶች ብዙ ናቸው፣ አካል ግን
አንድ ነው።
21ዐይን እጅን፣ "አታስፈልገኝም"
ሊለው አይችልም፤ ራስም እግርን፣
"አታስፈልጉኝም" ሊለው አይችልም።
22እንዲያውም ደካማ የሚመስሉት የአካል
ብልቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። 23የተናቁ
ለሚመስሉን ብልቶች ይበልጥ ክብር
እንሰጣቸዋለን፤ ደግሞም የምናፍርባቸውን
ብልቶች ይበልጥ እንንከባከባቸዋለን፤
24የማናፍርባቸው ብልቶቻችን ግን ይህ
አያስፈልጋቸውም። እግዚአብሔር ግን የአካል
ብልቶችን አንድ ላይ አገጣጥሞ ክብር
ለሚጐድላቸው የበለጠ ክብር ሰጥቶ
አቸዋል፤ 25ይህንም ያደረገው በአካል
ብልቶች መካከል መለያየት ሳይኖር፣ እርስ

12፥2 መዝ115፥5፤ ኤር10፥5፤ ዕን2፥18፡19፤ ኤፌ2፥2
12፥3 ዮሐ13፥13፤ ሮሜ9፥3፤ 1ቆሮ16፥22፤ 1ዮሐ4፥2፡3
12፥4 ቍ8-11፤ ሮሜ12፥4-8፤ ኤፌ4፥11፤ ዕብ2፥4
12፥6 ኤፌ4፥6፤ ፊል2፥13
12፥7 1ቆሮ14፥12፤ ኤፌ4፥12
12፥8 1ቆሮ2፥6፤ 2ቆሮ8፥7
12፥9 ቍ28:30፤ ማቴ10፥1፤ 17፥19:20፤ 1ቆሮ13፥2
12፥10 ቍ28-30፤ ማር16፥17፤ ገላ3፥5፤ ኤፌ4፥11፤ 1ዮሐ4፥1
12፥11 ቍ4
12፥12 ቍ27፤ ሮሜ12፥5
12፥13 ዮሐ7፥37-39፤ ገላ3፥28፤ ኤፌ2፥18፤ ቈላ3፥11
12፥14 ቍ12:20
12፥18 ቍ11:28
12፥20 ቍ12:14፤ ሮሜ12፥5

[ን]12፥10 ወይም ቋንቋ፤ እንዲሁም ቍ28 ይመ

**12፥3 ኢየሱስ ጌታ ነው፤** ሐዋርያው ጳውሎስ *መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ ያለውን እውነት መናገር የሚጀምረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና መግለጦች የቤተ ክርስቲያን ጌታ እንደመሆኑ ኢየሱስን ከፍ ከፍ እንደሚያደርጉት በመግለጽ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከፍተኛው መመዘኛ በአማኝ ሕይወት ውስጥ እያደገ መምጣት ያለበትን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት፣ ሀልዎት፣ ኀይል፣ ፍቅርና ጽድቅ መግለጹ ነው:: በመንፈሳዊ ስጦታዎች መገለጥ ውስጥ ክርስቶስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሕዝቡ አማካይነት ሕዝቡን ያገለግላል (ቍ 12-27፤ ማቴ 25፥40 ይመ)::*

**12፥7 መንፈስ ቅዱስን መግለጥ፤** *መንፈሳዊ ስጦታዎች የመንፈስ ቅዱስ መገለጫዎች ስለ መሆናቸው የተሰጠውን ማብራሪያ እንዲሁም በዚህ ስፍራ በዝርዝር ስለተጠቀሱት አያሌ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለመረዳት በገጽ 1800 ላይ፣* ***«ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች»*** *በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::*

**12፥12 ክርስቶስም እንደዚሁ ነው፤** *ቍ 1 እንዲሁም ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና ስለ ክርስቶስ አካል የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::*

**12፥13 እኛ ሁላችን ... በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤** *«በአንድ መንፈስ መጠመቅ» የሚለው ሐረግ የውሃን ጥምቀት ወይም በጰንጤ ቈስጤ ዕለት እንደሆነው ክርስቶስ አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቁን የሚያመለክት አይደለም (ማር 1፥8፤ ሐሥ 2፥4 እና ማብ ይመ):: ይልቁንስ ይህ የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በአካሉ ውስጥ አንድ እንዲሆኑና በመንፈሳዊ ረገድም አንዱ ከሌላው አማኝ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ ወደ ክርስቶስ አካል እንዲገቡ የሚያጠምቀውን ጥምቀት ነው:: ይህም መንፈሳዊ መለወጥ (ዳግም ልደት) አንድ ሰው ክርስቶስን መከተል በሚወስንበት ጊዜ የሚፈጸምና አማኙን «በክርስቶስ እንዲሆን» የሚያደርግ ነው (በገጽ 1606 ላይ፣* ***«ዳግም ልደት»*** *በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::*

**12፥25 ብልቶች ... እርስ በእርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው፤** *መንፈሳዊ ስጦታ አንድ ሰው የሚከበርበት ወይም ስጦታው ያለው አማኝ ከሌላው ሰው የተሻለ ሆኖ የሚቈጠርበት መሠረታዊ መመዘኛ ሊሆን አይገባም (ቍ 22-24):: ይልቁንስ እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ አካል ውስጥ የተቀመጠው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነና (ቍ 18) እያንዳንዱ ብልትም ለአካሉ መንፈሳዊ ደህንነት እንዲሁም ተገቢ ለሆነው ሥራው አስፈላጊ እንደሆነ ሊታሰብ ይገባል:: መንፈሳዊ ስጦታዎችም አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚገባው በትዕቢት ወይም የግል ማንነትን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሳይሆን፣ ሌሎችን ለመርዳት ካለን ጥልቅ ምኞትና ርስ በርስ ለመረዳዳትም ካለን እውነተኛ የልብ ፍቅር የተነሣ ነው (ምዕ 13 ይመ)::*

# ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች

*1ቆሮ 12፥7 "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው።"*

**አጠቃላይ እይታ፤** መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች በተሰጡ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተገልጦአል (1ቆሮ 12፥7)። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባትና ለመቀደስ ታስበው የቀሰጡ ናቸው (1ቆሮ 12፥7፤ 14፥26 እና ማግብ ይመ)። እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሮሜ 12፥6-8 እና በኤፌ 4፥11 ላይ ከተጠቀሱት ስጦታዎችና አገልግሎቶች ጋር ተመሳሳይ አይደሉም፤ አማኝ እነዚያን ስጦታዎች የሚቀበለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቋሚ በሆነ መንገድ ለማገልገል የሚያስችለውን ኀይልና ችሎታ ለማግኘት ነው። በ1ቆሮ 12፥8-10 ያለው ዝርዝር የግድ ስጦታዎቹን ሁሉ ያካተተ መሆን የለበትም፤ ስጦታዎቹም የተጠቀሱት በተለያየ ሁኔታ ተጣምረው ሊሆን ይችላል።

(1) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መገለጦች ለሰዎች የሚሰጡት የሚያስፈልጉበት ሁኔታ ሲከሠትና አማኝ በትጋት ሲሻቸው (1ቆሮ 12፥31፤ 14፥1) እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነው (1ቆሮ 12፥11)።

(2) አንዳንድ ስጦታዎች በአማኝ ሕይወት ውስጥ በቋሚነት ሊገለጡ ይችላሉ፤ እንዲሁም አንድ አማኝ ሁኔታው በሚጠይቅበት ጊዜ ያገለግል ዘንድ ከአንድ ስጦታ በላይ ሊኖረው ይችላል። አማኝ መሻት ያለበት "ብዙ ስጦታዎችን" እንጂ አንድ ስጦታን ብቻ መሆን የለበትም (1ቆሮ 12፥31፤ 14፥1)።

(3) በጣም አስደናቂ በሆነና በሚታይ ስጦታ የሚያገለግል አንድ አማኝ አስደናቂ ባልሆነና በማይታይ ስጦታ ከሚያገለግለው አማኝ ይበልጥ መንፈሳዊ ነው ብሎ ማሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነና ጥበብ የጐደለው አስተያየት ነው። ከዚህም በላይ ስጦታ ያለው ሰው ለሚያደርገውና ለሚሰጠው ትምህርት ሁሉ እግዚአብሔር ማረጋገጫን ይሰጠዋል ማለት አይደለም። መንፈሳዊ ስጦታዎች ከክርስቲያን ባሕርይና ከመቀደስ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ካላቸው ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ጋር ፈጽሞ ሊምታቱ አይገባም (ገላ 5፥22-23)።

(4) በስጦታዎች አማካይነት የሚገለጠውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሰይጣን ወይም ራሳቸውን በመሰወር እንደ ክርስቶስ አገልጋይ የሚንቀሳቀሱ ሐሰተኛ ሠራተኞች አስመስለው ሊያደርጉት ይችላሉ (ማቴ 7፥21-23፤ 24፥11፡24፤ 2ቆሮ 11፥13-15፤ 2ተሰ 2፥8-10)። አማኝ ማንኛውንም መንፈሳዊ መገለጥ ማመን አይገባውም፤ ነገር ግን ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ስለወጡ መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆናቸውን መመርመር አለበት (1ዮሐ 4፥1፤ ከ1ተሰ 5፥20-21 ጋር ያነጻጽሩ እንዲሁም በገጽ 1694 ላይ፣ "እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**ለእያንዳንዱ አማኝ የሚሰጡ የተለያዩ ስጦታዎች፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 12፥8-10 መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ስለ ሰጠው ስጦታ በዝርዝር ጠቅሶአል። በዚህ ስፍራ የእያንዳንዳቸውን ባሕርይ ባይገልጽም ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምን እንደሚመስሉ ማየት እንችላለን።

(1) *የጥበብን ቃል መናገር፤* ይህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚገለጥ የጥበብ አነጋገር ነው። ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል በጥበብ መግለጥ ወይም ለተለየ ሁኔታ ወይም ችግር (ሐሥ 6፥10፤ 15፥13-22) መፍትሔ ለመስጠት መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን የጥበብ ቃል መናገር ነው። ይሁን እንጂ ይህ ጥበብ ለዕለታዊው ኑሮ ከሚያስፈልገን ጥበብ ጋር የሚመሳሰል አይደለም። ለዕለታዊው ኑሮ የሚያስፈልገን ጥበብ የሚገኘው የእግዚአብሔርን መንገድ ወይም ቃል በትጋት ስናጠናና ስናሰላስል እንዲሁም በጸሎት ነው (ያዕ 1፥5-6)።

(2) *የዕውቀትን ቃል መናገር፤* ይህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚገለጠው የዕውቀት ንግግር ሰዎችን፣ ሁኔታዎችን ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን የሚመለከት ነው። ይህ የዕውቀት ስጦታ ብዙውን ጊዜ ከትንቢት ስጦታ ጋር በጣም የተያያዘ ነው (ሐሥ 5፥1-10፤ 10፥47-48፤ 15፥7-11፤ 1ቆሮ 14፥24-25)።

(3) *እምነት፤* ይህ ዐይነቱ እምነት ለድነት ከሚያበቃው እምነት ጋር አንድ አይደለም፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚተላለፍ ልዩ የሆነ ዲበ ተፈጥሮአዊ እምነት ሲሆን፣ ያልተለመደና ታምራዊ የሆነ ነገር እንዲፈጸም ክርስቲያን እግዚአብሔርን እንዲያምን የሚያደርገው ነው። እንዲህ ዐይነቱ እምነት ተራራን የሚያንቀሳቅስ እምነት ነው

(1ቆሮ 13፥2)፡፡ ይህም ብዙውን ጊዜ ፈውስንና ታምራትን ከመሳሰሉ ሌሎች ስጦታዎች ጋር ተያይዞ የሚገኝ ነው (በማቴ 17፥20 እና ስለ እውነተኛ እምነት የቀረበውን ማብ ይመ፤ ማር 11፥22-24፣ ሉቃ 17፥6)፡፡

(4) *የመፈወስ ስጦታዎች፤* እነዚህ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት ዲበ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የተስተካከለ አካላዊ ጤንነት እንዲኖር ለማድረግ ነው (ማቴ 4፥23-25፤ 10፥1፣ ሐሥ 3፥6-8፤ 4፥30)፡፡ "ስጦታዎች" የሚለው ቃል በብዙ ቍጥር መጠቀሱ የሚያመለክተው ከብዙ በሽታዎች መፈወስን ሲሆን፣ እያንዳንዱን በሽታ መፈወስ ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነም ያሳያል፡፡ የፈውስ ስጦታዎች በአካሉ ውስጥ ላለ ለሁሉም አባል ልዩ በሆነ መንገድ የሚሰጡ ባይሆኑም (ከ1ቆሮ 12፥11፡30 ጋር ያነጻጽሩ) አባላት ሁሉ ለበሽተኞች ሊጸልዩ ይችላሉ፡፡ እምነት ሲኖር በሽተኞች ይፈወሳሉ (በገጽ 1433 ላይ፣ "መለኮታዊ ፈውስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ ፈውስ በያዕ 5፥14-16 ላይ ያሉትን መመሪያዎች በመታዘዝ ሊመጣ ይችላል (ያዕ 5፥15 እና ማብ ይመ)፡፡

(5) *ታምራትን የማድረግ፤* እነዚህ ስጦታዎች የተለመደውን የተፈጥሮ ሂደት የሚለውጡ የመለኮታዊ ኀይል ሥራዎች ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በሰይጣንና በክፉ ኀይላት ላይ የሚገለጥበትንም መለኮታዊ ሥራዎችንም ያካትታሉ (ዮሐ 6፥2 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1443 ላይ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

(6) *ትንቢትን የመናገር፤* ጊዜአዊ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ በሆነው ትንቢትን የመናገር ስጦታና (1ቆሮ 12፥10) የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታ በሆነው የትንቢት አገልግሎት (ኤፌ 4፥11) መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አለብን፡፡ ትንቢት እንደ አገልግሎት ስጦታ የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነቢያት ሆነው ለሚያገለግሉ አማኞች ብቻ ነው (በገጽ 1866 ላይ፣ "የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ ትንቢት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደ መሆኑ መጠን በማንኛውም መንፈስ ቅዱስን በተሞላ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛል (ሐሥ 2፥17-18)፡፡

ትንቢትን እንደ መንፈሳዊ ስጦታ በሚከተሉት ሁኔታዎች ልንመለከተው እንችላለን፤ (ሀ) ትንቢት ልዩ ስጦታ ሲሆን፣ አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ግፊት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ቃልን ወይም መገለጥን እንዲያመጣ የሚያስችለው ነው (1ቆሮ 14፥24-25፡29-31)፡፡ ትንቢት ቀደም ብሎ የተዘጋጀን ስብከት ማቅረብ አይደለም፡፡ (ለ) በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ትንቢት በይበልጥ ስለ ወደፊቱ አስቀድሞ መናገር አይደለም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወጅ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለ ጽድቅ፣ ስለ ታማኝነትና ስለ ጽናት መምከርና ማበረታታት ነው (14፥3 እንዲሁም በገጽ 1009 ላይ፣ "ነቢይ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ (ሐ) መልእክቱ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ሊገልጥ (14፥25) ወይም ኀይልን፣ ብርታትን፣ መጽናናትን፣ ማስጠንቀቂያንና ፍርድን ሊያመጣ ይችላል (14፥3፡25-26፡31)፡፡ (መ) አያሌ ሐሰተኛ ነቢያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊገቡ ስለሚችሉ (1ዮሐ 4፥1) ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዐይነቱን ትንቢት ጨርሶ ስሕተት የሌለበት መልእክት አድርጋ ልትቈጥረው አይገባም፡፡ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከመስማማቱና ካለመስማማቱ አንጻር (1ዮሐ 4፥1)፣ የቅድስናን ኑሮ ከማበረታታቱና ካለማበረታታቱ አኳያ (1ጢሞ 6፥3) እንዲሁም መልእክቱን የተናገረው ሰው በክርስቶስ ጌትነት ሥር በእውነት የሚኖርና የማይኖር ከመሆኑ አንጻር (1ቆሮ 12፥3) ትክክለኛነቱና እውነተኛነቱ (1ቆሮ 14፥29፡32፤ 1ተሰ 5፥20-21) ሊመረመር ይገባል፡፡ (ሠ) ትንቢት የሚመጣው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በሰው ፈቃድ አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሆን ብላ ነቢያት ነን ከሚሉ መገለጥን ወይም ምሪትን ስለመጠየቋ የሚያመለክት ክፍል በአዲስ ኪዳን አናገኝም፡፡ ትንቢት ለቤተ ክርስቲያን የሚነገረው እግዚአብሔር መልእክት ሲሰጥ ብቻ ነው (1ቆሮ 12፥11፤ 2ጴጥ 1፥21)፡፡

(7) *መናፍስትን የመለየት፤* በአዲስ ኪዳን መናፍስትን የመለየት ስጦታ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራና የክፉ መንፈስን አሠራር ለይቶ ለማወቅ የሚሰጥ ልዩ የሆነ ችሎታ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ይህ ስጦታ ትንቢቶችን በሚገባ ለመለየትና ለመመርመር እንዲሁም መልእክታቸው ከመንፈስ ቅዱስ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የሚረዳ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ልዩ የሆነ ችሎታ ነው (1ቆሮ 14፥29 እና ማብ ፤ 1ዮሐ 4፥1 ይመ)፡፡ በተጨማሪም ይህ ስጦታ የክፉ መንፈስ ዐይነቶችንና አሠራሮችን ለማወቅ ይረዳል፤ ለምሳሌ የድካም መንፈስ (ሉቃ 13፥11)፣ የጥንቈላ መንፈስ (ሐሥ 16፥16)፣ ደንቆሮና ዲዳ መንፈስ (ማር 9፥25፡29)፣ የእውነት መንፈስና የሐሰት መንፈስ (1ዮሐ 4፥6) ወ.ዘ.ተ. በመጨረሻው ዘመን ማብቂያ ላይ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ሲበዙና (ማቴ 24፥5 እና ማብ) መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክርስትና የሚያጣምም ትምህርት ሲስፋፋ (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ) ይህ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን እጅግ የሚያስፈልግ ነው፡፡

(8) *በልዩ ልዩ ልሳን መናገር፤* "ልሳን" (*ግሪክ፡ "ግሎሳ" ቋንቋ ማለት ነው*) የመንፈስ ቅዱስ ዲበ ተፈጥሮአዊ መገለጫ ምልክት እንደ መሆኑ መጠን የሚከተሉትን ልብ ማለት ይገባል፤

(ሀ) ልሳን በመነገር ላይ ያለ የሰዎች ቋንቋ (ሐሥ 2፥4-6) ወይም በምድር ላይ ያልታወቀ ቋንቋ፣ ለምሳሌ "የመላእክት ልሳን" (1ቆሮ 13፥1፤ ምዕ 14 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1669 ላይ፣ "በልሳን መናገር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዐይነቱን ቋንቋ ሰው ሊማረው እንዲሁም ተናጋሪውም ሆነ (1ቆሮ 14፥14) ሰሚዎቹ (1ቆሮ 14፥16) በአእምሮአቸው ሊረዱት አይችሉም።

(ለ) በልሳን መናገር ከአእምሮ ይልቅ (1ቆሮ 14፥2፡14) በሰውየው መንፈስ ደረጃ አባባልን ወይም ንግግርን በመስጠት፣ በአእምሮ ከሚፈጸም ድርጊትም ይልቅ (ከ1ቆሮ 14፥2፡4፡15፡28፤ ይሁ 1፥20) ቀጥተኛ በሆነ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለራስ ወይም ለሌሎች በመጸለይ አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ (በጸሎት፣ በውዳሴ፣ በመባረክ ወይም ምስጋና በማቅረብ)፤ የሰው መንፈስና የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ላይ የሚሆኑበት ነው።

(ሐ) በጉባኤ የሚመጣ ልሳን በመንፈስ ቅዱስ በተሰጠ የትርጒም ስጦታ የቋንቋው ይዘትና ትርጒም ለአማኙ ኅብረተሰብ ተያይዞ መቅረብ አለበት (1ቆሮ 14፥3፡27-28)። ይህም ለጉባኤ የሚሆነውን መግለጥን፣ ዕውቀትን፣ ትንቢትን ወይም ትምህርትን ሊይዝ ይችላል (ከ1ቆሮ 14፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

(መ) በጉባኤ ውስጥ የሚነገር ልሳን በሥርዐት መሆን አለበት። በልሳን የሚናገር ሰው በልቅ ስሜት ውስጥ ወይም ከቍጥጥር ውጪ ሊሆን አይገባም (1ቆሮ 14፥27-28 እንዲሁም በገጽ 1669 ላይ፣ "በልሳን መናገር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(9) *በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ፤* ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በልሳን የተነገረውን መልእክት የመረዳትና የማስተላለፍ ችሎታ ነው። ለጉባኤ በሚተረጐምበትም ጊዜ ልሳኑ ወደ አምልኮና ወደ ጸሎት የሚመራ ወይም እንደ ትንቢት የሚያገለግል ይሆናል። ከዚያም በጉባኤ ውስጥ ያሉ አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ የመጣውን መልእክት ተቀብለው አገልግሎቱን ሊካፈሉ ይችላሉ። በልሳን ተነግሮ ለተተረጐመው መልእክት ጉባኤው በሙሉ ልብ ምላሽ ሲሰጥ ልሳኑ የሚታነጹበት መልእክት ይሆናል (ከ14፥6፡13 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ስጦታ በልሳን ለሚናገረው ሰው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ሊሰጥ ይችላል። በልሳን የሚናገሩ የመተርጐም ስጦታ እንዲሰጣቸው መጸለይ አለባቸው (1ቆሮ 14፥13)።

በርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው። [26]አንድ
ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ አብረው
ይሠቃያሉ፤ አንድ ብልት ቢከብር ሌሎቹም
ብልቶች አብረው ደስ ይላቸዋል።
[27]እንግዲህ እናንተም የክርስቶስ አካል
ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ብልቶች
ናችሁ። [28]እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን
ውስጥ አንደኛ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ ነቢያ
ትን፣ ሦስተኛ መምህራንን፣ ቀጥሎም
ታምራት አድራጊዎችን፣ የመፈወስ
ስጦታዎች ያላቸውን፣ ሌሎችን የመርዳት
ስጦታ ያላ ቸውን፣ የማስተዳደር ስጦታ
ያላቸውንና በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር
ስጦታ ያላቸ ውን ሰዎች መድቦአል።
[29]ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት
ናቸውን? ሁሉስ መምህራን ናቸውን? ሁሉስ
ታምራት ያደርጋሉን? [30]ሁሉስ የመፈወስ
ስጦታዎች አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች
ይናገራሉን[ሀ]? ሁሉስ ይተረጉማሉን?
[31]ነገር ግን ከሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ
40 በብርቱ ፈልጉ።[ለ]

12፥27 ሮሜ12፥5፤ ኤፌ1፥23፤ 4፥12፤ ቈላ1፥18፡24
12፥28 ቍ9፡10፤ ማር16፥17፤ ሮሜ12፥6-8፤ 1ቆሮ10፥32፤ ኤፌ4፥11
12፥30 ቍ10
12፥31 1ቆሮ14፥1፡39
13፥1 ቍ8፤ ማር16፥17
13፥2 ቍ8፤ ማቴ17፥20፤ 21፥21፤ ሐሥ11፥27፤ 1ቆሮ12፥9፤ 14፥2፤ 2ቆሮ8፥7፤ ኤፌ4፥11
13፥3 ዳን3፥28፤ ሉቃ19፥8፤ ሐሥ2፥45
13፥4 1ቆሮ5፥2፤ 1ተሰ5፥14

## ፍቅር

ደግሞም ከሁሉ የሚበልጠውን መንገድ
አሳያችኋለሁ።

13 በሰዎችና በመላእክት ልሳን[ሐ] ብና
ገር፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚ
ጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሿሿ ጸናጽል
ነኝ። [2]የትንቢት ስጦታ ቢኖረኝ፣ ምስጢርን
ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ፣ ተራራ ንም
ከቦታው የሚነቅል እምነት ቢኖረኝ፣ ፍቅር
ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። [3]ያለኝን ሁሉ 1ተሰ 3፥7
ለድኾች ብሰጥ፣ ሰውነቴንም እንዲቃጠል
ለእሳት ብዳርግ፣[መ] ፍቅር ግን ከሌ ለኝ
ምንም አይጠቅመኝም።
[4]ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር

[ሀ]12፥30 ወይም፣ በሌሎች ቋንቋዎች
[ለ]12፥31 ወይም፣ እናንተ ግን ከሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ በብርቱ እየፈለጋችሁ።
[ሐ]13፥1 ወይም ቋንቋዎች
[መ]13፥3 አንዳንድ የጥንት ቅጆች፣ እንድታበይ ሰውነቴንም አሳልፌ ብሰጥ ይላሉ
[ሠ]13፥2 ወይም በሌላ ቋንቋ፤ እንዲሁም ቍ 4፡13፡14፡19፡26 እና 27 ይመ
[ረ]13፥2 ወይም በመንፈሱ

**12፥28 እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን … መድቦአል፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የአገልግሎት ስጦታዎችን በከፊል ዘርዝሮአል (ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችን ዝርዝር ለማግኘት ሮሜ 12፥6-8 እና ኤፌ 4፥11-13 ይመ)። የሐዋርያትን፣ የነቢያትን፣ የወንጌላውያንን፣ የእረኞችንና የአስተማሪዎችን ትርጒም ለመረዳት፣ (በገጽ 1866 ላይ፣ *“የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስጦታዎች”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ በተጨማሪም “የታምራትን” ትርጒም ለመረዳት ዮሐ 6፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ፤ ሌሎችን ስለ መርዳት (ምሕረት ማድረግ) እና ስለ አስተዳደር (መሪነት) ስጦታዎች በሮሜ 12፥7-8 የተጠቀሱትን ማብራሪያዎች ይመልከቱ።

**12፥30 ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን?** ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ያቀረበው መልስ አዘል ጥያቄ አሉታዊ መልስን የሚያስከትል ነው። ይሁን እንጂ፣ የምዕራፍ 12 ፀውድ የሚያሳየው ጳውሎስ ስለ ልሳን ስጦታና ከእርሱ ጋር ተያይዞ ስላለው ልሳንን የመተርጐም ስጦታ በጉባኤ አምልኮ ውስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ መናገሩን ነው። ይህንንም ሲናገር በግል ጸሎት ውስጥና በግል ለእግዚአብሔር ምስጋና በሚቀርብበት ጊዜ በልሳን መናገርን ለመገደብ ጥረት ሳያደርጉ አይደለም (ከ14፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ብዙ አማኞች ለመንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን በሰጡ ቍጥር በልሳን መጸለይ ይቀናቸዋል። በጰንጠቈስጤ ዕለት (ሐሥ 2፥4)፣ በቂሣርያ (ሐሥ 10፥44-46) እና በኤፌሶን (ሐሥ 19፥2-6) በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሁሉ በልሳን ተናገሩ፤ ይህም በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላታቸው ምልክት ነበር (በገጽ 1669 ላይ፣ *“በልሳን መናገር”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**13፥1 ፍቅር ግን ከሌለኝ፤** ምዕራፍ 13 ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ ሲናገር ለነበረው ቀጣይ ሐሳብ ነው። አንድ አማኝ ፍቅር ሳይኖረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ባለቤት መሆኑ ከንቱ እንደሆነም በአጽንዖት ተናግሮአል (ቍ 1-3)። “ከሁሉ የሚበልጠው መንገድ” (1ቆሮ 12፥31) መንፈሳዊ ስጦታዎችን በፍቅር መፈጸም ነው (ቍ 4-8)። መንፈሳዊ ስጦታዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማሟላት እንዲችሉ መንፈሳዊ መገለጦች ሁሉ የሚገዙበት መርሕ ፍቅር ብቻ መሆን አለበት። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች፣ “ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን … በብርቱ ፈልጉ” (1ቆሮ 14፥1) በማለት ይመክራል። በዚህ ዓለም ሌሎችን ለመርዳት፣ ለማጽናናትና ለመባረክ በእውነት የሚፈልጉ፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት በብርቱ መሻት አለባቸው።

**13፥2 ከንቱ ነኝ፤** ሕይወታቸው፣ “በመንፈሳዊ ድርጊቶች” የተሞላ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ያገኙ ላይሆኑ ይችላሉ፤ እንዲያውም አማኞች ላይሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በልሳን የሚናገሩ፣ ትንቢት የሚናገሩ፣ የዕውቀት ስጦታ ያላቸው ወይም ታላቅ የእምነት ሥራ የሚሠሩ፣ ነገር ግን የክርስቶስ ፍቅርና ጽድቅ የሌላቸው በእግዚአብሔር ፊት፣ “ከንቱ ናቸው”። በእግዚአብሔር እይታ የእነርሱ መንፈሳዊነትና እምነት አለን ብለው መመስከራቸው ባዶ ነው (ቍ 1)፤ በመንግሥቱም ውስጥ ስፍራ የላቸውም (ከ6፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)። የጐደላቸው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብቻ ሳይሆን፣ የህልዎቱ ማደሪያ በመሆን ረገድም ባዶ ናቸው። በእነርሱ በኩል የሚተላለፍ መንፈሳዊ መገለጥ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሳይሆን፣ ከሌላ መንፈስ ያውም ከክፉ መንፈስ ነው (ሐሥ 8፥21 እና ማብ፤ 1ዮሐ 4፥1 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1694 ላይ፣ *“እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ለእውነተኛው ክርስቲያናዊ እምነት አስፈላጊው ነገር ሌሎችን በማይጐዳ ሥነ ምግባር የሚገለጥ እንዲሁም ለክርስቶስና ለቃሉ በታማኝነት የሚጸና ፍቅር ነው (ቍ 13 እና ማብ ይመ)።

**13፥4 ፍቅር ታጋሽ ነው፤** ከቍ 4-7 ይመልከቱ። ይህ ክፍል ፍቅርን እንደ ድርጊትና እንደ ባሕርይ የሚገልጽ እንጂ የውስጥ ስሜትና መነሣሣት መሆኑን የሚያሳይ አይደለም። በዚህ ስፍራ የተገለጹት አያሌ የፍቅር ገጽታዎች የእግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና

ነው። ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤
አይታበይም፤ [5]ተገቢ ያልሆነ ነገር
አያደርግም፤ ራስ ወዳድ አይደለም፤
አይበሳጭም፣ በደል ልን አይቈጥርም። [6]ፍቅር
ከእውነት ጋር እንጂ በዐመፅ ደስ አይሰኝም።
[7]ፍቅር ሁል ጊዜ ይታገሣል፤ ሁልጊዜ
ያምናል፤ ሁልጊዜ ተስፋ ያደርጋል፤
ሁልጊዜ ጸንቶ ይቆማል።
[8]ፍቅር ከቶ አይወድቅም፤ ነገር ግን
ትንቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን
ይቀራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል።
[9]ምክንያቱም የምናውቀው በከፊል ነው፤
ትንቢት የምን ናገረውም በከፊል ነው።
[10]ነገር ግን ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል
የነበረው ይሻራል። [11]ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ
እናገር ነበር፤ እንደ ልጅ ዐስብ ነበር፤ እንደ
ልጅም አሰላ ነበር። ከጐለመስሁ በኋላ ግን
የልጅነትን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቻለሁ።
[12]አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ
እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ
ግን ፊት ለፊት እናያለን። አሁን የማውቀው
በከፊል ነው፤ በዚያን ጊዜ እኔ ራሴ ሙሉ
በሙሉ የታወቅሁትን ያህል ዐውቃለሁ።
[13]እንግዲህ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር
እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም
የሚበልጠው ፍቅር ነው።

## የትንቢትና የልሳን ስጦታዎች

**14** ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ
ስጦታዎችን፣ በተለይም ትንቢት
የመናገርን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ።
[2]በልሳን[u] የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው
አይናገርምና፤ ምስጢር የሆነውን በመንፈስ

13፥5 ኢዮ14፥16:17፤ ምሳ10፥12፤ 17፥9፤ ማቴ5፥22፤ 1ቆሮ10፥24፤ 1ጴጥ4፥8
13፥6 2ተሰ2፥12፤ 2ዮሐ1፥4፤ 3ዮሐ1፥3:4
13፥7 ቍ8:13
13፥8 ቍ1:2
13፥9 ቍ12፤ 1ቆሮ8፥2
13፥10 ፊል3፥12
13፥11 መዝ131፥2
13፥12 ዘፍ32፥30፤ ኢዮ19፥26፤ 26፥14፤ 36፥26፤ 1ቆሮ8፥3፤ ገላ4፥9፤ 1ዮሐ3፥2
13፥13 ማቴ22፥37-40፤ ሮሜ5፥2-5፤ 1ቆሮ16፥14፤ ገላ5፥5:6፤ ኤፌ4፥2-5፤ ቈላ1፥4:5፤ 1ተሰ1፥3፤ 5፥8፤ ዕብ6፥10-12፤ 1ዮሐ4፥7-12:16 14፥1 ቍ39፤ 1ቆሮ12፥1:31፤ 16፥14፤ ኤፌ4፥11 14፥2 ቍ6-11:16፤ ማር16፥17፤ 1ቆሮ13፥2

*[u]13፥5 ወይም በሌሎች ቋንቋዎች፤ እንዲሁም ቍ6:18:22:23 እና 39 ይመ*

*መንፈስ ቅዱስን ባሕርይ ያሳያሉ። ማንኛውም አማኝ በዚህ ዐይነቱ ፍቅር ለማደግ መሻት ይኖርበታል።*

**13፥8 ልሳንም ቢሆን ይቀራል፤** *እንደ ትንቢት፣ ልሳን፣ ዕውቀት የመሳሰሉ መንፈሳዊ ስጦታዎች በዘመን መጨረሻ ይሻራሉ። ያ ጊዜ "ፍጹም የሆነው ሲመጣ" (ቍ 10) በሚል ተገልጸአል፤ ይኸውም ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ የአማኝ ዕውቀትና ባሕርይ ለዘላለም ፍጹም የሚሆንበት የታሪክ መጨረሻ ነው (ቍ 12፤ 1፥7)። እስከዚያው ድረስ በየቤተ ክርስቲያናችን መንፈስ ቅዱስና ስጦታዎቹ ያስፈልጉናል። በዚህ ስፍራም ሆነ በሌላ ቦታ በስጦታዎቹ በኩል የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ማብቂያ ላይ እንደሚያቆም የሚያመለክት አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የለም።*

**13፥13 ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው፤** *በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር ከአገልግሎት፣ ከእምነት ወይም መንፈሳዊ ስጦታዎችን ከማግኘት ይልቅ ክርስቶስን የመምሰል ባሕርይን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚወድ በግልጽ ተጠቅሶአል። (1) ተራራን ከሚያንቀሳቅሰው እምነት ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚከናወነው ታላቅ ሥራ ይልቅ (ቍ 1-2:8:13) እግዚአብሔር ከፍተኛ ዋጋና ትኩረት የሚሰጠው በፍቅር፣ በትዕግሥት (ቍ 4)፣ በቸርነት (ቍ 4)፣ ራስ ወዳድ ባልሆነ ፍቅር (ቍ 5)፣ ከእውነት ጋር እንጂ በዐመፅ ደስ በማይሰኝ ፍቅር (ቍ 6)፣ በእውነትና በጽድቅ በሚጸና ፍቅር (ቍ 6-7) በሚገለጸው ባሕርይ ነው።*

*(2) በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ታላቅ የሚሆኑት ለእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅርና የውስጥ ቅድስና ያላቸው እንጂ በውጫዊ ክንዋኔዎች ብቻ ታላቅ የተባሉት አይደሉም (ሉቃ 22፥24-30 እና ማብ)። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአማኝ ልብ ውስጥ የፈሰሰው ፍቅር ምንጊዜም ቢሆን ከእምነት፣ ከተስፋ ወይም ከሌላ ከማንኛውም ነገር ይበልጣል (ሮሜ 5፥5)።*

**14፥1 መንፈሳዊ ስጦታዎችን ... በብርቱ ፈልጉ፤** *በክርስቶስ አካል ውስጥ ለሆኑት ለሌሎች የሚገባው እውነተኛው ፍቅር በውስጣቸው ያላቸው አማኞች በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለመርዳት፣ ለማጽናናት፣ ለማበረታታትና ለማስታጠቅ ይችሉ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መሻት አለባቸው (ከ12፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ትጋት ሳያሳዩ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ይሰጣቸው ዘንድ መጠባበቅ የለባቸውም (12፥7-10)። ነገር ግን ሌሎችን በመምከር፣ በማጽናናትና፣ በማበረታታት ለማገልገል የሚረዷቸውን ስጦታዎች ለማግኘት በትጋት መሻት፣ መፈለግና መጸለይ አለባቸው (ቍ 3:13:19:26)።*

**14፥2 በልሳን የሚናገር፤** *የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጉባኤ አምልኮ ውስጥ የልሳን ስጦታን አስፈላጊነት ከሚገባ በላይ በማጋነን (በገጽ 1800 ላይ፣ "**ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ በሌሎች ስጦታዎችም ቦታ ይበልጥ ትኩረት እንዲያገኝ አደረጉ። ከዚህም በላይ ይህንን ስጦታ ሳይተረጐም ይጠቀሙበት ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አግባብ ያልሆነ አጠቃቀም ለማስተካከል በመሻት፣ በጉባኤ አገልግሎት ልሳን ካልተተረጐመ ጥቅም እንደሌለው አመለከተ። የዚህ ምዕራፍ ዋና ሐሳብ እንደሚከተለው ተዘርዝሮአል፦*

*(1) ካልተተረጐመ ልሳን ይልቅ ትንቢት ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል (ቍ 1-4)።*

*(2) ትንቢትና የተተረጐመ ልሳን ለቤተ ክርስቲያን እኩል አስፈላጊ ናቸው (ቍ 5)።*

*(3) ያልተተረጐመ ልሳን በጉባኤ አገልግሎት ውስጥ ለሌሎች ምንም ጥቅም የለውም (ቍ 6-12)።*

*(4) በጉባኤ በልሳን የሚናገሩ ወይም የሚጸልዩ ቤተ ክርስቲያንን ያንጹ ዘንድ የመተርጐም ስጦታ እንዲሰጣቸው በመሻት መጸለይ ይገባቸዋል (ቍ 13)።*

*(5) በሐዋርያው ጳውሎስ የግል ሕይወት ውስጥ በልሳን ለእግዚአብሔር መናገር ለአምልኮና ለመንፈሳዊ እድገት መንገድ በመሆን ጠቃሚነቱ የጐላ ነበር (ቍ 14-19)።*

*(6) ኀጢአተኛነትን ለመረዳትና የእግዚአብሔርን ሀልዎት ለማወቅ ስለሚያግዝ ካልተተረጐመ ልሳን ይልቅ ትንቢት ይጠቅማል (ቍ 20-25)።*

*(7) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉ በሥርዐት ይሆን ዘንድ ትንቢትን መናገርና በልሳን መጸለይ በአግባቡ መደረግ አለበት (ቍ 26-40)።*

**14፥2 ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና፤** *ይህንን ጥቅስ ለመረዳት ሁለት መሠረታዊ መንገዶች አሉ፤ (1) አንዳንዶች የልሳን*

ስለሚናገር የሚረዳው የለም። 3ትንቢትን
የሚናገር ግን ለማነጽ፣ ለማበረታታትና
ለማጽናናት ለሰው ይናገራል። 4በልሳን
የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን
የሚናገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል።
5ሁላችሁም በልሳን[ㄲ] ብትናገሩ እወዳለሁ፤
ከዚህ ይልቅ ግን ትንቢትን ብትናገሩ
እወዳለሁ። ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ
በልሳን የሚናገር ሰው የተናገረውን
ካልተረጐመ፣ በልሳን ከሚናገር ይልቅ
ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል።
6እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ወደ
እናንተ በምመጣበት ጊዜ፣ በመግለጥ
ወይም በዕውቀት ወይም በትንቢት ወይም
በትምህርት ካልነገርኋችሁ በልሳን ብናገር
ምን እጠቅማችኋለሁ? 7እንደ ዋሽንትና እንደ
በገና ያሉ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች እንኳ
የድምፃቸው ቃና ልዩነት ከሌለው ዜማቸውን
እንዴት ማወቅ ይቻላል? 8ደግሞም መለከት
ትክክል ያልሆነ የጥሪ ድምፅ ካሰማ፣
ለጦርነት ማን ይዘጋጃል? 9እናንተም
እንደዚሁ ናችሁ፤ ከአንደበታችሁ ትርጕም
ያለው ቃል ካልወጣ፣ የምትናገሩትን ማን
ሊያስተውለው ይችላል? ለነፋስ የምትናገሩ
ትሆናላችሁ። 10በዓለም ላይ ብዙ ዐይነት
ቋንቋዎች አሉ፤ ትርጕም የሌለውም ቋንቋ
የለም። 11እንግዲህ አንድ ሰው የሚናገረውን
ቋንቋ ትርጕሙን ካላወቅሁ፣ ለሚናገረው
እንግዳ እሆንበ ታለሁ፤ እርሱም ለእኔ
እንግዳ ይሆንብኛል። 12እናንተም እንደዚሁ
ናችሁ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት
የምትሹ በመሆናችሁ፣ ቤተ ክርስቲያን
የምትታነጽበትን ስጦ ታዎች ለማግኘት
ይበልጥ ፈልጉ።
13ስለዚህ በልሳን የሚናገር ሰው የሚናገ
ረውን መተርጐም እንዲችል ይጸልይ።
14በልሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ
ይጸልያል፤ አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።

14፥3 ቍ4:5፡ 12:17:26:31፡ ሮሜ14፥19
14፥4 ቍ3፡ ማር16፥17፡ 1ቆሮ13፥2
14፥5 ቍ3፡ ዘኍ11፥29
14፥6 ቍ26፡ ሮሜ6፥17፡ 2ቆሮ8፥7፡ ኤፌ1፥17
14፥8 ዘኍ10፥9፡ ኤር4፥19
14፥11 ዘፍ11፥7
14፥12 ቍ3፡ 1ቆሮ12፥1
14፥13 ቍ5
14፥14 ቍ2

ዋና ጥቅም በቤተ ክርስቲያን ሆነ በግል በመሠረቱ ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር መናገር እንደሆነ ይህ ጥቅስ ያመለክታል ብለው ያምናሉ:: በልሳን በመናገር ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚደረግ ከሆነ፣ ተናጋሪው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በጸሎት፣ በውዳሴ፣ በዝማሬ፣ በመባረክና በምስጋና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያደርጋል ማለት ነው:: የተነገረው ነገር "ምስጢር" ነው፤ ማለትም ተናጋሪውም ሆነ ሰሚዎቹ ያልተረዱት ነገር ነው (ከቍ 2:13-17 ጋር ያነጻጽሩ):: በልሳን የተነገረው መልእክት መተርጐም (ቍ 5:13) ጉባኤው በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ወደሚመራው የአምልኮ መንፈስ ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል፤ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት ለቀረበው ጸሎት ወይም ምስጋና ጉባኤውን "አሜን" ያሰኘዋል (ቍ 16፤ ቍ 6 እና ማብ ይመ)::

(2) በሌላ በኩል ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው ነገር የሚያመለክተው ልሳን ካልተተረጐመ በቀር ሊያውቀው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ነው (ቍ 5):: ስለዚህ ልሳን ከተተረጐመ መልእክቱ ሰውን የሚመለከት ይሆናል:: ይህ አመለካከት "ማንም ስለማይረዳው" በልሳን የሚነገረው ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነው በሚለው የሐዋርያው ጳውሎስ አነጋገር የተደገፈ ነው (ቍ 6 እና ማብ ይመ)::

**14፥3 ትንቢትን … ለማነጽ፤** የትንቢት ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት የሚነገረው በይበልጥ የወደፊቱን ሁኔታ ለመተንበይ ሳይሆን የአማኙን እምነት፣ መንፈሳዊ ሕይወትና ግብረገባዊ ውሳኔ በማበረታታት ለክርስቶስና ለትምህርቶቹ በመታመን እንዲጸና ለማድረግ ነው:: ትንቢት የተዘጋጀን መልእክት መስበክ አይደለም፤ ነገር ግን ግለሰብን ወይም ጉባኤን ለማነጽ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት የሚተላለፍ ድንገተኛ መልእክት ነው (በገጽ 1800 ላይ፣ *"ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**14፥4 ራሱን ያንጻል፤** በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አእምሮን በሚያልፍ ሁኔታ፣ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲፈጥር ስለሚያደርግ (ከኤፌ 3፥16፤ ከይሁ 1፥20 ጋር ያነጻጽሩ) ያልተተረጐም ልሳን ተናጋሪውን ያንጻል ማለትም የአማኙን እምነትና መንፈሳዊ ሕይወት ይገነባል (ቍ 26 እና ማብ ይመ):: ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መንገድ እንዲሁም በአእምሮው በመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንደሚያደርግ ተናግሮአል (ቍ 14-15)::

**14፥5 ሁላችሁም በልሳን ብትናገሩ እወዳለሁ፤** በዚህ ስፍራ የተገለጸው የጳውሎስ ፍላጐት አማኞች በግል ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት በሚገናኙበት ጊዜ በልሳን መናገራቸውቁ ነው:: በግልጽ እንደሚታወቀው እንዲህ ዐይነቱ ልሳን ክርስቲያን በአምልኮና በጸሎት በግል ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኝ ይጠቅማል (ቍ 2:4):: ልክ እንደ ትንቢት እውነተኛ ልሳን በጉባኤ ውስጥ ከትርጓሜው ጋር ሲመጣ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽን እንደሚያመጣ ሐዋርያው ጳውሎስ በተጨማሪ ገልጾአል:: ያልተተረጐመ ልሳን ለቤተ ክርስቲያን የሚያመጣው ጥቅም የለም (ቍ 7-9)::

**14፥6 … ካልነገርኳችሁ በልሳን ብናገር ምን እጠቅማችኋለሁ፤** አንዳንድ ጊዜ በልሳን መናገር ክርስቲያን ኅብረተሰብን የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አምልኮ መካከል ተገኝቶ ድንገት በልሳን የሚናገርበትን መላምታዊ ሁኔታ ይገልጻል:: እንዲህ ዐይነቱ ልሳን የመገለጥን ወይም የትምህርትን ቃል ካላመጣላቸው ለእነርሱ ምንም ጥቅም እንደሌለው ይነግራቸዋል:: የዚህ ጥቅስ አቀራረብ በልሳን የተነገረው ቢተረጐም ለጉባኤው የመጣ መገለጥን፣ ዕውቀትን፤ ትንቢትን ወይም ትምህርትን ያዘለ መልእክት ሊሆን ይችላል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በቍ 8 ላይ መልእክት ለማምጣትና ለጦርነት ዝግጅት እንዲደረግ ከሚነፋው መለከት ጋር በማገናዘብ የሰጠው ምስስሎሽ ይህን ትርጓሜ የሚደግፍ ነው:: በሌላ አነጋገር በልሳን የተነገረው ሲተረጐም ለእግዚአብሔር ሕዝብ መልእክትን ያመጣል፤ ይኸውም ከሰይጣን፣ ከኀጢአትና ከረከሱ ዓለማዊ ነገሮች ጋር ለሚደረገው መንፈሳዊ ጦርነት ለመዘጋጀት እንዲሁም የማይቀረውን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ለመቀበል የሚያነቃ መልእክት ሊሆን ይችላል::

**14፥8 መለከት … ለጦርነት ማን ይዘጋጃል፤** በልሳን የሚናገሩ አማኞች የድምፅ ቃናቸው እንዲሰማ በግልጽ መናገር አለባቸው (ቍ 7):: ልክ እንደ መለከት ግልጽ የሆነ መልእክት ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል:: ስለዚህ በልሳን የሚናገሩ የተናገሩት ለሌሎች መታነጽ ይሆን ዘንድ ትርጕሙ እንዲሰጣቸው መጸለይ አለባቸው (ቍ 12)::

15ታዲያ፣ ምን ማድረግ አለብኝ? በመንፈስ
እጸልያለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤
በመንፈስ እዘምራለሁ፤ በአእምሮም
ደግሞ እዘም ራለሁ። 16እንዲህማ ካልሆነ
እግዚአብሔርን በመንፈስ በምታመሰግንበት
ጊዜ፣ ለነገሩ እንግዳ የሆነ ሰው[r] አንተ
የምትናገረውን ካልተረዳ፣ እንዴት አድርጎ
ለምስጋናህ፣ "አሜን" ሊል ይችላል? 17አንተ
በሚገባ ታመሰግን ይሆናል፤ ሌላው ሰው
ግን አይታነጽበትም።
18ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 19ነገር ግን በቤተ
ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተ ማር፣
ዐሥር ሺህ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ፣
አምስት ቃላት በአእምሮዬ ብናገር ይሻላል።
20ወንድሞች ሆይ፤ በአስተሳሰባችሁ
ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፋ ነገር ሕፃናት ሁኑ፤
በአስተሳሰባችሁ ግን ጐልማሶች ሁኑ። 21በሕ
ግም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤
"ቋንቋቸው እንግዳ በሆነ ሰዎች፣
በባዕዳንም አንደበት፣
ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁ፤
ይህም ሆኖ አይሰሙኝም፤"
ይላል ጌታ።

22ስለዚህ በልሳን መናገር ለማያምኑ
የሚሆን ምልክት እንጂ ለሚያምኑ
አይደለም፤ ትንቢት ግን ለሚያምኑ
እንጂ ለማያምኑ አይደለም። 23እንግዲህ
የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአንድነት
በተሰበሰቡበት፣ ሁሉም በልሳን በመናገር
ላይ ሳሉ፣ እንግዶች[s] ወይም የማያምኑ
ሰዎች ወደ ጉባኤው ቢገቡ፣ አብደዋል
አይሉምን? 24ነገር ግን ሁሉም ትንቢት
በመናገር ላይ ሳሉ፣ እንግዳ[t] ወይም
የማያምን ሰው ቢገባ፣ በሁሉ ይወቀሣል፤
በሁሉ ይመረመራል፤ 25በልቡም የተሰወረው
ነገር ይገለጣል፤ እንዲሁም፣ "እግዚአብሔር
በርግጥ በመካከላችሁ ነው" በማለት በግንባሩ
ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።

## ሥርዐት ያለው አምልኮ

26ወንድሞች ሆይ፤ እንግዲህ ምን
እንበል? በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳንዱ

14፥15 ቍ2:14፤ ኤፌ5፥19
14፥16 ዘዳ 27፥15-26፤ 1ዜና16፥36፤ ነህ8፥6፤ መዝ106፥48፤ ማቴ14፥19፤ 1ቆሮ11፥24፤ ራእ5፥14፤ 7፥12
14፥17 ቍ3
14፥19 ቍ6
14፥20 ኤር4፥22፤ ማቴ10፥16፤ ሮሜ16፥19፤ 1ቆሮ3፥11፤ ኤፌ4፥14፤ ዕብ5፥12:13፤ 1ጴጥ2፥2
14፥21 ቍ34፤ ዘዳ28፥49፤ ኢሳ28፥11:12፤ ዮሐ10፥34
14፥22 ቍ1
14፥23 ሐሥ2፥13
14፥25 ኢሳ45፥14፤ ዘካ8፥23፤ ሮሜ2፥16
14፥26 ቍ2:6፤ ሮሜ7፥1፤ 14፥19፤ 1ቆሮ12፥7-10፤ ኤፌ5፥19

[r]14፥16 ወይም የሚጠይቁት መካከል
[s]14፥23 ወይም አንዳንድ የሚጠየቁ
[t]14፥24 ወይም የሚጠይቅ

**14፥15 በመንፈስ እጸልያለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤** ሐዋርያው ጳወሎስ በዚህ ስፍራ የሚጠቅሰው የግል ልምምዱንና በግሉ ልሳንን የሚጠቀምበትን ሁኔታ ነው:: "በመንፈስ እጸልያለሁ" ሲል በመንፈስ ቅዱስ ግፊት በራሱ መንፈስ በልሳን የሚጸልይበትን ሁኔታ ነው:: መንፈስ ቅዱስ እንዲናገር ሲያነሣሣው የአማኝ መንፈስ ይጸልያል (ከ12፥7:11፤ ከሐሥ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ):: በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የሚናገረው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ በግል ስለሚጸልይበት የልሳን ጥቅም ነው:: እርሱ ልሳንን የሚጠቀመው ለጸሎት ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ዝማሬ ለማቅረብ፣ እግዚአብሔርን ለማወደስና ምስጋናን ለመሠዋት ነበር (ቍ 14-16):: "በአእምሮ መጸለይ" ማለት አሁንም በመንፈስ ቅዱስ ግፊት ተምረው ባወቁት ቋንቋ በራስ አእምሮ መጸለይና ማወደስ ነው::

**14፥18 በልሳን ስለምናገር፤** ጳውሎስ የልሳንን ስጦታ ለመጸለይ፣ ለመዘመር፣ ለማወደስና የምስጋና መሥዋዕትን ለማቅረብ ሙሉ በሙሉ በተሰጠው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ የያዘ እንደሆነ ተረድቶአል:: ሐዋርያው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለሚገለጠው ስለዚህ ስጦታ በአክብሮትና በምስጋና ይናገራል:: አንዳንዶች ይህን ጥቅስ ሲተረጒሙ ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ሰዎች ይልቅ በአእምሮ በታወቀ ቋንቋ እንደሚጸልይ መናገሩ ነው ይላሉ:: ነገር ግን አተረጓጐሙ ትክክል አይደለም፤ "የበለጠ" (ግሪክ፡ "ማሉን") የሚለው ቅጽል የሚያብራራው "ልሳን" የሚለውን ስም ሳይሆን፣ "ስለምናገር" የሚለውን ተነጻጻሪ ተውሳከ ግስ ነው:: ስለዚህ ጳውሎስ ይህን ሲናገር "በአእምሮና በታወቀ ቋንቋ ብዙ እጸልያለሁ" ማለቱ ሳይሆን፣ "ከእናንተ ይልቅ በልሳን ብዙ እጸልያለሁ ወይም ብዙውን ጊዜ በልሳን እጸልያለሁ" ማለቱ ነው::

**14፥19 ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፤** ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባልተተረጐመ ልሳን ዐሥር ሺህ ቃላት ከመናገር ይልቅ ሰዎች ሊረዱት የሚችሉትን ጥቂት ቃላት መናገርን እንደሚመርጥ ይናገራል:: ከቍ 18-19 ያለው ክፍል ጳውሎስ በልሳን መናገርን በጉባኤ አምልኮ ከሚያደርገው ይልቅ በግል የጸሎት ጊዜው እንደሚጠቀምበት ያመለክታል::

**14፥22 በልሳን መናገር … የሚሆን ምልክት፤** በጉባኤ የሚነገር ልሳን ለማያምኑ አሉታዊ ምልክት ይሆናል፤ ይኸውም የማያምኑ ከእግዚአብሔር የተለዩ መሆናቸውንና የሚደረገውን ነገር ፈጽሞ ሊረዱ አለመቻላቸውን በማሳየቱ ነው (ቍ 21:23):: ይሁን እንጂ ትንቢት ለሚያምኑ ምልክት ነው፤ ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሥራ መሆኑን ስለሚያውቁና እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሠራ እንደ ሆነ ማረጋገጫ ምልክት በመሆኑ ነው (ቍ 24-25):: አማኞች መንፈስ ቅዱስ መፍሰሱንና (ከሐሥ 10፥44-46፤ 11፥15-17) በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል መገለጡንም (ከ12፥7:10 ጋር ያነጻጽሩ) የሚያውቁበት ምልክት ልሳን ነው::

**14፥24 የማያምን ሰው … በሁሉ ይወቀሳል፤** በማንኛውም ጉባኤ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መኖሩና እርሱም ሥራውን እየሠራ ለመሆኑ እርግጠኛ ምልክቱ ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ መውቀሱ ነው (ዮሐ 16፥8 እና ማብ ይመ):: (1) በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በሚገለጠው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ኀጢአት ይጋለጣል፤ የንስሐ ጥሪ ይደረጋል፤ ኀጢአተኞችም ስለ ኀጢአታቸው ይጸጸታሉ:: ርኩሰት ካልተጋለጠ ስለ ኀጢአት መጸጸት ወይም ስለ ንስሓ ጥሪ ማድረግ አይኖርም፤ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አካሄድ መሠረትም መንፈስ ቅዱስ በግልጽ እየሠራ አይደለም:: (2) በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ኀጢአት ለማጋለጥ (ቍ 25)፣ ልዩ የሆነ የመገለጥ ወይም በሰው አእምሮ ውስጥ ያለውን ሐሳብ የማወቅ ስጦታ አያስፈልግም:: በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት የትንቢት ቃልና የትንቢቱ ግብረገባዊ እውነት ሲታወጅ የነጢአተኞችን ልብ ለመውቀስ በራሱ በቂ ይሆናል (ዕብ 4፥12)::

**14፥26 ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ ይሁን፤** የመንፈሳዊ ስጦታዎች ሁሉ ዋና ዐላማ ቤተ ክርስቲያንንና ግለሰቦችን ማነጽ ነው (ቍ 3-4:12:17:26)::፣ "ማነጽ"

መዝሙር አለው፤ ትምህርት አለው፤
መግለጥ አለው፤ በልሳን መናገር አለው፤
መተርጐም አለው። ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ
ይሁን። [27]በልሳን የሚናገር ቢኖር፣ ሁለት
ወይም ቢበዛ ሦስት በየተራ ይናገሩ፤ ሌላው
ደግሞ ይተርጕም፤ [28]የሚተረጕም ሰው
ከሌለ ግን በጉባኤ መካከል ዝም ይበልና፤
ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር።
[29]ሁለት ወይም ሦስት ነቢያት ይናገሩ፤
ሌሎቹ ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ
ይመዝኑ። [30]ከተቀመጡትም መካከል አንድ
ሰው አንድ ነገር ቢገለጥለት፣ የመጀመሪያው
ተናጋሪ ዝም ይበል። [31]እያንዳንዳችሁ
እንድትማሩና እያንዳንዳችሁ
እንድትበረታቱ፣ ሁላችሁ በየተራ ትንቢት
መናገር ትችላላችሁ። [32]የነቢያት መናፍስት
ለነቢያት ይታዘዛሉ፤ [33]እግዚአብሔር የሰላም
አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም።
በቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ
እንዲሁ ነው፤ [34]ሴቶች በጉባኤ ዝም
ይበሉ፤ ሕግም እንደሚለው እንዲታዘዙ
እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም፤

14፥29 ቍ32:37፤
1ቆሮ12፥10፤
13፥2
14፥32 1ዮሐ4፥1
14፥33 ቍ40፤
ሐሥ9፥13፤
ሮሜ15፥33፤
1ቆሮ7፥17፤
10፥32
14፥34 ቍ21፤
ዘፍ3፥16፤
1ቆሮ11፥5:13፤
ኤፌ5፥22፤
1ጢሞ2፥11:12

(ግሪክ: "አይኮዶሚአ") ማለት በአማኞች ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ ብስለትንና የቅድስና ባሕርይን ማሳደግ ነው። አማኞች ይህንን ዓለም ሳይመስሉ (ሮሜ 12፥2-8) በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካይነት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በይበልጥ እየተለወጡ በቅድስና፣ እግዚአብሔርን በመውደድ፣ ስለ ሌሎች በማሰብ፣ በልብ ንጽሕና፣ በንጹሕ ኅሊናና በእውነተኛ እምነት እንዲያድጉ የሚደረጋቸው (ምዕ 13፤ ሮሜ 8፥13፤ 14፥1-4:26፤ ገላ 5፥16-26፤ ኤፌ 2፥19-22፤ 4፥11-16፤ ቈላ 3፥16፤ 1ተሰ 5፥11፤ ይሁ 1፥20፤ 1ጢሞ 1፥5 እና ማብ ይመ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።

**14፥27 ሌላው ደግሞ ይተርጕም፤** የመንፈሳዊ ስጦታዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ሥርዐትና ሚዛናዊነት ሊኖር ይገባል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልሳን መናገርን ለመጠቀም የሚረዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፤ (1) በማንኛውም ስብሰባ ውስጥ በልሳን የሚናገሩ፣ በልሳን የሚጸልዩ ወይም በልሳን የሚያወድሱ ከሁለት ወይም ከሦስት ሰው በላይ መሆን የለባቸውም፤ ይህም የሚከናወነው በትርጕም ሊሆን ይገባል (ቍ 27-28)። (2) በአንድ ጊዜ በልሳን መናገር ያለበት አንድ ሰው ብቻ ነው (ቍ 27)። (3) በልሳን የተነገረው መልእክት ሁሉ ትክክለኛነት በቤተ ክርስቲያን መመርመር አለበት (ቍ 29:32)። (4) በጊዜው የሚተረጕም ሰው ባይኖር፣ አማኝ በግሉ በልሳን ወደ እግዚአብሔር ሊጸልይ ይችላል (ቍ 28)።

**14፥29 ሌሎቹ ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ ይመዝኑ፤** የተነገረውን ትክክለኛነት ለማወቅ ትንቢት ሁሉ መመዘን አለበት። በአዲስ ኪዳን ዘመን የሚነገር ትንቢት ስሕተት ሊኖርበት ስለሚችል መመዘን እንደሚያስፈልገው ይህ ጥቅስ ያመለክታል። (1) አንዳንድ ጊዜ ትንቢትና በልሳን የሚነገር መልእክት ከእግዚአብሔር የመጣ ቃል ላይሆን ይችላል (ከ1ዮሐ 4፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። በጉባኤ ውስጥ እንኳ ክፉ መናፍስት በሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ወይም በሐሰተኛ ነቢያት አማካይነት ሥራቸውን ሊሠሩ ይችላሉ። ትንቢት መናገር፣ በልሳን መናገር ወይም ማናቸውንም ዲበ ተፈጥሮአዊ ስጦታ መለማመድ አንድ ሰው እውነተኛ ነቢይ ወይም ለእውነተኛ አማኝ ለመሆኑ ማረጋገጫ አይደለም (በገጽ 1519 ላይ፣ "*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ ሰይጣን መንፈሳዊ ስጦታዎችን አስመስሎ ሊሠራ ይችላልና (ማቴ 24፥24፤ 2ተሰ 2፥9-12፤ ራእ 13፥13-14)።

(2) ቤተ ክርስቲያን ትንቢቶችን ለመመርመር የሚዩስችል ተገቢና ሥርዐት ያው መንገድ (ቍ 40) ካላበጀች፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን ለመከተል ዐቅም አጥታለች ማለት ነው። በተጨማሪም ትንቢት ሊቈጣጠሩት የማይቻል የመንፈስ ቅዱስ ግፊት እንዳልሆነ ልብ ይበሉ፤ በአንድ ጊዜ አንድ ነቢይ ብቻ ትንቢት ሊናገር ይገባዋልና (ቍ 30-32)።

(3) ትንቢታዊ መልእክቶችን በተመለከተ የቤተ ክርስቲያን አስተሳሰብ ምን ሊሆን ይገባል? (ሀ) ትንቢት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት መስፈርት መሠረት መፈተን አለበት (ከዘዳ 13፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ትንቢቱ ሊፈጸም ወይም ላይፈጸም እንደሚችል አስበው ራሳቸውን በማዘጋጀት አማኞች ተፈጻሚነቱን መጠባበቅ አለባቸው (ከዘዳ 18፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። (ለ) የተገለጠው የትንቢት ቃል ምክር ከሆነ፣ ጉባኤው፣ "የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ ለመፈጸም ምን ማድረግ አለብን?" ብሎ መጠየቅ አለበት።

**14፥31 ሁላችሁ በየተራ ትንቢት መናገር ትችላላችሁ፤** በሁለቱም መንገድ የምንቀበለው መልእክት ከእግዚአብሔር ቢሆንም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ በሆነው በትንቢት ስጦታና የቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ ክፍል ሆኖ በተጻፈው ትንቢት መካከል ያለው ልዩነት መጠበቅ አለበት። (1) የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሓፊዎች መልእክታቸውን የተቀበሉት በቀጥታ ከመንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ ያስተላለፉትም ያለምንም ስሕተት ነበር። ስለዚህ መልእክታቸው ፍጹም ስሕተት የሌለበት ነው (በገጽ 1941 ላይ፣ "***መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆንና ያለው ሥልጣን***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ይሁን እንጂ ትንቢት በምዕራፍ 12 እና 14 ላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ከሆነው ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥልጣን እንዳለውና ሊሳሳት የማይችል እንደሆነ ሊቈጠር አይገባም (2ጢሞ 3፥16)። መልእክቱ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት ቢመጣም እንዲህ ዐይነቱ ትንቢት ሕጸጽ አልባ እንደሆነ ሊቈጠር አይችልም። መልእክቱ ምንጊዜም ቢሆን ሰው በሚፈጥረው ስሕተት ሊዛባ ይችላል። ስለዚህ ነው ዛሬ ትንቢት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እኩል ተደርጎ ሊታይ የማይገባው። ከዚህም በላይ በአሁኑ ዘመን የሚነገረው ትንቢት ሌሎች አማኞች የመልእክቱን ይዘት እውነተኛነት መርምረው ካላረጋገጡ በቀር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላትቀበለው ትችላለች (ቍ 29 እና ማብ፤ 12፥10 ይመ)። ትንቢት የሚፈተንበት መሠረታዊ መመዘኛ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይኸውም መጠየቅ ያለበት ጥያቄ፣ "መልእክቱ ከሐዋርያት ትምህርት ጋር ይስማማል ወይ?" የሚለው ነው። ምንጊዜም ቢሆን የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ከልምምዶች ሁሉና ከንግግሮች ሁሉ በላይ ሆኖ የሚዳኝ መሆን አለበት።

**14፥34 ሴቶች ... ዝም ይበሉ፤** ይህ ጥቅስ የሚተረጐመው ከቍ 35 አንጻር መሆን አለበት፤

[35]ሴቶች ለማወቅ የሚፈልጉት አንዳንድ
ነገር ካለ፣ ባሎቻቸውን በቤት ይጠይቁ፤
ምክንያቱም ሴት በጉባኤ መካከል ብትናገር
የሚያሳፍር ነው።
[36]የእግዚአብሔር ቃል የወጣው ከእናንተ
ነውን? ወይስ የደረሰው ወደ እናንተ ብቻ
ነውን? [37]ማንም ነቢይ ነኝ የሚል ወይም
መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ የሚል ቢኖር፣
ይህ የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ መሆኑን
ይወቅ፤ [38]ይህን የማያውቅ ቢሆን ግን
እርሱም አይታወቅ።[ገ]
[39]ስለዚህ፣ ወንድሞች ሆይ፤ ትንቢት
ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፤ በልሳን
መናገርንም አትከልክሉ፤ [40]ነገር ግን ሁሉም
ገላ 3፥5 በአግባብና በሥርዐት ይሁን።

## የክርስቶስ ትንሣኤ

**15** አሁንም፣ ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክ
ሁላችሁንና የተቀበላችሁትን
ደግሞም ጸንታችሁ የቆማችሁበትን ወንጌል
ላሳ ስባችሁ እወዳለሁ፤ [2]የሰበክሁላችሁን
ቃል አጥብቃችሁ ብትይዙ፣ በዚህ ወንጌል
ትድናላችሁ፤ አለዚያ ያመናችሁት በከንቱ
ነው።
[3]እኔ የተቀበልሁትንና ከሁሉ በላይ
የሆነውን[ሀ] ለእናንተ አስተላልፌአለሁ፤
ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት ክርስቶስ
ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ [4]ተቀበረ፤ በቅዱሳት
መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው
ቀን ተነሣ፤ [5]ከዚያም ለኬፋ[ለ] ታየ፤
ቀጥሎም ለዐሥራ ሁለቱ ታየ፤ [6]ከዚያም
በኋላ ከአምስት መቶ በላይ ለሚሆኑ
ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነዚህም
አብዛኞዎቹ በሕይወት አሉ፤ አንዳንዶቹ
ግን አንቀላፍተ ዋል። [7]ከዚያም ለያዕቆብ
ታየ፤ በኋላም ለሐዋርያት በሙሉ ታየ፤ [8]
ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምቈጠር
ለእኔ ደግሞ ታየ።
[9]እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ፣ ሐዋርያ
ተብዬ ልጠራ እንኳ የማይገባኝ ነኝ፤
ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን
አሳድጃለሁ፤ [10]ነገር ግን በእግዚአብሔር

14፥36 ዕብ12
14፥37 ሐሥ11፥27፤ 1ቆሮ13፥2፤ 2፥15፤ 12፥1፤ 2ቆሮ10፥7፤ 1ዮሐ4፥6
14፥39 ቍ1፤ 1ቆሮ12፥31፤ ኤፌ4፥11
14፥40 ቍ33፤ ቈላ2፥5
15፥1 ኢሳ40፥9፤ ሮሜ2፥16፤ 1ቆሮ3፥6፤ ገላ1፥8
15፥2 ሮሜ1፥16፤ 11፥22
15፥3 ኢሳ53፥5፤ ማቴ26፥24፤ ሉቃ24፥27፤ 24፥44፤ ዮሐ1፥29፤ ሐሥ17፥2፤ 26፥22፡23፤ 1ቆሮ11፥2፤ ገላ1፥4፡12፤ 1ጴጥ2፥24
15፥4 ማቴ16፥21፤ 27፥59፡60፤ ዮሐ2፥21፡22፤ ሐሥ2፥24፡25፡30፡31
15፥5 ማር16፥14፤ ሉቃ24፥34፡36-43 15፥6 ቍ18፡20፤ ማቴ9፥24 15፥7 ሉቃ24፥33፤ 36፡37፤ ሐሥ1፥3፡4፤ 15፥13 15፥8 ሐሥ9፥3-6፡17፤ 1ቆሮ9፥1፤ ገላ1፥16 15፥9 ሐሥ8፥3፤ 1ቆሮ10፥32፤ 2ቆሮ12፥11፤ ኤፌ3፥8፤ 1ጢሞ1፥15 15፥10 ሮሜ3፥24፤ 12፥3፤ 2ቆሮ11፥23፤ ፊል2፥13፤ ቈላ1፥29

*[ገ]14፥38 አንዳንድ ቅጆች፣ ይህን ለማወቅ የማይፈልግ ቢሆን እርሱም አይታወቅ ይላሉ።*
*[ሀ]15፥3 ወይም፤ ከሁሉ በፊት*
*[ለ]15፥5 ጴጥሮስን ማለት ነው*

ይህም ሴቶች በቤት ጠይቀው ሊረዱት የሚገባቸውን ጥያቄ በማንሣት አገልግሎት እንዳቋረጥ እንዳያደርጉ የሚከለክል መመሪያ ነው። በ11፥5 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሴቶች በጉባኤ ሊጸልዩና ትንቢት ሊናገሩ እንደሚችሉ አመልክቶአል (በ1ቆ 14፥23-24፡31 ላይ "ሁሉና ... እያንዳንዳችሁ" የሚለውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)።

**14፥39 ትንቢት ለመናገር ... በልሳን መናገርንም አትከልክሉ፤** ይህ ቀምር ትእዛዝ ጳውሎስ ትንቢት መናገርንና በልሳን መናገርን በተመለከተ ላስተማረው ትምህርት ማጠቃለያ ነው። የቆሮንቶስ ሰዎች የእርሱን ትምህርት የ"ጌታ ትእዛዝ" እንደ ሆነ አድርገው ባይቀበሉ፣ ነቢያት ወይም በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ሰዎች አለመሆናቸውን ያሳያሉ (ቍ 37-38)። ዛሬ የእግዚአብሔርን ቃል እንከተላለን የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት ሆኖም በልሳን መናገርን የሚከለክሉና ሕዝባቸው ትንቢትን እንዲናገር ፈጽሞ የማይፈልጉ ቍ 37-38ን እንዴት እንደሚተረጕሙት ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው።

**15፥2 የሰበክሁላችሁን ቃል አጥብቃችሁ ብትይዙ፤** አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ብቻ አይደሉም። ነገር ግን አማኞች በወንጌል ሙሉ መልእክት ራሱን በገለጠው መሠረት በክርስቶስ የሚያምኑ ናቸው (ቍ 1-4)። በክርስቶስ ያላቸው እምነት ምንጊዜም ቢሆን በእግዚአብሔር ቃልና በሐዋርያት አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ ነው (ቍ 1፡3፤ 11፥2፡23፤ ሮሜ 6፥17፤ ገላ 1፥12)። ከዚህም የተነሣ አማኞች ለመጽሐፍ ቅዱሱ ክርስቶስ ራሳቸውን በማስገዛት እርሱን ጌታና አዳኝ አድርገው የተቀበሉ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሚኖሩ ሰዎች ናቸው ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ። ለቃሉ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ይገዛሉ፤ ትምህርቱን አጥብቀው ይይዛሉ፤ የተስፋ ቃሎቹን ያምናሉ፤ ማስጠንቀቂያዎቹን በጥንቃቄ ያስተውላሉ፤ ትእዛዞቹንም ይከተላሉ። ለእግዚአብሔር ቃል ምርኮኛ የሆኑ ሰዎች ናቸው፤ ቅዱሳት መጻሕፍትንም መሠረት በማድረግ የሰውን ሐሳብ ሁሉ ይመረምራሉ፤ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ የሆነውን ማናቸውንም ነገር አይቀበሉም።

**15፥8 ከሁሉም በኋላ፤** "ከሁሉም በኋላ" የሚለው የሐዋርያው ጳውሎስ ዐረፍተ ነገር ፍጹም በሆነ መንገድ መታየት አለበት። ሐዋርያው ጳውሎስ ከሞት ከተነሣው ጌታ ጋር በግል ተገናኝቶ ከእርሱ ልዩ የሆነ የወንጌልን ተልእኮ በመቀበል፣ የመጀመሪያውንና መሠረታዊውን የክርስቶስ ምስክርነት ምሥረታ ሥራ ውስጥ ለመግባት ከሐዋርያት ሁሉ የመጨረሻው እንደ ሆነ ተገልጾአል (ከሐሥ 9፥3-8፤ 22፥6-11፤ 26፥12-18 ጋር ያነጻጽሩ)። የመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ መሥራችና የመሠረት ማእዘን ድንጋይ ናቸው (ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ፤ ከማቴ 16፥18፤ ከራእ 21፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ምክንያት የተሰጣቸው የሐዋርያነት ሥልጣን ልዩ የሆነና የማይደገም ነው። ከሙታን የተነሣው ጌታ ቀጥተኛ ምስክሮችና መልእክተኞች ስለሆኑ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን መሠረት አነጹ፤ ይህም መሠረት ሊለወጥ ወይም ሊጨመርበት ፈጽሞ የማይችል ነው። ስለዚህ የመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና ጳውሎስ ሥልጣናቸውን የሚያወርሱት ምትክ አይኖራቸውም።

**15፥10 የእግዚአብሔር ጸጋ፤** ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለአማኞች በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ሀልዎትና ፍቅር ነው፤ ይህም ጸጋ ለእነርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ይቅርታ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የሚያስችል ኀይል ይሰጣል (ዮሐ 3፥16፤ ፊል 2፥13፤ 1ጢሞ 1፥15-16 እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ "*እምነትና ጸጋ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

ጸጋ አሁን የሆንሁትን ሆኛለሁ፤ ለእኔም
የተሰጠኝ ጸጋ ከንቱ አልሆነም፤ እንዲያውም
ከሁሉም በላይ በትጋት ሠርቻለሁ፤ ዳሩ ግን
እኔ ሳልሆን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር
ጸጋ ነው። 11እንግዲህ እኔም ሆንሁ እነርሱ
የምንሰብከው ይህንኑ ነው፤ እናንተም
ያመናችሁት ይህንኑ ነው።

## የሙታን ትንሣኤ

12ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ
የሚሰበክ ከሆነ፣ ከእናንተ አንዳንዶቹ
እንዴት የሙታን ትንሣኤ የለም ይላሉ?
13የሙታን ትንሣኤ ከሌለማ ክርስቶስም
አልተነሣም ማለት ነዋ! 14ክርስቶስም
ካልተነሣ ስብከታችን ዋጋ ቢስ ነው፤
እምነታችሁም ከንቱ ነው። 15ከዚህም በላይ፣
እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሞት አስነሥቶታል
ብለን በመመስከራችን፣ ሐሰተኞች
የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፤
ሙታን የማይነሡ ከሆነ፣ ክርስቶስንም
አላስነሣውም ማለት ነው፤ 16ምክንያቱም
ሙታን ካልተነሡ፣ ክርስቶስም አልተነሣም።
17ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ
ከንቱ ነው፤ እናንተም እስከ አሁን ድረስ
ከነኀጢአታችሁ አላችሁ ማለት ነው።
18እንዲህም ከሆነ፣ በክርስቶስ ያንቀላፉት
ጠፍተዋል ማለት ነው። 19ክርስቶስን ተስፋ
ያደረግ ነው ለዚህች ሕይወት ብቻ ከሆነ፣
ከሰው ሁሉ ይልቅ የምናሳዝን ነን።

20ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ
በኵራት ሆኖ በርግጥ ከሙታን ተነሥቶአል።
21ሞት በአንድ ሰው በኩል እንደ መጣ፣
የሙታንም ትንሣኤ በአንድ ሰው በኩል ሆኖ
አልፏል። 22ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ፣
እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን
ፊል 3፥20-21 ይሆናሉ፤ 23ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ
ተራ ይሆናል፤ መጀመሪያ በኵራት የሆነው
ክርስቶስ፣ ከዚያም በኋላ እርሱ ሲመጣ
የክርስቶስ የሆኑት። 24ከዚያም ግዛትን፣
ሥልጣንና ኀይልን ሁሉ ከደመሰሰ በኋላ
መንግሥትን ለእግዚአብሔር አብ ሲያስረክብ፣
ያን ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል። 25ጠላቶቹን
ሁሉ ከእግሩ ሥር እስኪያደርግ ድረስ
ሊነግሥ ይገባዋልና። 26የሚደመሰሰውም
የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው፤ 27"ሁሉን ነገር
ከእግሩ ሥር አስገዝቶለታል" ተብሎአልና፤
ነገር ግን፣ ሁሉን ነገር አስገዛለት ሲል፣ ሁሉ
ነገር በክርስቶስ ሥር እንዲገዛ ያደረገውን
እግዚአብሔርን እንደማይጨምር ግልጽ ነው።
28ሁሉ ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ
በሁሉ እንዲሆን ወልድ ራሱ ደግሞ ሁሉን
ላስገዛለት ለእርሱ ይገዛል።

29ትንሣኤ ከሌለማ ለሞቱ ሰዎች ብለው
የሚጠመቁት ምን እያደረጉ ነው? ሙታን
ከቶ የማይነሡ ከሆነ፣ ሰዎች ለእነርሱ
ብለው ለምን ይጠመቃሉ? 30እኛስ ብንሆን
ዘወትር ለአደጋ የምንጋለጠው ለምንድን
ነው? 31ወንድሞች ሆይ፤ እኔ በየቀኑ
እሞታለሁ፤ ይህ ንንም በጌታችን በክርስቶስ
ኢየሱስ በእናንተ ላይ ባለኝ ትምክሕት
አረጋግጣለሁ። 32በኤፌሶን ከአራዊት ጋር
የታገልሁት ለሰው አስተያየት ብቻ ከሆነ
ትርፌ ምንድን ነው? ሙታን የማይነሡ
ከሆነ፤

"ነገ ስለምንሞት፣
 እንብላ፣ እንጠጣ፤" እንደሚሉት
  መሆናችን ነው።

33አትሳቱ፤ "መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን
ጠባይ ያበላሻል።" 34ወደ ስክነ ልቦናችሁ
ተመለሱ፤ ኀጢአትንም አትሥሩ፤
እግዚአብሔርን የማያውቁ አሉና ይህንንም የም
ለው ላሳፍራችሁ ነው።

## የትንሣኤ አካል

35ነገር ግን፣ "ሙታን እንዴት ይነሣሉ?
የሚመጡትስ በምን ዐይነት አካል ነው?"
የሚል ሰው ሊኖር ይችላል። 36አንተ ሞኝ!
የምትዘራው ካልሞተ ሕይወት አያገኝም።
37የምትዘራውም የስንዴ ወይም የሌላ
ዐይነት ዘር ቅንጣት ብቻ እንጂ ወደ ፊት
የምታገኘውን አካል አይደለም። 38እግዚአብሔር
ግን እንደ ፈቀደ አካልን ይሰጠዋል፤
ለእያንዳንዱም የዘር ዐይነት የራሱን አካል
ይሰጠዋል። 39ሥጋ ሁሉ አንድ አይደለም፤
የሰው ሥጋ አንድ ነው፤ የእንስሳት ሥጋ
ሌላ ነው፤ የዓሣ ሥጋ ሌላ ዐይነት ነው።
40እንዲሁም ሰማያውያን አካላት አሉ፤ ምድ
ራውያን አካላት አሉ፤ ነገር ግን የሰማያዊ
አካላት ክብር አንድ ነው፤ የምድራዊም አካ
ላት ክብር ሌላ ነው። 41የፀሐይ ክብር አንድ
ዐይነት ነው፤ የጨረቃ ክብር ሌላ ነው፤
የከዋክብት ደግሞ ሌላ ነው፤ የአንዱም
ኮከብ ክብር ከሌላው ኮከብ ክብር ይለያል።

15፥11 ገላ2፥6
15፥12 ቍ4፤ የሐ11፥24፤ ሐሥ17፥32፤ 23፥8፤ 2ጢሞ2፥18
15፥14 1ተሰ4፥14
15፥15 ሐሥ2፥24
15፥17 ሮሜ4፥25
15፥18 ቍ6፡20፤ ማቴ9፥24
15፥19 1ቆሮ4፥9
15፥20 ቍ6፡18፡23፤ ማቴ9፥24፤ ሐሥ26፥23፤ 1ጴጥ1፥3
15፥21 ቍ12፤ ሮሜ5፥12
15፥22 ሮሜ5፥14-18፤ 1ቆሮ6፥14
15፥23 ቍ20፡52፤ 1ቆሮ3፥23፤ 1ተሰ2፥19
15፥24 ዳን2፥44፤ 7፥14፡27፤ ሮሜ8፥38፤ 2ጴጥ1፥11
15፥25 ቍ27፤ ኢሳ9፥7፤ 52፥7፤ ማቴ22፥44
15፥26 2ጢሞ1፥10፤ ራእ20፥14፤ 21፥4
15፥27 ቍ25፤ መዝ8፥6፤ ማቴ22፥44፤ 28፥18
15፥28 1ቆሮ3፥23፤ ፊል3፥21
15፥30 2ቆሮ11፥26
15፥31 ሮሜ8፥36
15፥32 ኢሳ22፥13፤ ሉቃ12፥19፤ ሐሥ18፥19፤ 2ቆሮ1፥8
15፥33 ምሳ22፥24፡25፤ 1ቆሮ6፥9
15፥34 1ቆሮ4፥14፤ ገላ4፥8
15፥35 ሕዝ37፥3፤ ሮሜ9፥19
15፥36 ሉቃ11፥40፤ 12፥20፤ ዮሐ12፥24
15፥38 ዘፍ1፥11 15፥41 መዝ8፥1፡3፤ 19፥4-6

**15፥17 ክርስቶስም ካልተነሣ፣** አንዳንዶች የክርስቶስን አካላዊ ትንሣኤ ይክዱ ነበር (ቍ 12)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ መልስ ሲሰጥ ክርስቶስ ከሙታን ካልተነሣ፣ ከኀጢአት አርነት መውጣት እንደማይኖር ተናግሮአል። የክርስቶስን አካላዊ ትንሣኤ ተጨባጭ እውነታ የሚክዱ የክርስትናን እምነት በአጠቃላይ ይክዳሉ። እነርሱ እግዚአብሔርንና ቃሉን የሚቃወሙ ሐሰተኛ ምስክሮች ናቸው። እምነታቸው ዋጋ የለውም፤ ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያኖችም አይደሉም።

**15፥29 ለሞቱ ሰዎች ብለው የሚጠመቁት፣** እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት በሞት ከተለዩአቸው ክርስቲያን ጓደኞቻቸው ወይም ቤተሰቦቻቸው ጋር በሚመጣው ሕይወት እንደገና ለመገናኘት በመፈለግ ክርስቲያን ሆነው የሚጠመቁትን ሰዎች የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "ሙታን ካልተነሡ" እንዲህ ማድረጉ ፍጹም ከንቱ ነው (ቍ 16-17)።

**15፥35 ሙታን እንዴት ይነሣሉ?** ከቍ 35-54 ይመልከቱ። በዚህ ስፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ የሙታን ትንሣኤን በተመለከተ ያለውን አስተምህሮ መግለጽ የጀመረበት ስፍራ ነው። የበለጠ ለመረዳት በገጽ 1810 ላይ፣ "አካላዊ ትንሣኤ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።